# ምልክት

አረፍ አረፍ በሉ። ሁላችሁም፡ እንደምን አደራችሁ! ዛሬ ጠዋት በጌታ አገልግሎት፡ እንደገና በመሳተፋችን ደስ ብሎኛል... እንደገና ተመልሰን እንምጣ እንምጣ አላወቅንም ነበር፡ ሆኖም ጌታ መንገድ አበጀልን፡ እነሆም ለአገልግሎቱ ተመልሰን መጥተናል። ዛሬ በዚህ ማለዳ፡ በዚህ የሰንበት ትምህርት፡ በቃሉ ውስጥ፡ አስደናቂ ጊዜዎችን እንጠብቃለን። እናም ዛሬ ማታ የፈውስ አገልግሎቶች እንደገና ይኖረናል፡ የጌታ እራት አገልግሎትም ይከተላል።

2 አሁን ደግሞ ልጅን ለጌታ አደራ የምንሰጥበት—አገልግሎት አለን፡ እንደሚመስለኝም... ወንድም ኔቪል አንድ ሰው ልጃቸው ለጌታ አደራ እንዲሰጥላቸው እንደፈለጉ ነግሮኛል። እናም፡ በዚህ ጊዜ ህፃኑን ይዘው ቢመጡ። ወንድማችን ወይም፡ አንዳቸው፡ ኦርጋን ወይም ፒያኖው፡ አንዱ እየተጫወቱልን ይቆያሉ። ህጻኑንም ወደዚህ አቅርቡት። ስለዚህ በቀጥታ፥ በቻልነው ፍጥነት፡ ወደ ቃሉ ለመግባት እንድንችል፡ ለጌታ አደራ የመስጠቱ ክፍለ ጊዜ እናደርጋለን።

3 ምክንያቱም፡ ለቃሉ—መገዛትን እንወዳለን። ጊዜአችን ለጌታ ቃል መስጠታችን፡ ዋናው—ነገሩ ያ ነው። ስለዚህ ዛሬ እዚህ ሁላችሁንም ለመገናኘት፡ እና—ለዚህ... አገልግሎት ለመገኘት መታደላችን በጣም እናመሰግናለን።

4 ተሳስቼ ሳልሆን አልቀረሁም። ችግር የለውም፡ እህቴ። እ—እ—እንደዚያ መስሎኝ ነበር። ምናልባት ስህተት ሊሆን ይችላል። እሺ። አሁን፡ በጣም፡ አመሰግናለሁ፡ ያው ነው። ምናልባት ይህ፡ በሌላ ሰው፡ በሌላ ሰው በኩል የመጣ ይመስለኛል፡ እና ትንሽ አሰቸጋሪ አድርጎታል።

5 አሁን ሁላችሁም ጥሩ ስሜት ተሰምቷችኋል? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።]... ? ... እግዚአብሔር ይመስገን!

6 [ወንድም ኔቪል፡ "እነሆ ይዛቸው እየመጣች ነው" አለ።—አርታዒ።] አሁን፡ ኦህ፡ ይኸው፡ ጨቅላዎቹ እነዚህ ናቸው። ይቅርታ። እኔ። እሺ፡ ሽማግሌው፡ እባክህ ወዲህ ና? ["አዎን፡ ጌታዬ።"]

7 እሺ፡ እነዚህ ሁለት፡ ህጻናት ሴት ልጆች፡ ትናንሽ ባለ ቡናማ-አይኖች ሴቶች! ሃ? ቆንጆ ናት። ስሟ ማን ነው? ተመልከቷት እስኪ! [እናትየው፡ "ጄኒፈር ሊ" አለች።—አርታዒ።] ጄኒ? ["ጄኒፈር ሊ።"] ጄኒፈር ሊ። የእያት ስም ማን ነው? ["ሴሬፐት።"] ሴሬፐት። ከየት ነሽ፡ እህት ሊ? ["ቨርሳይልስ፡ ኢሊኖይ።"] ቨርሳይልስ፡ ኢሊኖይ። እንዴት ድንቅ ነው!

8 አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ። ይኸውላችሁ፡ ብዙውን ጊዜ፡ የልጆች ጥምቀት የሚሉት ነገር አ—አላቸው፥ እኛ ልጆችን በማጥመቅ አናምንም፡ ምክንያቱም ገና ኃጢአት ስላልሠሩ፡ ገና እጅግ ትንሽ ስለሆኑ። ነገር ግን ልጆችን ለጌታ አደራ በመስጠት እናምናለን። አሁን እኔና ሽማግሌው እጃችንን በሕፃኗ ላይ እናኖራለን። ጄኒ፡ ነው ያልሺኝ? [ወንድም ኔቪል "ጄኒፈር" አለ።—አርታዒ።] ጄኒፈር። እሺ።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

9 የሰማይ አባት ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት ጄኒፈር የምትባለውን ትንሽ ልጅ፡ ወደ አንተ፡ ሰናቀርባት፡ ለጌታ አደራ ለመስጠት፡ እነሆ እናቷ እና ወዳጆቻቸው ከሩቅ አምጥተዋቸዋል። በአንተ ዘመን፡ እንደዚህ ባሉ ሕፃናት ላይ እጅህን እንደጫንህ እናውቃለን፡ እንዲህም—አልክ፡ “ሕፃናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ፡ አትከልክሉአቸው፡ የሰማይ መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።” እነሆ አሁን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአገልግሎት ሕይወት፡ ለአንተ እንሰጣታለን። አሜን።

10 የሌላኛዋ ህጻን ልጅ ስም ማን ነው? [እናትየው “ኮኒ ሊን፡” አለች።—አርታዒ።] ኮኒ ሊን። እሺ፡ ህጻን ኮኒ፡ ትንሽ እንደሆንኩ እንዲሰማኝ፡ ታደርጊኛለሽ። ኦህ፡ ፈራሽ’ዴ? ኦህ፡ ይህ ነገር አያስኬድም፡ እናት። በጣም ጥሩ።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

11 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እናቲቱ ዛሬ ጠዋት ይህችን ህጻን ኮኒን፡ ለልዑል እግዚአብሔር አደራ ለመስጠት አገልግሎት ይዛት መጥታለች። ታሳድጋት ዘንድ፡ ይህችን ህጻን ልጅ ሰጥተሃታልና፡ እነሆ ዛሬ በፊትህ ለማቅረብ፡ ከህጻን እህቷ ጋር አምጥታቸዋለች። የሰማይ አባት ሆይ፡ አቤቱ ምህረትህን እለምናለሁ፡ እጸልያለሁ። ቤተሰቡን ባርክ። ህጻኗን ባርካት። በእርሷ ላይ እጃችንን ሰንጭን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአገልግሎት ሕይወት ለአንተ ሰጠናቸው። አሜን።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ልጆቻችሁም እንዲሁ።

አቤት፡ አሁን እጅግ ብዙ ልጆች መጡልን!

12 የህጻኑ ልጅ ስም ማን ነው? [እናትየዋ፡ “ጆኤል ሊ ዋትሰን” አለች።—አርታዒ።] ጆኤል ሊ ዋትሰን። [“ጆኤል ሊ።”] ጆኤል ሊ ዋትሰን። እንዴት ያለ ውብ ልጅ ነው፡ ባለ ትልልቅ ሰማያዊ አይኖች! ማይ! እናንተስ ከየት ናችሁ? [“ኢስትማን፡ ጆርጂያ።”] ከጆርጂያ። [“እሃ-ሃ።”] ከደቡብ ትሆናላችሁ ብዬ አሰቤ ነበር። አላወቅኩም… [“እይ፡ ቤታችን እንኳ ቲፍተን ውስጥ ነው። እዚያ ነው።”] ኦህ፡ አዎን። ኦህ፡ ሰላም! ይህ ውብ የሆነ፡ የጆርጂያ ወንድ ልጅ ነው፡ ስለዚህ፡ ሃ? እሺ፡ ወዳጄ። አዎን፡ ጌታዬ፡ በጣም ጥሩ ነው። ደግሞም፡ መናገር ይችላል። እናንተስ?

ራሶቻችን ዝቅ እናድርግ።

13 የሰማይ አባት ሆይ፡ እነሆ ይህን ውድ ልጅ ይዘን እንቀርባለን፡ እናት እና አባትም ከጋብቻቸው ኅብረት—ጋር እነሆ እዚህ ቆመዋል። ይህን ትንሽ ልጅ ሰጥተሃቸዋል፡ እነርሱም ወደ አንተ አመጡት። ይህ እንዴት ያለ ውብ ትዕይንት ነው፡ ልክ ልጅን ፍለጋ እንደጸለየችው፡ እንደ ጥንቷ፡ ሐና፥ እግዚአብሔርም—ልጁን ሰጣት፡ እሷም ወደ እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ፡ መልሳ አመጣችው። ጌታ ሆይ፡ ይህ ህጻን ልጅ አገልጋይህ እንዲሆን፡ ፍቀድ፡ አባትና እናት እንዲባረኩ፡ ለማሳደግም ጤናና ጥንካሬ ይኑራቸው። ረጅምና፡ ደስተኛ ሕይወት ይኑር፡ እኛም ወደ አንተ ሰናቀርበው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ አገልጋይህ ይሁን። አሜን። (ተባረክ!) ጥሩ ሰው፡ ምናልባትም እንደ ሳሙኤል ያለ ሌላ ትንሽ ነቢይ አድርገው።

14 አሁንም እነሆ እነዚህ ሁለት ውብ ወንዶች። አቤት! ለካ፡ ሦስቱ ናቸው? እሺ፡ መላው ቤተሰብ ነው። ስምህ ማን ነው? [ልጁ “ማይክል፡” አለ።—አርታዒ።] ማይክል። ያንተስ? [ሌላኛው ልጅ “ፖል፡” አለ።] ፖል። እንዴት ያሉ ድንቅ ሰሞች ናቸው! የአንቺስ? [ልጅቷም “ዴቢ፡” አለች።] ዴብራ። በጣም ጥሩ ነው። ማይክል፡ ፖል፡ እና ዴብራ። የአያት ስምህ ማን ነው? [አባትየው፡ “ኤሊስ” አለ።] ኤሊስ? [“አዎ።”] መልካም፡ እላችኋለሁ፡ በጣም ጥሩ ቤተሰብ ነው።

15 ታውቃላችሁ፡ እንደዚህ አይነት ትናንሽ ልጆች ሳይ፡ ትንሽ ልጅ ሳለሁ ሁልጊዜ ወደ ኋላ ትዝ ይለኛል። እንግዲህ የድሮ አባባል ሲሉ፡ እንደምታውቁት፡ “አሁን እግርህን ይረግጣሉ፡ በኋላም ልብህን” ይላሉ፡ ቢሆንም ለጌታ አደራ ስንሰጣቸው እንዲህ ይሆናል ብዬ አላምንም። እዚህ ጋር ሐላፊነት አለብሽ፡ እግዚአብሔርም ይህን እጅሽ ላይ ሰጥቶሻል። ሰባኪ አድርጎሻል። ሁሌም ስለ ሴት ሰባኪዎች እናገራለሁ፡ ታውቃላችሁ፡ ግን እያንዳንዷ እናት ሰባኪ ናት፥ ጉባኤዋ እነዚህ ናቸው፡ አያችሁ፡ አባትየው ስራ ላይ ሲውል፡ እነዚህን ህጻናት በትክክል ማሳደግ ነው። ሐላፊነት አላችሁ። እግዚአብሔር ሁለታችሁን ይባርካችሁ። ጥሩ ቤተሰብ አላችሁ።

16 የሰማይ አባት ሆይ፡ እነሆ ማይክልን ይዘን በፊትህ ቀርበናል፡ የበኩር ልጅ ይመስላል። ለኢየሱስ ክርስቶስ አደራ ለመስጠት፡ እነሆ እጆቻችንን፡ በራሱ ላይ እንጭናለን። ቤተሰቡም ታናናሾቹን ይዘው መጥተዋል ያሳድጓቸው ዘንድ—አንተ ሰጥተሃቸዋልና፡ ሆኖም ያለ አንተ እርዳታ፡ ብቁዎች እንዳልሆኑ ያውቃሉ፡ ስለዚህም ለአንተ አደራ ለመስጠት፡ ትንሿን ቤተሰባቸውን አምጥተዋል።

17 አሁንም ህጻን ማይክልን፡ ለአገልግሎት ህይወት ይበቃ ዘንድ፡ ለአንተ አደራ ሰጠሁህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። እንዲሁም፡ ህጻን ፖል ላይ እጃችንን ጭነን፡ ሕይወቱን ለኢየሱስ ክርስቶስ አሳልፈን እንሰጣለን፡ ለእግዚአብሔር ክብር ለአገልግሎት ሕይወት ይሆን ዘንድ። እንዲሁም በህጻን ዴብራ፡ እጆቻችንን በእሷ ላይ ጭነን፡ አባት ሆይ፡ ለአንተ አደራ ሰጠናት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መታሰቢያ በማድረግ፡ እርሱ እጆቹን በሕጻናት ላይ ጭኖ፡ እንዲህ ብሏልና፡ “ወደ እኔ መጡ ዘንድ ተውአቸው፥ አትከልክሉአቸው።” የዚህች ትንሽ ልጅ ሕይወት በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተባረከ ይሁን።

18 አባት እና እናት ባርካቸው፡ ልጆቻቸውን በእግዚአብሔር አገልግሎት ለማየት፡ በጣም ረጅም ደስተኛ ህይወት መኖር፡ ይሁንላቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለአንተ አደራ እየሰጠናቸው፡ ለእግዚአብሔር ክብር ይህንን በረከት እንጠይቃለን። አሜን።

ተባረክ! ተባረክ! ጥሩ ቤተሰብ፡ ናችሁ። አዎ።

19 ምን... ምን እንደማስብ ታውቃላችሁ? የአሁኑ ትንንሽ ልጃገረዶች፡ ትንሽ ልጅ እያለሁ ከነበሩት ይልቅ ቆንጆ እየሆኑ ነው። አዎን፡ ወዳጄ። እንዴት ያለ ትልቅ ውብ ዓይኖች! ስሟ ምንድን ነው? [እናትየዋ፡ “ጆአና” አለች።—አርታዒ።] ጆአና። የአያት ስምህስ ደግሞ... [አባትየው፡ “ብሌር” አለ።] ብሌር፡ ጆአና ብሌር። እናንተ እዚያ ሆናችሁ የምታዩ ሆይ፡ አሻንጉሊት አይነት አይደለችምን? አዎን፡ ወዳጄ። አንቺስ እንዴት ነሽ፡ ጆአና፡ ሃ? ትንሽ አይናፋር፡ ኧ-ሃ፡ ትንሽ አይናፋር አይነት። በጣም ደስ የምትል ትንሽ ነገር።

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

20 የሰማይ አባታችን፡ ይህ የብሌር ቤተሰብ ለትዳራቸው ይህንን ሰጦታ፡ ይህች ህጻን ጆአናን አግኝቷል። እነሆ ሰይጣን በሁሉም መንገድ፡ በተለይ ደግሞ ልጃገረዶችን፡ የሚያጠቃበት፡ ቀኖቹ ክፋዎች እንደሆኑ እናውቃለን። እንዲሁም እሷን በትክክል ለ—ለማሳደግ በቂ እንዳልሆኑ ያውቃሉ። በትክክል አድጋ፡ ለአንተም አገልጋይ እንድትሆንልህ ይ—ይፈልጋሉ። እነሆ አንተን ለማክበር ይህችን ህጻን ልጅ ያሳድጋሉ። አሁንም አደራ ለመሰጠት፡ ወደ አንተ፡ አምጥተዋታል። በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ ትንሿን ጆአና ብሌርን ለእግዚአብሔር መንግሥት ሰንሰጥ፡ ለእግዚአብሔር ክብር፡ እጆቻችንን በእሷ ላይ እንጭናለን። አሜን።

ተባረክ፡ ወንድም ብሌር። ጌታ ከአንተ ጋር ይሁን።

21 እንደምን አደር፡ ጌታዬ! [አባትየው፡ "ደና አደርክ!" አለ—አርታዒ።] እንዴት ያለ መልከ መልካም ልጅ ነው! ሄይ፡ እንዴት ነህ? ኦህ፡ ማይ፡ **በዚህ** በኩል ዞር ብትል ይበልጥ ታምራለህ። አዎ፡ ጌታዬ። ደስ የሚል ራስ፡ ደግሞም፡ የሚስማማው ፊት፡ አለው። ሃ? ሰሙ ማን ነው? ["ዳንኤል ማርክ።"] ዳንኤል ማርክ። የመጨረሻ ሰሙስ? ["ማርክ ካርደም።"] ሃርደም። ["ካርደም።"] ካርደም፡ ዳንኤል ማርክ ካርደም።

22 የዚህ አካባቢ ነህ፡ ወንድም ካርደም? [ወንድም ካርደምም፡ "እንግዲህ፡ ከመልከሪክ ከተማ" አለ።—አርታዒ።] አዎ፡ ጌታዬ። ከየት አገር ነህ? ["በዋናነት ከኒው ዮርክ ነኝ።"] ኒው ዮርክ፡ ያንኪ፡ ልክ ነው። ["አዎ።"] አዎ፡ ደስ የሚል ክፍለ ሀገር ነው። እዚያ የሚኖሩ ዘመዶች አሉኝ። አጎቴ ፕላትሰበርግ ነው የሚኖረው። ኦህ፡ ኒው ዮርክ ውስጥ ብዙ አስደሳች ጊዜያት ነበሩኝ። ቀጣዩ አገልግሎቴ፡ እዚያው ኒው ዮርክ ሲቲ፡ ዘ ሰቶን ቸርች ውስጥ ይሆናል። መልካም ነው።

23 አሁን፡ ሰሙ፡ ማርክ ነው አልከኝ? [አባትየው፡ "ዳንኤል ማርክ።"—አርታዒ።] ዳንኤል ማርክ፡ እንዴት ያለ ውብ ልጅ ነው!

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

24 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ትንሹን ዳንኤል ማርክን፡ ሕይወቱን አደራ ለመሰጠት ወደ አንተ እናመጣዋለን። ይህንን ትንሽ ልጅ በእግዚአብሔር ምክርና ተግሣጽ እንዲያሳድጉ፡ በአባትና እናቱ እጅ ተሰጥቷል። ብቃት እንደሌላቸው ሰለሚያውቁ፡ ጌታ ሆይ፡ ሕይወቱን እንድትባርክለት፡ ወደ አንተ እያመጡት ነው። አሁንም፡ የምንኖርበት ዘመን፡ ክፉ መሆኑን፡ ሰለምናውቅ። እነዚህን ትንንሽ ልጆች ሰናይ፡ ነገ ምን እንደሚመጣ አናውቅም፡ ሆኖም፡ ሁኔታው ምንም ይሁን ምን፡ በአንተ እጅ አደራ እንሰጣቸዋለን። እጆችንን በዚህ ትንሽ ልጅ ላይ እንጭናለን፡ በኢየሱስ ሰም፡ ሕይወቱ ለእግዚአብሔር መንግሥት፡ አገልግሎት እንዲለይ ለአንተ አደራ እንሰጥሃለን። አሜን።

25 እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። ውብ ልጅ ነው። ተባረክ፡ ህጻን ማርክ።

ኦህ... አስገቧቸው፡ አስገቧቸው፡
ከኃጢአት መስክ አስገቧቸው፥
ኦህ፡ አስገቧቸው፡ አስገቧቸው፡
ትንንሾቹን ወደ ኢየሱስ አምጧቸው።

በጣም ጥሩ! አመሰግናለሁ፡ እህቴ።

26 ባለፈው እሁድ እዚህ የነበራችሁ፡ ባለፈው እሁድ ጸሎት ተደርጎላችሁ፡ ውጤቱን ያያችሁና መፈወሳችሁን የሚሰማችሁ ስንቶቻችሁ ናችሁ? ጸሎት የተደረገላችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ። ኦህ፡ ማይ፡ እዚህ ጋር ተመልከቱ፡ ሁሉም ለማለት ይቻላል።

27 [ወንድም ኔቪል፡ "ሃሌሉያ! አይደንቅም ወይ! እግዚአብሔር ይመስገን! ሳምንቱን ሙሉ፡ ስለ እርሱ እየሰማሁ ነበር አለ።—እርታዒ።] አዎ፡ ወዳጄ። እኔም፡ እንደዚሁ። እኔም እንዲሁ ተቀምጬ፡ መስማት እፈልጋለሁ፡ እያችሁ።

28 እያችሁ፡ አንድ ነገር እየተከናወነ ነው፡ ስለ እርሱ በኋላ ላይ፡ በሌላ ጊዜ እነግራችኋለሁ፡ እያችሁ፡ ነገሩ ክብር የሞላበትና ድንቅ—ነው። እናም እ... በሌላ ስብሰባ ላይ፡ ታውቃላችሁ፡ በሌላ ጊዜ፡ ስለ እርሱ እንነጋገራለን። አሁን መከናወን ጀምሯል፡ ለዚህም ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው።

29 እናም በየዓመቱ እንደማደርገው፡ ወደ ኬንታኪ፡ ሄጄ ነበር። እዚያ ከአንዳንድ ጓደኞቼ ጋር ነበርኩ። እናም ሙሉ በሙሉ ሽኮኮ ለማደን ብቻ አይደለም፡ ያንን እናንተም ታውቃላችሁ፡ እያችሁ።

30 ስለዚህ እኛ ክብር የሞላበት ጊዜ እያሳለፍን ነው፡ ለጌታም ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው!

31 አሁንም መሄድ ይኖርብኛል፡ ከዚህ ስብሰባ በኋላ ወደ ቤት መሄድ ይኖርብኛል። ከዚያም፡ እኛ'ማ... ከዚያም ለስብሰባው ወደ ኒው ዮርክ ከመሄዴ በፊት፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ በድጋሚ በዚህ በኩል አልፋለሁ። እናም እዚህ የምንቆምበትን ጥቂት ፋታ ካገኘን፡ ታዲያስ፡ እዚህ ተበርናክል ውስጥ ሌላ ጉባኤ ቢኖረን ደ—ደስታችን ነው።

32 ከዚያም መመለስ ይኖርብኛል፡ ወደ ሽሬቭፖርት እሄዳለሁ። ከዚያም ወደ ቤት እንመለሳለን፡ እናም ጌታ ቢፈቅድ፡ በበዓላት ሰሞን እዚህ ለመሆን አስባለሁ፡ ቤተሰቦቼንም ይዤ እመለሳለሁ። ከዚያም—ከዚያም የምፈልገው...

33 ከዚያም በጥር ወር፡ የፊኒክስ ስብሰባዬ ይመጣል። እዚያ በክርስቲያን ቢዝነስ ሜን የሚደረግ ዓመታዊ ስብሰባ ነው። እናም ከዚያ አንድ ሳምንት ወይም አሥር ቀናት ቀደም ብሎ፡ ያንን ትልቅ—ለመከራየት እሞክራለሁ... የጂሰስ ኔም ሰዎች፥ ወንድም ጋርሲያ ይገለገልበት የነበረው፡ እናም—እናም ያ ስፓኒሽ ወንድም እዚያ ድንቅና፡ ትልቅ ቦታ ነበረው። ገና አሁን ነው የገነቡት። ብዙ ሺህ ሰዎችን ያስተናግዳል፡ አዲስ ነው፡ እናም የእነርሱ ጉባኤ በጣም ትንሽ ነው። በፈለግሁት ጊዜ መከራየት እንደምችል ነግረውኛል። ዝም ብሎ በ—በሽለቆው ዙሪያ፡ ከቤተክርስቲያን ወደ ቤተክርስቲያን፡ እንደ ትዕይንት ሁሉንም አዳርሶ ከመዞር ይልቅ፡ ሁሉንም በአንድ ትልቅ የህብረት ስብሰባ ላይ የማተኩረው ይመስለኛል፡ እያችሁ፡ ከዚያም እዚያ አደርገዋለው።

34 እናም ቤተመቅደሱን መከራየት እንችላለን። አሁን መከራየት የምንችል መሆኑን ለማረጋገጥ እንሄዳለን፡ እናም የክርስቲያን ቢዝነስ ሜን ኮንቬንሽን ይኖረናል። ከዚያም፡ የባህር ማዶው ሁኔታ እልባት ያገኘ እስኪሆን ድረስ፡ ለጥር ለየካቲት እና ለመጋቢት፡ በደቡብ በኩል፡ በደቡባዊ ክፍለ ሀገራት፡ አገልግሎት

ለማድረግ፡ እንሞክራለን። ከዚያም—ከዚያም መሄድ... ምክንያቱም፡ አሁን ከጀመርንና ወደ አፍሪካ ከሄድን... እያችሁ፡ ይህ የገና ወቅት፡ ለእነርሱ፡ ሐምሌ አራት ነው። እያችሁ፡ እርሱ ዝናባማና አስቸጋሪ ነ—ነው፡ እናም በዚያ ጊዜ እዚያ መግባት አትችሉም፡ ስለዚህ እዚያ ለመግባት የተሻለው ጊዜ ወደፊት ነው። እናም ከዚያ ለመጀመር እንፈልጋለን፡ ከቻልን፡ በኖርዌይ፡ እናም ዓለምን ዞረን፡ ወደ አፍሪካ በመግባት፡ እዚያው እልባት እንዲያገኝ፡ ጌታ ቢፈቅድ።

35 ነገር ግን አሁን ለእኛ ጸልዩ። እናም እኛ እንወዳችኋለን፡ ያንን እናንተም ታውቃላችሁ። ስለዚህ እኛ ከምናደርገው፡ ወይም ጌታ ያደርገዋል ብለን ከምናስበው ሁሉ፡ እጅግ አብልጦ እንዲሆን እንጠብቃለን።

36 እናም ዛሬ ምሽት ታላቅ የፈውስ አገልግሎት ይኖራል ብለን እናምናለን። አምናለሁ... ዛሬ ምሽት የጌታ እራት ስላለን፡ አላበዛም ጥቂት ብቻ እናገራለሁ። እናም ወደ ሃያ ወይም ሰላሳ ደቂቃ ያህል፡ ከዚያ የጸሎት መሰመር ይኖረናል፡ እና—እናም ወዲያውኑ፡ ከዚያ በኋላ የጌታ እራት ይ—ይኖረናል። እናም ከእኛ ጋር እንድትቆዩ ግብዣችን ነው፥ ደስታችን ነው። እኛ ዝግ የ—የሆነ የጌታ እራት የለንም። ለአማኝ ሁሉ ነው፡ ለእያንዳንዱ አማኝ ነው።

37 መጽሐፍ ቅዱስን ከማንበቤ በፊት፡ ለጥቂት ደቂቃ ራሶቻችንን ዝቅ ብናደርግ ደስ ይለኛል። የእግዚአብሔር ቃል እንዲባርክልን፡ በጸሎት እንዲመራን፡ ጥሩ ጓደኛዬን ወንድም ሊ ቫይልን፡ እጠይቀዋለሁ። ወንድም ቫይል፡ ያንን ታደርግልናለህ?

[ወንድም ሊ ቨይል ጸለየ—አርታዒ።] አሜን። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ። አዎ፡ ጌታ ሆይ። አሜን።

38 አሁን በቁም ነገርና፡ በአክብሮት ወደ ቃሉ እንቀርባለን። አሁን ዛሬ ጠዋት፡ ከኦሪት ዘጸአት 12ኛው ምዕራፍ፡ ማንበብ እፈልጋለሁ፡ ከቁጥር 12 ጀምሮ፡ ቁጥር 12 እና 13ን ጨምሮ፡ ማንበብ እሻለሁ። እናም አሁን በጥንቃቄ አዳምጡ። ደግሞም ዛሬ ምሽት ከጌታ እራት በፊት፡ የኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 12ን ሙሉውን ምዕራፍ፡ እንብቡት፥ ምክንያቱም ይህ ቁጥር 11 ለጉዞው የመዘጋጀት ሁኔታና፡ ከጉዞው በፊት ስላለው የጌታ እራት የሚናገር ነው። እናም አሁን በዚህ ላይ እጅግ በአክብሮት መቅረብ እንፈልጋለን። አሁን የ12ኛው ምዕራፍ 12ኛው ቁጥር፡-

**እኔም በዚያች ሌሊት በግብፅ አገር እልፋለሁ፡ በግብፅም አገር ከሰው እስከ እንስሳ ድረስ፡ በኵርን ሁሉ እገድላለሁ፥ በግብፅም አማልክት ሁሉ ላይ እፈርድባቸዋለሁ፥ እኔ ጌታ ነኝ።**

**ደሙም ባላችሁበት** ቤቶች **ምልክት ይሆንላችኋል፥ ደሙንም ባየሁ ጊዜ፡ ከእናንተ እልፋለሁ፡ እኔም የግብፅን አገር በመታሁ ጊዜ፡ መቅሰፍቱ ለጥፋት አይመጣባችሁም።**

39 ጌታ ቅዱስ ቃሉን ይባርክ!

40 አሁን ከእዚያ ውስጥ አንድ ጭብጥ መውሰድ እፈልጋለሁ፡ እርሷም አንዲት ትንሽ፡ የአምስት-ፊደላት ቃል ናት፥ **ምልክት**። **ምልክት**። በዚህ ቃል ላይ መናገር፡ ወይም ይህን የሰንበት ትምህርት፡ **ምልክት** በሚለው ቃል ላይ ማስተማር እፈልጋለሁ። እዚህ ጋር መጽሐፍ ቅዱስ፡ "ደሙም ለእናንተ

ምልክት ይሆንላችኋል" ይላል። እኛም **ምልክት** የምትለውን ቃል መጠቀም እንፈልጋለን።

41 አሁንም ሰዓቱን ስመለከት፡ እናውቀውም፡ ጊዜው ሲደርስ፡ እንግዲህ፡ እነዚህ… እዚህ ጋር የጻፍኳቸው ብዙ፡ ብዙ ጥቅሶች አሉኝ። ስለዚህ… ለጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እንደማልቆይ እያወቅሁ። ደግሞስ ይህ አንዳንዶቻችን በህብረት የምንገናኝበት የመጨረሻ ጊዜ እንደማይሆን በምን እናውቃለን? ስለዚህ ያንኑ ያህል በአክብሮት ለመቅረብ እንሞክር። ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ። ጌታ አሁንም—ለአገልግሎቱ፡ ደስ የሚል፡ በጣም ደስ የሚል፡ ጠዋት እንደሰጠን አውቃለሁ። እናም አሁን በ—በምንነጋገርባቸው ነገሮች ሁሉ ላይ ትኩረታችንን ለማሰባሰብ እንሞክር፡ በዚህም… ጌታ እንድታውቁት የሚፈልገው አንዳች ነገር ቢኖር፡ እርሱ ይሰጣችኋል።

42 እዚህ የቆምኩት ለመታየት ብቻ አይደለም። ሌሎች የምንለብሰውን ልብስ እንዲያዩ ብለን ፈጽሞ እዚህ አልመጣንም፡ ወይም፡ እኛ—እኛ እዚህ የመጣነው ለአንድ ነገር ነው፡ ወንድማችን እንደጸለየው፡ "ቃሉን ለመስማት፡ ቃሉ ወደ እኛ እንዲመጣ እዚህ መጥተናል።" ያንን እንፈልጋለን፡ ምክንያቱም ለእኛ ትርጉም የሚኖረው ብቸኛው ነገር እርሱ ነው፡ ዘላቂ የሚሆን ነገር፡ የ—የሚረዳን ነገር እርሱ ብቻ ነው።

43 እኛም ሟች ህዝቦች ነን። የሰው ልጆች ሁሉ ወደ ዘለአለምነት እያመሩ ነው። እናም በየትኛው አቅጣጫ እንደምናመራ ለመወሰን ይህንን ያህል ጊዜ አግኝተናል። መንገዱም በፊታችን ነው፥ መምረጥ የምንፈልገውን ማንኛውንም ወገን መያዝ እንችላለን። አዳምና ሄዋንን ያስቀመጣቸው በዚህ መንገድ ነው፡ እኛንም የሚያስቀምጠን በዚህ መንገድ ነው።

44 ምንም ብናደርግ፡ ወይም በህይወታችን ውስጥ፡ ምንም ያህል፡ ስኬታማ ብንሆን፡ ያለ ክርስቶስ ሁሉንም ነገር ሙሉ በሙሉ እንዳጣን ማስታወስ ይኖርብናል። ስለዚህ እርሱ፡ በኋላ… የምንጠብቀው ሁሉ እርሱ ከሆነ፡ እርሱን ባንቀበል፡ እና—እና ባንንከባከበው እጅግ ሞኞች፡ እንሆናለን። እርሱን መቀበል ብቻ ሳይሆን፡ ከዚያ ወደሚበልጥ ነገር ትመጣላችሁ። ካገኛችሁት በኋላ፡ ወስዳችሁ በመደርደሪያ ላይ አታስቀምጡት። ስራ ላይ መዋል ይኖርበታል።

45 ልክ መድኃኒት ለመውሰድ ወደ ሐኪም እንደመሄድና፡ ከዚያም መደርደሪያ ላይ እንደማስቀመጥ ማለት ነው። መድኃኒቱን ለመውሰድ ከሄዳችሁ፡ መድኃኒቱን ውሰዱት። የሚያስቸግራችሁ በሽታ ካለ፡ እናም ይህ መፍትሔ ይረዳችኋል ተብሎ ከታሰበ፡ የሰጣችሁን ውሰዱ፥ ልክ እርሱ እንዳዘዛችሁ አድርጋችሁ ውሰዱት፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ ጥቂት ደቂቃዎች በምትወስዱበት መንገድ ላይ ትልቅ ልዩነት ያመጣሉ። እናም በምን እናውቃለን…

46 ሆኖም በዚህ ሁኔታ፡ ዛሬ፡ የአንተ የአንድ ቅጽበት ውሳኔ የዘለአለም መድረሻህን ሊወስን ይችላል። ልክ እርሱ በእጅህ ላይ እንደሚያስቀምጥልህ አድርገህ ውሰደው።

ምልክት፡ "ደሙ ለእናንተ ምልክት ይሆንላችኋል።"

47 አሁን፡ በመጀመሪያ፡ ምልክት ምንድን ነው? እኛ እንግሊዝኛ-ተናጋሪዎች ዘንድ፡ በተለይም እዚህ አሜሪካ ውስጥ በብዛት የምንጠቀምበት ቃል ነው።

ምልክት ማለት... በእርግጥ፡ መዝገበ ቃላቱ እንደሚለው ምልክት ማለት አምሳያ ነው፡ ዋጋ መከፈሉን የሚያሳይ፡ አምሳያ ነው፡ አያችሁ፥ ማለትም—ክፍያው፡ ዋጋ፡ ወይም ዋጋ መከፈሉን የሚገልጽ ነው።

48 ልክ በባቡር ወይም በአውቶብስ ላይ እንዳለ የታሪፍ ዋጋ ማለት ነው። ትሄዳለህና የታሪፍ—ዋጋህን ትገዛለህ፡ ከዚያም ምልክት ይሰጡሃል፡ ያም ምልክት ለዚያ ባቡር መስመር እንጂ ለሌላ ለማንኛውም ነገር ሊውል አይችልም። እናም ይህ ለባቡሩ ኩባንያ፡ የታሪፍ ዋጋህን መክፈልህን የሚያሳይ፡ ምልክት ነው። እርሱ ምልክት ነው፡ ለሌላ ለማንኛውም ነገር ልታውለው አትችልም። በሌላ በማንኛውም መስመር ላይ አይሰራም። በዚያ መስመር ላይ ብቻ ነው የሚሰራው። እናም ይህ—ይህ ምልክት ነው።

49 አሁን እዚህ ጋር፡ እየተናገርንበት ባለው ጉዳይ፡ የምንጀምርበት ቦታ፡ እግዚአብሔር ለእስራኤል እንዲህ እያለ ነው፡ “የበጉ ደም ለእናንተ ምልክት ነው።” የታረደው፡ የእስራኤል በግ፡ ያሕዌ የሚጠይቀው ምልክት ነበረ። ደሙ መሆን ይኖርበታል። እግዚአብሔር ምልክት አደረገ ለእስራኤልም ሰጠው። ሌላው ምልክት አይሠራም፡ አያችሁ፡ ተቀባይነት አይኖረውም።

50 ለዓለም፡ ይህ የሞኻነት ክምር ነው። ነገር ግን፡ ለእግዚአብሔር፡ ይህ ብቸኛው መንገድ ነው። እርሱ የሚፈልገው ብቸኛው ነገር ያ ምልክት ነው። የግድ መኖር አለበት። እናም ዋጋው እስካልተከፈለ ድረስ ምልክቱን ልታገኝ አትችልም፡ ከዚያም በነጻ የማለፊያ ፈቃድ የሚሰጥህን ምልክት—ባለቤት ትሆናለህ። “ደሙን አያለሁ፡ አልፋችኋለሁ።” በውስጥህ፡ ማለፊያውን ይዘህ መጓዝህን፡ ስታውቅ፡ ይህ፡ ምንኛ ታላቅ ጊዜ፡ ምንኛስ ታላቅ መታደል ነው። “ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።” እሱ የሚያውቀው ብቸኛው ነገር ይህ ነው። ሰፍራውን ሊተካ የሚችል ምንም ነገር የለም፥ እሱን የሚተካ የለም፡ የሃይማኖት ተቋም የለም፡ ሌላ ምንም ነገር የለም። ያንን ይጠይቃል ። እግዚአብሔርም፡ “ያንን ብቻ ነው የማየው” አለ።

51 የቱንም ያህል ጻድቃን ቢሆኑ፡ ምንም ያህል ደጎች ቢሆኑ፡ ምን ያህል ትምህርት ቢኖራቸውም፡ አለባበሳቸው ምንም ይሁን ምን፡ ምልክቱ ብቸኛው ነገር ነበረ። “ምልክቱን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።” ደሙ ይሖዋ የሚጠይቀው ነገር መሟላቱን፡ መደረጉን የሚያሳይ ምልክት ነበረ። ደሙ ምልክት ሆኖ ቆመ። ደሙ ምልክት ነበር። አያችሁ? ህይወቱ...

52 እግዚአብሔር እንዲህ ብሎ ነበር፡ “ከእርሱ በበላህ ቀን፡ በዚያ ቀን ሞትን ትሞታለህ።” እናም በአማኙ ሕይወት ፋንታ የሚወሰድ ተለዋጭ ሕይወት ነበረ። እግዚአብሔር፡ በምሕረቱ፡ በኃጢአት በረከሰ ሰው ሕይወት ፋንታ ምትክን ተቀበለ። ልጁ በቃሉ ባለማመን፡ ራሱን በኃጢአት ባረከሰ ጊዜ፡ ያን ጊዜ እግዚአብሔር፡ በምሕረት ባለጸጋ ስለሆነ፡ ምትክን አደረገ፥ ይህም፡ በእርሱ ፋንታ፡ አንድ ነገር መሞት ነበረበት። ሌላ ምንም ሊሰራ አይችልም ነበር።

53 የቃየን ፖም እና ኮክ፡ እና የመሳሰሉት ያልሰሩት፡ ለዚህ ነው። ደም ያለበት ሕይወት መሆን ነበረበት፡ ሕይወቱም ከመሥዋዕቱ ወጥቶ ነበር፡ አሁንም ደሙ የእግዚአብሔር ትዕዛዝ መፈጸሙን የሚያሳይ ምልክት ነበረ። አሁን፡ እግዚአብሔር ምን ጠየቀ? ሕይወትን፥ ደሙም ሕይወት መጥፋቱን አሳየ። ስለዚህ ደሙ ሕይወት እንደተሰጠ፡ በእርሱ ፋንታ አንድ ነገር እንደሞተ፡

የእግዚአብሔር ጥያቄ መሟላቱን የሚያሳይ ምልክት ነበረ፥ ማለትም ሕይወት እንደተሰጠ፡ ደምም እንደፈሰሰ። ደሙም ሕይወት እንዳለፈ፡ የሚያሳይ ምልክት ሆኖ ቆመ። እግዚአብሔር እንዲያልፍ የተናገረው የእንስሳው ሕይወት፡ ደሙ ምልክት ሆኖ የቆመለት ነበረ። አያችሁ?

54 አ—አ—አማኙ የሆነው መሰዋዕት አቅራቢው፡ በምልክቱ ምክንያት ከመሰዋዕቱ ጋር ይታወቃል። በእነዚህ ትናንሽ ጥቅሶች ላይ ብዙ መቆየት አልፈልግም፡ ሆኖም፡ መልእክቱን በሙሉ በአንደኛው ላይ ልትወስዱ ትችላላችሁ፡ ነገር ግን ያንን ለመግለጽ እዚህ ጋር ለጥቂት ጊዜ መቆም እፈልጋለሁ። አ—አ—አማኙ ከመሥዋዕቱ ጋር መታወቅ አለበት። አያችሁ? መሥዋዕቱ እንዲሁ ዝም ብሎ የሆነ ቦታ የቀረበ—መሥዋዕት ብቻ ቢሆን ኖሮ፡ ፋይዳ አይኖረውም ነበር፥ ነገር ግን ከመሥዋዕቱ ጋር አብሮ መቆጠር ነበረበት። በግልጽ ለመናገር፡ እራሱ ከመሰዋዕቱ ጋር መቆጠር እንዲችል፡ በመጀመሪያ፡ እጆቹን በእርሱ ላይ መጫን ይኖርበታል። ደሙም የሚቀባው እርሱ በደሙ ጥላ ሥር መቆም በሚችልበት ነበረ። ደሙ በላዩ ላይ ሊሆን ይገባ ነበርና። ይህም እርሱ ራሱን፡ እንደ በደለኛ መቆጠሩን የሚያሳይ ምልክት ነበረ፡ ደግሞም ንጹሕ ምትክ በእርሱ ፋንታ ቦታውን እንደያዘ ማረጋገጫ ነበረ።

55 ምንኛ ውብ ምስል ነው! ኦህ፡ የተዋጀ! አያችሁ፡ ፍርድ ተሟልቷል፡ የእግዚአብሔር ቅዱስ ፍርድ ጥያቄ ተሟልቷል። እናም እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ "አሁን ሕይወትህን እፈልጋለሁ፡" እናም መቼ፡ ሕ—ሕ—ሕይወቱ ኃጢአት በሠራች ጊዜ። ከዚያም ንጹሕ ምትክ ሰፍራውን ተካ። እርሱም ደም ያለው እንስሳ ነበረ፥ ፖም፡ ወይም ኮክ አይደለም። ይህም ይህ ደም እንደነበረ፡ የእባቡን ዘር ለሁሉም ሰው በጣም ግልጽ ሊሆንለት ይገባል። ይህ ደምም፡ ከፍራፍሬ ሊወጣ የማይችል፡ ከንጹሕ ምትክ የወጣ ነው። ሕ—ሕይወትም፡ በእርሱ ፋንታ፡ ወጥታ ነበር፡ ደሙም እንስሳው እንደሞተና ደሙ እንደወጣ የሚያሳይ ምልክት ነበረ።

56 እናም መሰዋዕት አቅራቢው ደሙን በላዩ ላይ በማድረጉ፡ በቤዛነቱ ውስጥ መቆጠሩን አሳይቷል፡ ምክንያቱም… በመሥዋዕቱ ላይ ራሱን ስለቆጠረ፡ ከመሥዋዕቱ ጋር ራሱን ስላገናኘ፡ ደሙም ምልክት ሆኖ ቆሟል።

57 እንዴት—እንዴት ያለ ድንቅ ነገር ነው! እንዴት ያለ ምስል ነው! ይህ ፍጹም የክርስቶስ ምሳሌ ነው፡ ልክ እንደዚሁ፡ ዛሬ ባፈሰሰው ደም ሥር የቆመው አማኝ፡ ከመሥዋዕቱ ጋር ይቆጠራል። ልክ ፍጹም እ—እንደሆነው ሁሉ፡ ከዚያ ከክርስቶስ፡ እንስሳ እ—እንዳልሆነ… አያችሁ፡ እ—እንስሳው ሞቷል፡ ነገር ግን እርሱ…

58 ካለን ነገር ሁሉ እጅግ ንጹሕ የሆነው፡ እ—እንስሳው፡ ብዬ የማስበው፡ እንግዲህ፡ የበግ—ጠቦት ሳይሆን አይቀርም። እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስን ማስተዋወቅ በፈለገ ጊዜ፡ እንደ በግ አስተዋወቀው። ራሱንም ማስተዋወቅ በፈለገ ጊዜ፡ እንደ ወፍ፡ እንደ ርግብ አስተዋወቀ። ርግብ ከወፎች ሁሉ እጅግ ንጹሕና የጠራች ናት፡ ጠቦት—ደግሞ ከእንስሳት ሁሉ እጅግ ንጹሕና ገር ነው። ስለዚህ ስታዩት…

59 ኢየሱስ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ፡ እንደ ርግብ ሲወርድበትና፡ በእርሱ ላይ ሲያርፍ—

አየ።” ስለዚህ እንዲህ ቢሆን ኖሮ… ተኩላ ቢሆን፡ ወይም ሌላ እንስሳ ቢሆን ኖሮ፡ የርግቧ ባ—ባሕርይ ከተኩላው ባሕርይ ጋር ሊዋሃድ አይችልም ነበር፡ እንዲሁም የርግቧ ብሳ—ባሕርይ ከጠቦቱ በቀር ከሌላ ከማንኛውም እንስሳ ባሕርይ ጋር ሊዋሃድ አይችልም ነበር። እነዚያም ሁለት ባሕርያት አንድ ላይ መጡ፡ ከዚያም አንዳቸው ከሌላው ጋር መስማማት ቻሉ።

60 አሁን አስቀድሞ መወሰንን አያችሁት? እዚያ ሲመጣ ጠቦት ነበረ። አያችሁ? አያችሁ? እ… ሲመጣ—ጠቦት ነበረ። ጠቦት ነበረ። ጠቦት ሆኖ ተወለደ። ጠቦት ሆኖ፡ አደገ። አያችሁ?

61 እናም፡ ስለዚህ፡ ያ ቃሉን ሊቀበል የሚችል፡ ክርስቶስን ሊቀበል የሚችል ብቸኛው እውነተኛ መንፈስ አይነት ይህ ነው። የተቀሩት ይሞክራሉ፡ ለማግኘት ሞክረዋል፡ እናም የእግዚአብሔርን መንፈስ በተኩላ ላይ ያደርጋሉ፡ አያችሁ፡ ቁጡዎች፡ ህመምተኞች፡ ክፉዎች ናቸው። እዚያ አይቆይም። መንፈስ ቅዱስ ወድያው ይበርራል። አያደርገውም።

62 ያች ርግብ ብትወርድና፡ እናም፡ ጠቦት ላይ ከመሆን ይልቅ፡ ሌላ እንስሳ ብትሆን ኖሮ ምን ሊሆን ይችል ነበር? ወድያው ይበራል እናም ይመለሳል። አያችሁ? ከራሱ ሊዋሃድ የሚችለውን ተፈጥሮ ሲያገኝ ግን፡ አንድ ይሆናል።

63 ከዚያም እርግቧ—እርግቧ—እርግቧ በጉን መራችው፡ እናም፡ እስተውሉ፡ በጉን ወደ መታረድ መራችው። አሁን፡ በጉ ለእርግቧ ታዛዥ ነበር። አያችሁ? ወዴትም ብትመራው፡ ለመሄድ ፈቃደኛ ነበር።

64 ግርም የሚለኝ፡ ዛሬ፡ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ወደ—መገዛትና እርሱን ወደማገልገል ህይወት ሲመራን፡ መንፈሳችን አንዳንዴ፡ ያንን ነገር እያሳየ እያመፀ፡ ለመሆኑ እኛ የበግ ጠቦት ነን ወይ ብዬ እገረማለሁ? አያችሁ? አያችሁ? ጠቦት ታዛዥ ነው።

65 ጠቦት ራሱን-መስዋዕት የሚያደርግ ነው። የ—የራሱ የሆነውን እ—እርሱ አይወስድም፡ አያነሳም። ወዲያውኑ ታስተኛዋለህ ሱፉንም ትላጨዋለህ። ያ ያለው ብቸኛው ነገር ነው። ስለ እርሱ ምንም—ምንም አይናገርም፥ ያለውን ሁሉ መስዋዕት ያደርጋል። ያ በግ ነው። ሁሉን ነገር አሳልፎ ይሰጣል… ሁሉን ነገር አሳልፎ ይሰጣል፡ ራሱንና የሆነውን ሁሉ።

66 እውነተኛ ክርስቲያንም እንዲህ ነው፡ ራሳቸውን… ራሳቸውን-መስዋዕት የሚያደርጉ ከሆኑ፡ ስለዚሁ ዓለም ምንም አይጨነቁም፡ ዳሩ ግን ያላቸውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ይሰጣሉ። አያችሁ?

67 አሁንም ክርስቶስ፡ ያ ፍጹም ጠቦት ነበር። በዚህ ጠቦት መታረድ በኩል፡ በግብፅ በነበረው ተፈጥሯዊው ጠቦት፡ ደሙ ተቀባ፡ እና፡ ያ ሲሆን፡ ለምልክት ተቆጠረ፡ ታዲያ የዚህ ጠቦት ደም ለምን ይቆጠራል? አያችሁ? ምልክቱ እኛ ለራሳችን እንደሞትንና ከመስዋዕታችን ጋር እንደታወቅን ነው። አያችሁ? ከዚያም፡ ጠቦቱ እና—እና—ደሙ እና ግለሰቡ አብረው ይቆጠራሉ፡ መስዋዕቱ እና አማኙ። አያችሁ፡ በህይወታችሁ ውስጥ የምትታወቁት፡ በመስዋዕታችሁ ነው። ማንነታችሁን የሚያደርገው ያ ነው።

68 ስለዚህ ደሙ ምልክት፡ ወይም መታወቂያ ነበር። ደሙ መስዋዕት አቅራቢውን ጠቦቱን እንዳረደው፡ ጠቦቱንም እንደተቀበለ፡ እና ምልክቱንም

በራሱ ላይ እንዳደረገ፡ እንዳላፈረበትም ጭምር ያሰቆጥረዋል። ማን አየኝ ብሎ አልተጨነቀም። ሁሉም ሰው እንዲያየው ፈለገ፡ እናም አላፊ አግዳሚው ሁሉ ያንን ምልክት ሊያየው በሚችልበት ሰፍራ ላይ ተደረገ።

69 አያችሁ፡ ብዙ ሰዎች ክርስትያን መሆን ይፈልጋሉ፡ ሆኖም ማንም—ማንም—ክርስቲያን መሆናቸውን እንዳያውቅባቸው በድብቅ ሊያደርጉት—ይወዳሉ። ወይም፡ አብረዋቸው ሰለሚውሉ—ሰለሚውሉ ጓደኞቻቸው፡ አንዳንዶቹ እንዲህ ብለው ያሰባሉ፡ "እንግዲህ፡ አሁን፡ ተመልከት፡ እ—እኔ—ክርስቲያን መሆን እፈልጋለሁ፡ ቢሆንም **እገሌ-እና-እገሊት** ይህንን እንዲያውቅብኝ አልፈልግም።" አያችሁ? መልካም፡ አሁን፡ አያችሁ፡ ያ ክርስትና አይደለም።

70 ክርስትና ምልክቱን ማሳየት አለበት፡ አያችሁ፡ በአደባባይ፡ በማህበራዊ ህይወት ውሰጥ፡ በሰራ ቦታ፡ በመንገድ ላይ፡ ችግር ሲያጋጥም፡ በማንኛውም ነገር፡ በቤተክርስቲያን፡ እና በየትኛውም ሰፍራ። ደሙ ምልክት ነው፡ ምልክቱ መቀባት አለበት፡ አያችሁ፡ ወይም (አይደለም) ቃል ኪዳኑ ጥቅም ላይ አይደለም።

71 ደሙ ይህ ሰው እንደተቤዠ የሚያሰቆጥር፡ ምልክት፡ ወይም መታወቂያ ነበር። አሁንም፡ እንግዲህ፡ አሰተውሉ፡ አንዳች ነገር ከመፈጸሙ በፊት፡ አሰቀድመው ተዋጅተዋል። በእምነት ደሙን ቀቡት። አያችሁ፡ ከመፈጸሙ በፊት፡ እንደሚፈጸም በማመን፡ ደሙ በእምነት ቀባ። አያችሁ? የእግዚአብሔር ቁጣ በምድሪቱ ላይ ከማለፉ በፊት፡ አሰቀድሞ፡ ደሙ መቀባት ነበረበት። ቁጣው ከወደቀ በኋላ እጅግ ረፍዷል።

72 አሁንም ለአፍታ ያህል፡ ምናልባት ወደ ሃሳባችሁ ልናመጣው የምንችለው፡ ከዚያ የምናነሣው ትምህርት አለን። ይኸውላችሁ፡ ከመፈጸሙ **በፊት**፡ ምክንያቱም ምንም ዓይነት ደም ልትቀቡ የማትችሉበት ጊዜ ይመጣልና።

73 ጠቦቱ የታረደው ለአሰራ አራት ቀናት ከተጠበቀ በኋላ፡ ሲመሽ ነበር። ከዚያም ሲመሽ ጠቦቱ ታረደ ደሙም ተቀባ። ገባችሁ? እሰኪመሽ ድረሰ ምልክቱ ከቶ ወደ ህልውና አልመጣም።

74 ይህም የምንኖርበት ዘመን ምሽት ነው። ይህ ለ—ለቤተክርሰቲያን የምሽት ጊዜ ነው። ይህ ለእኔ የምሽቱ ዘመን ነው። ይህ ለመልእክቴ የምሽቱ ዘመን ነው። እየሞትኩ ነው። እየሄድኩ ነው። በወንጌል የምሽት ዘመን፡ እየወጣሁ ነው። በጽድቅና፡ በሌሎች አልፈን መጥተናል፡ ዳሩ ግን ምልክቱ መቀባት ያለበት ጊዜ ይህ ነው። ባለፈው እሁድ ላናግራችሁ የምፈልገው አንዳች ነገር እንዳለኝ ነግሬያችሁ ነበር፥ ያም ይሄው ነው። ልትቀልዱበት—የማትችሉበት ዘመን። መደረግ አለበት። መቼም መደረግ ካለበት፡ አሁን መደረግ አለበት። ምክንያቱም፡ ቁጣው በምድሪቱ ላይ ለማለፍ መዘጋጀቱን ማየት እንችላለን፡ ከዛ ምልክት ሰር ያልሆነው ሁሉ ይጠፋል። ደሙ፡ ያውቃችኋል። አሰተውሉ።

75 ምክንያቱም፡ የእንሰሳው ህይወት በሰው ልጅ ላይ ተመልሶ ሊመጣ አይችልምና። ደሙ ሲፈሰ፡ በእርግጥ፡ ህይወቱ ወጣ፡ ምክንያቱም አንድ አካል ነበረና። የህይወት ደም ከእርሱ በሄደ ጊዜ፡ ህይወት ከደሙ የተለየ ሰለሆነ… አሁን፡ ደሙ የዚያ ሕይወት ኬሚሰትሪ ነው፡ ሕይወት ግን ከደሙ የተለየ

ነው፡ ነገር ግን ሕይወት በደሙ **ውስጥ** ነው። ስለዚህ የእንስሳው ህይወት በመሰዋዕት አቅራቢው ላይ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም። የዚህን ጠቦት ደም ባፈሰሰ ጊዜ፡ ኬሚስትሪውን መቀባት ነበረበት፡ ምክንያቱም ህይወቱ—ህይወቱ ወጥቶ ነበርና ተመልሶ ሊመጣም ስለማይችል።

76 ምክንያቱም፡ በእሰው ልጅ ላይ ሊመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም የእንስሳው ህይወት ነፍስ የለውም። እንስሳው ራቁቱን መሆኑን አያውቅም፡ እንደውም—እንችሁ… ኃጢአትን አይገነዘብም። ምንም አያውቅም፡ ስለዚህም ህያው ፍጡር ነው እንጂ ህያው ነፍስ አይደለም። ስለዚህ፡ ያ የእንስሳ ህይወት በሰው ህይወት ላይ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም በዚያ ህይወት ውስጥ ነፍስ የለውምና። አሁን፡ ህይወት፡ ደም አለ፥ ህይወት፡ እና በህይወት ውስጥ ነፍስ፥ ነፍስ የህይወት ተፈጥሮ ናት። ስለዚህ፡ የተወሰነ ዓይነት ተፈጥሮ አልነበረውም፡ እንስሳ ነበር፡ ስለዚህ ደሙ ሕይወት ለተሰጠው ምልክት ቆሞ ነበር።

77 ነገር ግን በዚህ በከበረው ስፍራ፡ በዚህ ቃል ኪዳን ስር፡ በደም እና በሕይወት መካከል ልዩነት አለ። ዛሬ ለአማኙ ምልክት መንፈስ ቅዱስ ነው፥ ደም ሳይሆን፡ ኬሚስትሪው ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ዛሬ ከቤተክርስቲያንን የሚጠይቀው ምልክት ይህ ነው። እግዚአብሔር ይህን ምልክት ማየት አለበት። በእያንዳንዳችን ውስጥ ሊያየው ይገባል።

78 ስለዚህ፡ የምሽቱ ጥላ እየታየ ሲመጣ፡ ቁጣውም ኃጢአተኛ በሆኑ ሕዝቦች ላይ፡ እና ኃጢአተኛ በሆኑት የማያምኑት ላይ፡ በእነዚህ ነገሮች ላይ፡ የያዙት ነገር ሳይኖራቸው—አለን በሚሉት ላይ፡ ከላይ ሊፈስ ተዘጋጅቷል! ደግሞም—እነዚህን ነገሮች ከመናገሬ በፊት፡ የት እንደቆመ ለማየት ራሴን ገልጬ፡ በእርሱ መካከል በትክክል ለመኖር ሞክሬአለሁ። አሁንም በጥላዎች ውስጥ እየኖርን ነው፡ ቁጣውም ለመምታት ተዘጋጅቷል፡ እግዚአብሔርም እናንተ ራሳችሁ ምልክቱን፡ መንፈስ ቅዱስን እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ ምልክት ይፈልጋል። እርሱ ብቸኛው መንገድ ነው፡ እግዚአብሔርም የሚያልፈው ብቸኛው ምልክት ነው፡ ምክንያቱም እርሱ ወደ አማኙ የተመለሰው ቃል በቃል የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት ራሱ ነውና።

79 የእንስሳው ህይወት ተመልሶ ሊመጣ አይችልም፡ ስለዚህም ደም በበሩ ላይ፡ እና በጉበኑ እና በበሩ መቃን ላይ መቀባት ነበረባቸው፥ ይህም አላፊ አግዳሚው ሁሉ፡ ህዝቡ በሙሉ፡ በቤቱ አጠገብ የሚያልፍ ሁሉ፡ በዚያ በር ላይ፡ የ—የደም ምልክት እንዳለ፡ በዚያ በር ላይ ህይወት እንደሞተ ያውቁ ዘንድ ነው። አሜን!

80 በመንፈስ ቅዱስ ለተሞላ እያንዳንዱ አማኝ፡ ዛሬም እንደዚያው መሆን አለበት፥ የፈሰሰው የጠቦቱ ደም፡ በጠቦቱ ውስጥ የነበረው ያ ህይወት፡ ተመልሶ እንደመጣና በዚያም በአደባባይ እንደታተመ የሚያሳይ ምልክት፡ አላፊ አግዳሚው ሁሉ፡ የሚያናግራችሁ፡ ከእናንተ ጋር ግንኙነት ያለው ማንኛውም ሰው፡ ደሙ እንደተቀባ፡ እና በዚያ ደም ውስጥ የነበረው የህይወት ምልክት በእናንተ ላይ እንዳለ ያያል። ከቁጣው የተጠበቃችሁ ናችሁ። ያ ብቻ፥ አባል በመሆን አይደለም። አይ፡ ወዳጄ!

81 የእንሰሳት ህይወት በአማኙ ላይ ሊመጣ አይችልም፡ ምክንያቱም እንሰሳ ነበረና፡ እንዲሁም ፍጹም የሆነ መሰዋዕት እንደሚመጣ በማሳየት፡ ስለ ህሊና ብቻ የሚናገር ነበር።

82 ታዲያ፡ አሁንስ፡ እግዚአብሔር ራሱ ማስተሰሪያ ከመሆኑ፡ ከራሱ የበለጠ ፍጹም የሆነ መሰዋዕት እንዴት ሊኖር ይችላል? እግዚአብሔር በራሱ ፈጣሪ በሆነው ደም ውስጥ፡ ስጋ በሆነ ጊዜ፡ ያ... የእግዚአብሔር ህይወት መቼም ቢሆን ተመልሶ ሊመጣ የሚችልበት ብቸኛው መንገድ ያ ነበር።

83 ምክንያቱም፡ ሁላችንም በግብረ ስጋ ግንኙነት ተወልደናል፡ ስለዚህም በዚያ ውስጥ ያለው ህይወት የዓለም ነው፡ ያም ህይወት አይጸናም። አስቀድሞ የተፈረደበትና የተኮነነ ነገር ነው። ልትጠግኑት አትችሉም። የሚጠገንበት ምንም መንገድ የለም። ልታለስልሱት የምትችሉበት—ምንም መንገድ የለም። የተሻለ ልታደርጉት የምትችሉበት መንገድ የለም። መሞት አለበት! የሚጠበቅበት ብቸኛው መስፈርት ያ ነው። መሞት አለበት።

84 ምትኩም፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወት፡ ወደ እናንተ ሊመጣ ይገባዋል፡ እርሱም የእግዚአብሔር ምልክት የሆነው፡ መንፈስ ቅዱስ ነው፥ ይህም የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም፡ እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ ነው።

85 ስለዚህ፡ በዌስሊ ዘመን ወይም... በሉተር ዘመን፡ "ማመን፡" ተብሎ ይታሰብ ነበር። በዌስሊ ዘመንም፡ "የደሙ ኬሚስትሪ"። ዳሩ ግን ይህ—ይህ ምልክት የሚፈለግበት፡ የመጨረሻው ዘመን ነው። ያም፡ በአንድነት፡ ለንጥቀት ሙሉውን አካል ያበጃል። አያችሁ?

86 እናት ህፃን ስትወልድ ውሃ፡ ደም፡ እና መንፈስ ይመጣሉ። መጀመሪያ የሚፈሰው፡ በተፈጥሮአዊ ውልደት፡ ውሃ ነው፡ ሁለተኛው ነገር ደም ነው፡ ቀጣዩ ነገር ደግሞ ህይወት ነው።

87 ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ አካል፥ ውሃ፡ ደም፡ እና ህይወት ወጣ። ቤተክርስቲያን በሙሉ፡ ሙሽራይቱ፡ በአንድነት፡ በመጽደቅ፡ በመቀደስ፡ እና በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኩል ተሰርታለች፡ እርሱም ምልክት ነው።

88 ዕብራውያን 11 እንደሚለው፡ "እነዚህ ሁሉ በበግና በፍየል ሌጦ የዞሩ፡ እና የተቸገሩ፡ እና ያደረጉት እነዚህ ሁሉ ነገሮች ነበሩ፡ ሆኖም ያለ እኛ ፍጹማን አልሆኑም።"

89 እናም በዚህ ዘመን ያለችው ቤተክርስቲያን፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት የተገኘውን፡ ምልክት የተቀበለች፡ ደሙ እንደፈሰሰ እና መንፈስ ቅዱስም በቤተክርስቲያን ላይ እንዳለ የሚያሳየውን፥ ያለ እኛ፡ እንግዲያው፡ ሊነሱ አይችሉም። ዳሩ ግን በእኛ ላይ ጥገኞች ናቸው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር ይህ እንዲኖር ቃል ገብቷል፡ እናም አንድ ሰው በዚያ መገኘቱ አይቀርም። ማን ሊሆን እንደሚችል አላውቅም፡ ነገር ግን አንድ ሰው ይቀበለዋል። ኃላፊነት ያለብኝ ብቸኛ ነገር፡ ያንን መስበክ ነው። ያንን አስቀድሞ የተወሰነ ዘር መፈለግ የእግዚአብሔር ስራ ነው። ዳሩ ግን፡ መምጣቱ አይቀሬ ነው። ምክንያቱም፡ እያንዳንዳቸው፡ አንዱ ከሌላው ጋር፡ ይመጣሉ፥ የውኃው ዘመን፡ የደም ዘመን፡ አሁን የመንፈስ ቅዱስ ዘመን ምልክት።

90 እና፡ አስታውሱ፡ እስራኤል በብዙ ነገሮች አልፋ መጣች፡ ዳሩ ግን ምልክቱ የተፈለገው ሲመሽ ነበር፥ በጠዋት አይደለም፡ በዝግጅቱ ጊዜ አይደለም፡ ጠቦቱ ተጠብቆ በቆየባቸው አስራ አራት ቀናት አይደለም። እስራኤልም የሆነ ነገር እንደሚመጣ አውቆ ነበር።

91 ሉተርም ያውቀዋል፡ ዌስሊም እንዲሁ አውቆታል፡ ፊኒክስ፡ ካልቪን፡ ኖክስም፡ አውቀውታል። ይኸው ነው! የእሳት ዓምድ ወደ ቤተክርስቲያን የሚመለስበት ጊዜ እንደሚመጣ ያውቁ ነበር። እነዚህ ነገሮች የሚፈጸሙበት ጊዜ እንደሚመጣ ያውቁ ነበር፡ ያዩት ዘንድ ግን በሕይወት አልኖሩም፡ ለማየት ግን በጉጉት ይጠባበቁ ነበር።

92 እስራኤል አንዳች ነገር እየመጣ እንደሆነ ታውቅ ነበር፡ ዳሩ ግን ያ የጠቦት ደም፡ ምልክቱ፡ በበሩ ላይ የተደረገው ሲመሽ ነበር። ሆኖም፡ ጠቦቱ አስቀድሞ ተዘጋጅቶ ነበር።

93 እስከ መጨረሻው ድረስ ጠቦቱ ነበር። በሉተር ዘመን ጠቦቱ ነበር፡ በዌስሊ ዘመን ጠቦቱ—ጠቦቱ ነበር፡ ዳሩ ግን አሁን እያንዳንዱ ቤት በምልክቱ መሸፈን ያለበት የምልክት ዘመን ነው። የእግዚአብሔር ቤት ሁሉ በምልክት መሸፈን አለበት። በውስጡ ያለው ሁሉ በምልክት መሸፈን አለበት። የእግዚአብሔርም ቤት የኢየሱስ ክርስቶስ አካል ናት፡ እኛም ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደዚህ ምልክት ተጠምቀናል የአካሉ ብልት ሆንን፡ እግዚአብሔርም፡ "ይህን ምልክት ሳይ፡ አልፋችኋለሁ፡" ብሏል። እንዴት ያለ ዘመን ነው የምንኖረ! ኦህ!

94 የደም መታወቂያ፡ አማኙን የሚታወቅበት፡ ምክንያቱም ህይወት አንዴ ወጥቷል፡ ተመልሶ ሊመጣ አይችልም፡ ሰለዚህም አንድ—አንድ ኬሚስትሪ ሊኖረው አስፈልጎት ነበር። እንደ ቀለም ያለ፡ ደም፡ ህይወት ከእርሱ እንደወጣ የሚያሳይ ኬሚስትሪ አስፈልጎ ነበር።

95 አሁን ያው መንፈስ ራሱ ምልክት ነው። መንፈስ ቅዱስ ራሱ፡ ምልክት ነው እንጂ፡ ደም አይደለም። ደሙ በቀራንዮ ላይ ፈሰሰ፡ እውነት ነው። ዳሩ ግን ደሙ፡ ያለ ነገር እንደመሆኑ መጠን፡ ይኖርበት ከነበረው ከምግብ፡ ወደ መጣበት ንጥረ ነገር ተመልሷል። ዳሩ ግን፡ አያችሁ፡ በዚያ የደም ሴል ውስጥ የደም ሴሉን ማንቀሳቀስ የጀመረ ህይወት ነበረ። እንዲህ ቢሆን... ኬሚስትሪው በራሱ፡ ህይወት አልነበረውም፡ ሰለዚህም መንቀሳቀስ አይችልም። ነገር ግን ህይወት ወደ ደሙ ኬሚስትሪ በመጣ ጊዜ፡ ሴልን ፈጠረ። የራሱን ሴል ፈጠረ፡ ከዚያም በሴል ላይ ሴል፡ ከዚያም ሰው ሆነ። ያም ሰው፡ በሰጋ የተገለጠው እግዚአብሔር፡ አማኑኤል ነበር። ነገር ግን ያ ህይወት ወደ ኋላ በተመለሰ ጊዜ፡ ኬሚስትሪው ወደ እርሱ ሄደ፡ ነገር ግን ምልክቱ በቤተክርስቲያን ላይ ያለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡ ይህም ክርስቶስን ያዩት ዘንድ ነው።

96 መሆንም አለበት፡ ምክንያቱም እንዲት ሴትና ባሏ አንድ ይሆናሉ። አንድ ይሆናሉ። ሙሽራይቱና ክርስቶስም እንደዚሁ አንድ ይሆናሉ። የሙሽራይቱ አገልግሎት፡ እና የክርስቶስ አገልግሎት፡ አንድ ነው። አስታውሱ፡ "ቴዎፍሎስ ሆይ፡ ኢየሱስ ሊያደርግና ሊያደርገው ሰለጀመረው ነገር፡ የመጀመሪያዎቹ ነገሮች፡ ጽፌልሃለሁ።" ሞቱ አላቆመውም። በፍጹም፡ ወዳጄ! ዳግመኛ ተመለሰ። ሶስተኛ አካል አይደለም፡ ነገር ግን ያው አካል በመንፈስ ቅዱስ

መልክ ዳግመኛ ተመለሰ፡ እናም ሰራውን ሊቀጥል፥ ደግሞም ይቀጥላል፡ ይላል የሐዋርያት ሰራ መጽሐፍ። "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።" ምልክት ያ ነው። ምልክቱ ያ ነው።

97 ጴጥሮስና ዮሐንስ መልካም በሚባለው በር ባለፉ ጊዜ፡ ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ሽባ የሆነ፡ አንካሳ የሆነ ሰው ተኝቶ ነበር፡ እርሱም እንዲህ አለው፡ "ብርና ወርቅ የለኝም፥ ያለኝን ግን፡ እሰጥሃለሁ። በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተነሣና ተመላለስ።" አያችሁ? እነርሱም አነጋገሯቸው፡ መሃይማንና ያልተማሩ ሰዎች እንደሆኑም አወቁ፡ ነገር ግን ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ አስተዋሉባቸው። አያችሁ፡ ምልክቱ በዚያ ነበር፡ ታይቷል። አያችሁ፡ "ይህ ያለኝን!" አንድ ምስኪን፡ የወደቀ ወንድም በዚያ ተኝቶ፡ ሽባ ሆኖና ተበላሽቶ፡ እና ሁሉንም ነገር አዩት። በክርስቶስም የነበረው ያው ህይወት፡ "ይህ ያለኝን!"

98 "በስሜ አጋንንትን ታወጣላ**ችሁ**።" "**እኔ** አወጣለሁ፡" አላለም። "**እናንተ** ታወጣላችሁ!" "**እናንተ** ይህን ተራራ እንዲህ ብትሉት!" "**እኔ** ይህን ተራራ እንዲህ ብለው፡" አይደለም። "**እናንተ** ይህን ተራራ እንዲህ ብትሉት!"

99 ኦህ፡ ወንድሜ፡ ያ ምልክት የሚታይበት ሰዓት ደርሷል። ልናየው እንችላለን። አሁን ወደ መጨረሻው እንደቀረብን እናውቃለን። ምልክቶችንና ድንቆችን ለማሳየት፡ ሁሉንም ዓይነት መልእክቶች ይዘን መጥተናል፡ አሁን ደግሞ ቤተክርስቲያን ምን ማድረግ እንዳለባት ወደሚለው ተመልሰን መጥተናል። ምልክቱ መታየት አለበት። "ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።" ሌላ ምንም ነገር አይሰራም። ደሙ መሆን አለበት። አሁን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ከእግዚአብሔር የተሰጠን ምልክታችን ነው።

100 እንደ ታላቅ፡ የሰነ መለኮት ምሁር፡ የ—የባፕቲስት ወንድም፡ መልካም፡ ጥሩ ባህሪ ያለው፡ አንድ ጊዜ ወደ እኔ ሲመጣ፡ እንዲህ አለኝ፡ "ወንድም ብራንሃም፡" እንዲህ አለ፡ "አንተ ስለ መንፈስ ቅዱስ ትናገራለህ፡" "እንዴ፡ ያ'ኮ አዲስ ነገር አይደለም፡" አለኝ። አለኝም፡ "በዘመናት ሁሉ፡ ስናስተምረው ቆይተናል።" እ—እኔም አልኩ፡ እንግዲህ፡ እ... እርሱ እንዲህ አለ፡ "መንፈስ ቅዱስን ተቀብለናል።"

101 "መቼ ነው የተቀበልከው፡" ብዬ ጠየቅኩት?

102 "ባመንኩ ጊዜ፡" ብሎ መለሰልኝ። ምክንያቱም፡ ያ የባፕቲስት ሥነ መለኮት እንደዚያ መሆኑን አውቅ ነበርና፡ ይኸውም፡ ባመንክ ጊዜ፡ መንፈስ ቅዱስን ትቀበላለህ የሚል ነው።

103 እንዲህ አልኩ፡ "ጳውሎስ ይህን ሲናገር፡ በሐዋርያት ሥራ 19፡ ለተወሰኑ ሰዎች፡ የባፕቲስት አባላት ለነበሩ ተናግሯቸዋል፡ ይኸውም፡ የዮሐንስ ተከታዮች ከነበሩት አንዱ ለነበረው የባፕቲስት ሰባኪ፡ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ሲያረጋግጥላት ነበር።"

104 "በኤፌሶን በላይኛው አገር አልፎ፡ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘና፡ እርሱም እንዲህ አላቸው፡ 'ካመናችሁ **ወዲህ** መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን?' እነርሱም አሉ፡ 'መንፈስ ቅዱስ እንዳለስ እንኳ አላወቅንም።'" ከዚያም እንዴት እንደተጠመቁ ጠየቃቸው። እናም የመሰዋዕት ጠቦት በሆነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አልተጠመቁም ነበር። በእርሱ ዘንድ፡ ከቶ አልታወቁም ነበር። ልክ በዚያ እንደተቀመጠ መድሃኒት፥ ዝም ብለው አምነው፡ ዳሩ ግን

እንዳልወሰዱት ማለት ነው። ጳውሎስም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ዳግመኛ እንዲጠመቁ አዘዛቸው።

105 እናም ይህን ባደረገ ጊዜ፡ ከዚያም ምልክቱ በእነርሱ ላይ መጣ። በመንፈስ ቅዱስ ስራዎችና ምልክቶች ታወቁ፡ በእነርሱ ውስጥ በልሳኖች በመናገር፡ እና ትንቢት በመናገር፡ እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጉ ነበር። ከ—ከመሥዋዕታቸው ጋር ታወቁ።

106 መንፈስ ቅዱስም መታወቂያችን ነው። እንደ ክርስትያኖች እኛ የምንታወቅበት ያ ነው። የአብያተ ክርስቲያናት አባልነታችን አይደለም፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤያችን አይደለም፡ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ያህል እንደምታውቁት አይደለም። ደራሲውን ምን ያህል ታውቃላችሁ ነው፡ አያችሁ፡ ደራሲው ምን ያህል በእናንተ ውስጥ አለ ነው። እራስህ—አንተ እራስህ መሞትህ ነው። ከእንግዲህ የለህም። እንደሞተ ትቆጠራለህ፡ በአንተ ውስጥ የሚነኦረው ምልክቱ ነው። ይህም የገዛ ህይወታችሁ አይደለም፥ እርሱ ነው።

107 ጳውሎስ ሲናገር፡ “አሁን የምኖረው ህይወት (ቀድሞ ከነበረው የተለየ ህይወት ይኖር ነበር።) እኔ አይደለሁም፡ ክርስቶስ ግን በእኔ ውስጥ ይኖራል።” እግዚአብሔር የፈለገው የታወቀው ምልክት ያ ነው። ከእኛ... ከመስዋዕታችን ጋር መታወቅ፡ በአዳኛችን ህይወት በውስጣችን፡ በመንፈስ ቅዱስ መታወቅ።

108 ኦህ፡ እንዴት ያለ—እንዴት ያለ እርግጠኛ ምልክት ነው! ከዚህ በላይ ሌላ ምልክት ሊኖር አይችልም። ኦህ፡ ማይ፡ የዚህን—የዚህን ሃሳብ ብቻ ብትረዱት ኖሮ። ዛሬ ጠዋት፡ በቃላት፡ ገልጬ በነፍሳችሁ ውስጥ የማስቀመጥ ኃይል—ኃይል ቢኖረኝ-... በጆሮአችሁ አይደለም፡ ነገር ግን በነፍሳችሁ፡ እና እናንተ—እናንተ የእርሱን ዋስትና ማየት ብትችሉ። እርሱ—እርሱ የሚወስደው፡ እርሱ እጅግ እንድታርፉ ያደርጋችኋል።

109 ምን ይመስላችኋል፡ ወንጀል ሰርታችሁ፡ በፌደራል ፍርድ ቤት ልትዳኙ ቢሆን። እናም፡ ጥፋተኛ ሆናችሁ ከተገኛችሁ፡ እንደምትሞቱ፡ ወደ ኤሌክትሪክ ወንበር፡ ወይም ወደ ጋዝ ክፍል፡ ወይንም ለእናንተ ወደተዘጋጀው ማንኛውም የአደባባይ ግድያ፡ ምናልባትም ስቅላት፡ ወይም ሌላ ነገር፡ ቅጣቱ ምንም ይሁን ምን፡ እንደምትሞቱ ብታውቁስ። ደግሞም ጥፋተኛ እንደነበረባችሁ... ብታውቁ። ጥፋተኛ መሆናችሁን ታውቃላችሁ፡ ከዚህ ነገር ሊያወጣችሁ የሚችል፡ የሚወክላችሁ ጠበቃ ካላገኛችሁ እንደምትሞቱ አውቃችኋል። ስለዚህ አሁን ልታገኙት የምትችሉትን ምርጥ የተባለውን ጠበቃ ትፈልጋላችሁ።

110 ከዚያም ጥሩ የሆነ፡ ብልህ ጠበቃ ስታገኙ፡ ጉዳያችሁ ትንሽ... ጠበቃ ስላገኛችሁ፡ ትንሽ ልታርፉ ትችላላችሁ። ዳሩ ግን ይህ ጠበቃ የዳኛውን ሃሳብ፡ ወይም የዳኞችን ውሳኔ ሊለውጥ ይችላል ወይስ አይችልም የሚል ጥያቄ አሁንም ይኖራል፥ ይህ ጠበቃ፡ በብልሃት ንግግሩና ህጎቹን በማወቁ፡ ያንን ሊለውጥ፡ እና ለጉዳያችሁ ተከራክሮ—በህይወት መኖር እንዳለባችሁ ማረጋገጥ ይችል እንደሆን ትጠይቃላችሁ። ሆኖም ግን፡ በዚያ ሁሉ—በታላቅ ስልጣኑና ሊያደርገው በሚችለው ታላቅ ንግግሩ፡ እንዲሁም በዳኞች ላይ ሊያሳርፍ በሚችለው ተጽዕኖ ወይም በዋናው ዳኛ ዘንድ በሚኖረው ሞገስ፡ እናንተ—እናንተ—እናንተ... ምናልባት ለጥቂት ደቂቃዎች እረፍት

ልታገኙ ትችላላችሁ፡ ዳሩ ግን አሁንም በአእምሮአችሁ ውስጥ፡ “ሊያደርገው ይችላልን” የሚል ጥያቄ ይኖራል?

111 ዳሩ ግን በዚህ ጉዳይ፡ ፈራጁ ራሱ ጠበቃችን ሆኗል። እግዚአብሔር ሰው ሆነ። ይህን ሊያደርግ የሚችል ምንም ጠበቃ አልነበረም። አንድም ልናገኝ አልቻልንም። ሙሴ፡ እና ህጉ፡ ነቢያትም ቢሆኑ፡ ምንም ሊያደርጉት አልቻሉም። ስለዚህ ፈራጁ ራሱ፡ ዳኛም፡ ጠበቃም፡ ፈራጅም ሆነ፥ የህጉንም ፍትህ በገዛ እጆቹ ወሰደ፡ ዋጋውን፡ ራሱ ከፈለው። ከዚህ በላይ ምን ያህል ደህንነታችን የተጠበቀ ሊሆን ይችላል? እንደተቀበለውም ምስክር እንዲሆን፡ የገዛ ህይወቱን በላያችን ላይ ላከልን። እንዴት ያለ አስተማማኝ ደህንነት ነው!

112 “አዎ፡ በሞት ጥላ ሸለቆ ውስጥ ብሄድ እንኳ፡ ከእኔ ጋር ነህና፡ ክፋን አልፈራም።”

113 እርሱ ራሱ ፈራጅ፡ ዳኛ፡ እና—እና ጠበቃ በሆነ ጊዜ፡ ስለ ጉዳያችን ተሟገተልን። እኛ፡ በገዛ ህጉ ጥፋተኛ ሆነን ተገኝተን ነበር፥ እርሱ ግን መጥቶ በመቅደሱ ውስጥ የነበረውን፡ የጥፋተኛውን ሰው ሰፍራ ወሰደ። ኃጢአቱን ወሰደ። በራሱ ላይ ወሰደው፡ ሞተም፡ ዋጋውንም ከፈለ፡ ደሙንም አፈሰሰ፡ እንዲሁም የገዛ ምልክቱን፡ የገዛ ህይወቱን መለሰልን።

114 ታዲያስ፡ እነሆ እኛ ፍጹም ነን። ጉዳዩ ተዘግቷል። ለአማኙ ከእንግዲህ ኃጢአት የለበትም። አምላክ ሆይ፡ ህዝቡ ከእንግዲህ ምንም ክስ እንደሌለ፡ ይህንን ማየት ካልቻሉ፡ እቤቱ ማረን። “ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው፡ ከሞትም ወደ ህይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድ አይመጣም።” ጉዳዩ ያ ነው። ክሱ ተዘግቷል! ከእንግዲህ ምንም ክስ የለም። አሜን! ስለዚህ ያለምንም ስጋት፡ ምልክቱ ተቀብቶ በሰላም ስትሆኑ፡ ሞት በውጭ ያለውን በር መምታት ሲጀምር፡ በላያችሁ ምንም አቅም የለውም። አያችሁ? አዎ።

115 ምልክቱ ተቀብቷል። አሁን የሚታወቀው ምልክቱ ብቻ ነው። አያችሁ፡ ምልክቱ መምጣት ይችል ዘንድ ይህን አድርጓል። ምልክቱ የእግዚአብሔር ሕይወት ነበረ።

116 እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ሰው ሲፈጥረው፡ ልጅ አደረገው። ልጁም በጣም ብልሹ ስለነበር እግዚአብሔርን ከመስማት ይልቅ የሚስቱን ቃል ሰማ፡ ሴቲቱም በባልዋ ፈንታ ዲያብሎስን ሰምታ ነበር፡ እንግዲህ፡ ይህ ሲሆን፡ ብክለት እስኪያመጡ ድረስ፡ ሁለቱ ተበረዙ። ይህንንም ባደረጉ ጊዜ፡ ልጆች ወደ ዓለም ሊያመጡ እንደሆነ፡ አውቋል። በዛፉ መካከል የነበረው ፍሬ መነካት አልነበረበትም፡ ዳሩ ግን፡ በተነካ ጊዜ፡ ይህንን ኃጢአት፡ በራሳቸው ላይ አመጡ። ስለዚህም፡ የተወለደው የሰው ዘር በሙሉ፡ በኃጢአት ውስጥ ወደቀ። በዚያ፡ መውጫ ምንም መንገድ አልነበረም።

117 ከዚያም እግዚአብሔር ወረደ። እርሱን የሚመልሰበት አንድ መንገድ ብቻ ነበር፡ ያም ዳግመኛ ልጅ አድርጎ መመለስ ነበር። አሁን የገዛ ህጉ በዚያ ቆሞ “ተኮንኗል” እያለ ሳለ፡ ይህን እንዴት ሊያደርገው ይችላል? ከዚያም አብ ራሱ ከእኛ አንዱ ሆነ። እውነተኛው ጠቦት እርሱ ነው። በአእምሮው ውስጥ የነበረው ዓላማ ያ ነበር።

118 ጠቦቱና ርግብ በአንድ ወቅት በሚገናኙበት ወቅት፡ ጠቦቱና ርግብ አብረው እንደሚሆኑ በማወቅ፡ ጠቦቱ በኤደን ገነት ውስጥ በዚያ መልክ የታወቀበት ምክንያት ያ ነው። በዚያም በኩል፡ ሁላችንም አብረን መሆን እንደምንችል ያወቀው፡ ያኔ ነበር። አሁንም፡ ምልክቱ መቀባት እንዲችል፡ ከእንግዲህ ባዕዳን እንዳንሆን፡ ከእንግዲህ እንግዶች እንዳንሆን፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንድንሆን፡ እርሱ እንደዚህ ያለውን መሰዋዕት ለማቅረብ ፈቃደኛ ነበር። አዳምና ሔዋን ሁለቱም፡ ሴቲቱና ወንዱ፡ በአንድነት ተጣምረው፡ በታላቅ መሰዋዕቱ አማካኝነት፡ በክርስቶስ ኢየሱስ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናቸው።

119 እናም፡ ከዚያም፡ ምንም ስህተት እንዳይኖር! በምድር ላይ መተከል ያለበት የዚህ ህይወት ዘር፡ ጠፊ ዘር ከሆነው—ከዚህ አካል፥ ህይወቱም፡ በዘሩ ውስጥ ያለ የተዛባ ህይወት ከሆነ፡ ከዘሩ ጋር አብሮ ይጠፋል። ዳሩ ግን የዘላለምን ህይወት በእርሱ ውስጥ አስቀመጠ፡ በትንሳኤም ዳግመኛ ሊያስነሳው፡ እንጂ እንዳይጠፋ የራሱም እንደሆነ አድርጎ አወቀው። ምን ማለቴ እንደሆነ ገባችሁ?

120 ይኸውላችሁ፡ አሁን ሊጠፋ አይችልም። ህይወት በላዩ ላይ አርፏል። እርሱ ምልክት ነው፡ በዚያች ትንሽ አካል ላይ አረፈ፡ በዚያ ሰው ነፍስ ላይ አረፈ። ይኸው በዚያ ላይ ምልክት አለ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ይህም የእግዚአብሔር ስለመሆኑ ያሳያል። የእርሱ ነው። "ምልክቱን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።" ትክክለኛ ምልክት፡ መንፈስ ቅዱስ ምልክታችን ነው። ስለዚህ፡ መንፈስ ቅዱስን ስትቀበሉ፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገራችሁ። ያለው ነገር ያ ብቻ ነው፡ ምክንያቱም ህይወት በእናንተ ውስጥ ነው። ከእንግዲህ ልትጠፉ አትችሉም።

121 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "ከእግዚአብሔር የተወለደ ኃጢአትን አያደርግም፡ ኃጢአት ሊሠራ አይችልም፡ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ዘር፡" አሜን፡ "የእግዚአብሔር ዘር በእርሱ ይኖራልና።" ኃጢአት የሌለበት እግዚአብሔር በእርሱ ውስጥ እየኖረበት እንዴት ኃጢአት ሊሠራ ይችላል? ኃጢአት በሌለው እግዚአብሔር እየኖረ፡ እንዴት ኃጢአት ሊሠራ ይችላል? ምንም ቢያደርግ፡ ደሙ ይሸፍናልና። አያችሁ? አሁን አዲስ ፍጥረት ነው። ምኞቱ እና ምኞቱ ከሰማይ ነው፡ ምክንያቱም ከእሾህ ወደ ስንዴ ተለውጧልና። ምኞቱ ድሮ እንደነበረው አይደለም፡ ያንንም ያሳያል።

122 "ኦህ፡ ያንን አምናለሁ፡" ትላላችሁ። ሆኖም አሁንም ኃጢአት ትሰራላችሁ? አሃ! ተታላችኋል። አያችሁ? ከምልክቱ በስተቀር ሌላ ምንም ሊያሳይ አይችልም።

123 እስራኤል የጉዞ ትእዛዝ እስኪመጣ ድረስ ከዚያ ደም ስር እንድትቆይ ታዛ ነበር። "ከዚያ ስር እንዳትወጡ!" አንዴ ከዚያ ምልክት ስር ከሆኑ በኋላ፡ በዚያ ውስጥ ታትመው ነበር። "ያንን እንዳትለቁ!" እኩለ ሌሊት እስኪሆንና መለከቶች እስኪነፉ ድረስ ልክ በዚያው ቆዩ። መለከቶቹም በተነፉ ጊዜ፡ ያ የቀድሞው የአውራ በግ ቀንድ መነፋት ሲጀምር፡ እያንዳንዳቸው ስንቃቸውን ይዘው ወጡ፡ ወደ ተስፋይቱም ምድር ሄዱ።

124 በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ወንድ ወይም ሴትም እንደዚሁ ነው፡ እርሱ ታትሞ ተለይቷል፡ ከማንኛውም ጉዳትና አደጋም ደህንነቱ የተረጋገጠ ነው።

ህይወቱ በሙሉ ምን እንደሆነ ያሳያል፡ በሚሄድበት ሁሉ፡ በሚሰራው ስራ ሁሉ፡ ከሚያወራው ሰው ሁሉ ጋር። ከሴቶች ጋር ግንኙነት ሲኖረው፡ ከስራ ባልደረቦቹ ጋር ሲገናኝ፡ ከማንኛውም ነገር ጋር ሲገናኝ፡ ያ ምልክት በዚያ አለ። አሜን! ወደ ሞት ስንመጣ፡ "አንተ ከእኔ ጋር ነህና፡ ክፉን አልፈራም፡" ያ ምልክት በዚያ አለ። ወደ ትንሳኤ ሲመጣም፡ በዚያ ይገኛል፡ እግዚአብሔር በመጨረሻው ቀን ያስነሳዋልና። ኢየሱስም እንደዚያ ብሏል! "ደሙን፡ ምልክቱን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።" ኦህ!

125 አስታውሱ፡ ያ ምልክት ካልታየ፡ ኪዳኑ እንኳ ይፈርስ ነበር። ያ ትክክል ነው። ኪዳኑ ተሽሯል። ያ ምልክት በዚያ እስከሌለ ድረስ—ምንም ዓይነት ኪዳን አልነበረም። ምልክቱ ለቃል ኪዳን የተሰጠ ነው። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን ገባላቸው፡ አዎን፡ ወዳጄ፡ ምልክት ግን መኖር ነበረበት። ምልክቱ ካልኖረ በቀር፡ ኪዳኑ፡ ተግባራዊ አይሆንም ነበር።

126 ብዙ አይሁዶች እንዲህ ሊሉ ይችላሉ፡ "ና'ማ! በሬ ላይ ደም አልቀባሁም፡ ሆኖም አንድ ነገር ላሳይህ እፈልጋለሁ፡ እኔ የተገረዝሁ አይሁዳዊ ነኝ። ተገርዣለሁ።" ያንን **ያ** ማለት አይደለም። [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ—አርታዒ።] "ደሙን ባየሁ ጊዜ! ምልክቱን ባየሁ ጊዜ!"

127 "እኔ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ሜቶዲስት ነኝ፡" ወይም፡ የፈለገውን ልትሉ ትችላላችሁ።

ይሁን እንጂ፡ "ምልክቱን ባየሁ ጊዜ!"

128 እንዲህ ትላላችሁ፡ "እኔ አማኝ ነኝ። እናቴ የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባል ነበረች። አባቴ የዚህች ቤተ ክርስቲያን አባል ነበር። ከልጅነቴ ጀምሮ አባል ነበርኩ።" ያንን **ያ** ማለት አይደለም። [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ—አርታዒ።] "እኔ አልዋሽም፡ አልሰርቅም። **ይሄን** አላደርግም። እ… " ያንን **ያ** ማለት አይደለም። [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ።] "የብራንሃም ተበርናክል አባል ነኝ። **ይህንን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን** አደርጋለሁ። ቃሉን ሁሉ አምናለሁ።"

129 እነዚያ አይሁዶች፡ "ይሖዋን አምናለሁ" ሊሉ ይችሉ ነበር! ቢያምን ኖሮ፡ የዘመኑን መልእክት ባዳመጠ ነበር። ያለጥርጥር።

ብዙ መልእክቶች ነበሯቸው፡ ይሄኛው ግን የዘመኑ መልእክት ነው። አያችሁ? እኔ የዘመኑን መልእክት አምናለሁ። አዎን። ደሙ ሲመሽ ይቀባል።

እነርሱም፡ "እኔ፡ እኔ አይሁዳዊ ነኝ" ሊሉ ይችሉ ነበር።

130 ሰዎች ዛሬ እንዲህ ይላሉ፡ "እኔ ክርስቲያን ነኝ። የረጅም ጊዜ አባልነቴን ላሳያችሁ እችላለሁ። ምን ሰርቄ አውቃለሁ፡ መቼስ ፍርድ ቤት ቆሜ አውቃለሁ እንድትነግሩኝ እፈልጋለሁ። ዝሙት ፈጽሜ እንደሆነ አሳዩኝ፡ መቼ እነዚህን ነገሮች ሁሉ እንዳደረግሁ፡ ወይም የመሳሰሉትን አሳዩኝ። አንዲት ሰፍራ አሳዩኝ።" ይህ አሁን ምንም ትርጉም የለውም። ኧረ፡ በፍጹም። አያችሁ፡ ምን ያህል በኪዳን ውስጥ ቢሆንም፡ ኪዳኑ ከጥቅም ውጪ ነው። ተግባራዊ-አይደለም።

"እንግዲህ፡ እኔ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ነኝ፡" ትላላችሁ።

131 ምንም ሁን አይገደኝም። ያ ኪዳን ከሌለ፡ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያችሁ ነው። ትክክል ነው። ደርሶባችኋል። አዎ። "ኃጢአታችሁ ያገኛችኋል።" ኃጢአት

ምንድነው? አለማመን። መልእክቱን አላመናችሁም። ቃሉን አላመናችሁም። የምልክቱን ምስክርነት፡ በመካከላችን ራሱን ባሳወቀ ጊዜ እንኳ፡ ራሱን አላመናችሁም። ታዲያ ያንን አላመናችሁም? ምን ያህል ብታቃልሉትም፡ መቀባት አለበት።

132 “እምነዋለሁ። አምነዋለሁ። እውነት እንደሆነ አምናለሁ። እንደ እውነት እቀበለዋለሁ፡” ልትሉ ትችላላችሁ። እንግዲያውስ ያ ሁሉ መልካም ነው፡ ዳሩ ግን አሁንም መቀባት አለበት።

133 ለምሳሌ፡ ጠቦቱ እየደማ ሳለ፡ ይህ አንዱ አይሁዳዊ በዚያ ቆሞ፡ ደሙን እያወዛወዘ፡ “ይህ ይሖዋ ነው፡” እያለ ነው።

134 በዚያም አንድ ካህን ተነሳና፡ “አዎን፡ ጌታዬ፡ ይህ እውነት እንደሆነ አምናለሁ፡” ዳሩ ግን በራሱ ቤት ላይ አልተቀባም፡ አለ። በዚያ ደም በበራቸው ላይ ካደረጉት ቡድን ጋር፥ ኸረ፡ በፍጹም፡ ከዚያ ከሐይማኖት አክራሪዎች ጋር አብሮ መታወቅን አይፈልግም። ያንን መታወቂያ አይፈልግም። ምን ያህል ካህን ቢሆንም፡ ቃሉን ምን ያህል ቢያውቅም፡ ምን ያህል በጥሩ ሁኔታ ቢደግም፡ ምን ዓይነት ስራዎችን ቢሰራ፡ ለድሆች ምን ያህል ቢሰጥ፡ ምን ያህል መስዋዕት ቢያደርግም!

135 ጳውሎስ፡ “ስጋዬን፡ እንደ መስዋዕት ሆኖ እንዲቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፥ ለድሆች እንዲመገቡት ንብረቴን ሁሉ ብሰጥ፥ ተራሮችን የሚያፈልስ እምነት ቢኖረኝ፡ እና የመሳሰሉትን፥ በሰዎችና፡ በመላእክት ልሳን ብናገር፥ እና እነዚህን ሁሉ ሌሎች ነገሮችን ባደርግ፡” እና አለ፡ “ምልክቱ እስኪቀባ ድረስ ከንቱ ነኝ። ይህ ምልክት!” ዛሬ ማታ የምናገረው ስለዚያ ነው፡ ስለ ፍቅር። አያችሁ? “አሁን፡ ይህ እስኪቀባ ድረስ፡ እኔ ከንቱ ነኝ።” አያችሁ?

136 አጋንንት አውጥታችሁ ቢሆንም እንኳ፡ አይገደኝም። በእምነት ጸሎታችሁ ድውያንን ፈውሳችሁ ሊሆን ይችላል። እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርጋችሁ ሊሆን ይችላል። ያ ምልክት በዚያ ከሌለ ግን፡ በእግዚአብሔር ቁጣ ስር ናችሁ። አማኝ ልትሆኑ ትችላላችሁ። በመድረክ ላይ ቆማችሁ ወንጌልን ትሰብኩ ይሆናል። “በዚያ ቀን፡ ብዙዎች ወደ እኔ መጥተው፡ ‘ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ በስምህ ትንቢት አልተናገርሁምን፡ በስምህ አልሰበክሁምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣሁምን?’” እነዚህ ሜቶዲስቶች፡ ባፕቲስቶች፡ እና ጴንጤቆስጤዎች ናቸው። ኢየሱስም፡ “እናንተ ዓመፀኞች፡ ከእኔ ራቁ። ከቶ አላውቃችሁም።”

137 “ይሁን እንጂ ምልክት ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።” የዘመኑ የእግዚአብሔር መስፈርት ነው ። የማምሻው-ዘመን መልእክት፡ ምልክቱን መቀባት ነው።

138 ሰይጣን ሁሉንም ዓይነት አስመሳይነት፡ እና እጅ መጨባበጥን፡ እና ማረጋገጫዎችን፡ እና የመሳሰሉትን ነገሮች ሁሉ ወርውሯል። እርሱት! የሆነ የአስመሳይነት፡ አስመሳይ-እምነት፡ የምትክ፡ ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን፥ የምልክቱ፡ የራሱ ዘመን ደርሷል።

139 ምልክቱ ራሱ በመካከላችን ራሱን እያሳወቀ ያለበትን ዘመን ደርሷል፡ እርሱ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ኢየሱስ መሆኑን፡ ከቃሉ ጋር እንደሆነም እያረጋገጠ ነው። መቀባት አለበት። ምልክቱ አለኝ የሚል ሰው፡ ይህንን ቃል የሚክድ ከሆነ፡ ታዲያ ምን ይባላል? አያችሁ፡ ይሄን ማድረግ አትችሉም።

ምልክቱ በዚያ መኖሩ ግድ ነው። “ባየሁ ጊዜ... ደሙ ምልክት ይሆንላችኋል።” አሁን ያ መንፈስ ቅዱስ፡ በደሙ ውስጥ የነበረው ያ ህይወት፡ ለእናንተ ምልክት ነው። ትንሽ ቆይቼ እመጣበታለሁ፡ እያችሁ። መንፈስ ቅዱስ ምልክቱ ነው። ክሱ ተዘግቷል። አዎን፡ ጌታዬ። አሁን፡ አስታውሱ። እኔም...

140 ምንም ብትሆኑ ለውጥ አያመጣም፡ የቱንም ያህል ጥሩ ብትሆኑ፡ **ሰንቴ-ዘላችሁ-እንደወረዳችሁ፡** ሰንት ቸርቾች እንደተቀላቀላችሁ፡ ሰንት መልካም ነገሮችን እንዳደረጋችሁ፡ ምልክቱ ካልተቀባ ምንም ትርጉም አይኖረውም። የማምሻው ዘመን ይህ ነው። ያ በሉተር ዘመን በትክክል ሰርቷል፡ ይህም በዌስሊ ዘመን በትክክል ሰርቷል፡ አሁን ግን አይሰራም። በጭራሽ።

141 አዎ፡ ጠቦቱን ጠብቆ ማቆየት በዚያን ጊዜ መልካም ነበር። ደሙ፡ ማለትም የጠቦቱ ደም፡ ከመቀባቱ በፊት የሞቱት እነዚያ የተለየ ነበር። አዎን፡ ጌታዬ። በበጎ ህሊና ምክንያት አልፈው ሄደዋል። መሆናቸውን እና—አለመሆናቸውን ይፈረዳሉ...

142 አስቀድመው የተወሰኑ ከነበሩ፡ ያገኛቸዋል። ካልነበሩ ግን፡ አያገኛቸውም። አለቀ። እርሱ አምላክ ነው። “እርሱ—እርሱ የሚፈልገውን ያጸድቃል፡ የፈለገውን ይምራል፡ የፈለገውን ይኮንናል።” እርሱ አምላክ ነው። አለቀ። “የሚምረውን ይምራል፡ ሊኮንነው የሚፈልገውንም ይኮንናል።”

143 አንድ አይሁዳዊ፡ አማኝ መሆኑን፡ በግርዛቱ አማካኝነት በግልጽ ሊያሳይ ይችል ይሆናል።

144 ብዙ ወግ አጥባቂ፡ ሰዎች፡ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው፡ “እኔ አማኝ ነኝ፡ ኢየሱስም ‘በእምነት’ ድናችኋል ብሏል። እኔ አማኝ ነኝ፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ምንም አይጠቅመኝም” ይላሉ። ስለዚህም ምልክቱ አልተቀባም። ምንም ያህል፡ ቢያምንም እንኳ፡ ከንቱ ሆኗል።

145 ልክ እንደ አይሁዳዊው ግረዘት ማለት ነው። እርሱም፡ “እኔ አይሁዳዊ ነኝ። እንደሌሎቹ ወግ አጥባቂዎች ወደዚያ መውጣት ለምን ያስፈልገኛል? ”

146 ሙሴ በመንገድ ላይ፡ ወዲያ-እና-ወዲህ እየተመላለሰ፡ ቆሞ፡ “የማምሻው ዘመን መልእክት ደርሷል! እንዲህም አድርጉ፡ አስራ አራቱ ቀን በተፈጸመ ጊዜ፡ ማኅበሩን በአንድነት ሰብስባችሁ ጠቦቱን ታርዳላችሁ። የእስራኤል ማኅበር ሁሉ፡ እጆቻቸውን በላዩ ላይ ጭነው፡ ከእርሱ ጋር ራሳቸውን በማሳወቅ ያርዱታል። ደሙም በበሩ መቃንና፡ በጉበኑ ላይ ይቀባል፡ እናም፡ ‘ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ፡ ምክንያቱም እኔ ያዘጋጀሁላችሁን የጠቦቱን ሞት እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ ምልክት ነውና’” ይል ነበር። ደሙ ምልክቱ ነበር።

147 አሁን መንፈሱ ምልክት ነው። “ከጥቂት ቀናት በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትሞላላችሁ።” እና ደሙ በፈሰሰ ጊዜ፡ እንደሚነጥቅ፡ አውሎ ንፋስ ሆኖ፡ ምልክቱ በጴንጤቆስጤው ቀን ተላከ።

148 የሁሉም ሐዋርያቶች ዋና መልእክታቸው ያ ነበር። ያም፡ “ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ፡ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታም ትቀበላላችሁ፡ እርሱም ከሞት ወደ ህይወት እንደተሻገራችሁ፡ እሜን፡ የሚያሳይ ምልክት ነውና” የሚል ነበር። ይኸው ነው። ያች የአሕዛ-... የአይሁድ

ቤተክርስቲያን በከሰመች ጊዜ፡ አሕዛብ ተረከቡት፡ እና እንደዚያ ያለ መዛባት መጣ፥ አሁን ደግሞ ስለ ሰሙ የተጠሩትን፡ የአሕዛብን ቅሬታ፡ ሙሽራይቱን፡ ለማውጣት እርሰዋ ወጥታለች።

149 ምን ለማለት እንደፈለኩ አያችሁ? ቅዱስ ቃል ስለ ምን እንደሚናገር አይታችኋል? ምልክቱ ካልታየ፡ ቃል ኪዳኑ ጥቅም አልነበረውም። አያችሁ? መሆን አለበት። ምክንያቱም፡ እምናለሁ እያላችሁ፡ የቃሉን መመሪያዎች የማትከተሉ ከሆነ፡ እንግዲያውስ አላመናችሁም። አያችሁ? የተገረዛችሁ ብትሆኑም፡ አባል ብትሆኑም፡ እና የተጠመቃችሁ ብትሆኑም፡ እንደዚህ ያሉትን ነገሮች ሁሉ አድርጋችሁ ቢሆንም እንኳ፥ ያ አሁንም ምልክቱ፡ መንፈስ ቅዱስ አይደለም።

150 ቅድም እንዳልኩት፡ ይህ መልካም ምሁር ሊያነጋግረኝ ቀጠለ። እሱም፡ "ቢሊ፡" አለ፡ "አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት። ሰው እግዚአብሔርን ከማመን በቀር ሌላ ምን ሊያደርግ ይችላል? "

151 እንዲህ አልኩት፡ "እውነት ነው፡ ዶክተር። ትክክል ነው። እግዚአብሔርን አመነ። መጽሐፍ ቅዱስም ይላልና። ትክክል ነህ። የመጣህበት ርቀት ያህል፡ ልክ ነህ።"

152 ሄደው የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ የተላኩት፡ አ—አሥራ ሁለቱ—ሰላዮች፡ ወደ ከነዓን አቅጣጫ ወደፊት እስከተራመዱ ድረስ፡ መሬት እየያዙ ነበር፥ ዳሩ ግን ወደ ድንበሩ በመጡ ጊዜ፡ ከዚያ በኋላ አልተቀበሉም።

153 እንዲህ አልኩት፡ "እናንተ ባፕቲስቶች እስካሁን በመጣችሁበት መንገድ፡ ጥሩ ናችሁ፡ ዳሩ ግን ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀብላችኋልን? " ህምም። እንዲህ አልኩ፡ "አስታውሱ፡ እግዚአብሔር የአብርሃምን እምነት ተቀብሎታል። እግዚአብሔርን አ—አመነ፡ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት፡ እውነት ነው፡ ነገር ግን ከዚያም እግዚአብሔር እምነቱን እንደተቀበለው የሚያሳይ ማረጋገጫ፡ ምልክት አድርጎ፡ የግርዘትን ማህተም ሰጠው።" የተገረዘው ሰጋው፡ ከነፍሱ ጋር፡ ምንም የሚያገናኘው ነገር ኖሮት አይደለም፡ ነገር ግን እርሱ (እግዚአብሔር) እምነቱን እንዳወቀለት የሚያሳይ ምልክት ነበረ።

154 እናም እግዚአብሔር እኛንም፡ አማኞች አድርጎ እንደተቀበለን የሚያሳይ ምልክት፡ የመንፈስ ቅዱስን ምልክት ሰጥቶናል። ምክንያቱም፡ "ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ። የተሰፋው ቃል ለእናንተ ነውና!"

155 ነጥቡን አሁን ያዙት። አይሁዶች፡ ምንም ያህል የተገረዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ቢችሉም፡ ምልክቱ ግን መታየት ነበረበት። በዚያ ከሌለ፡ ኪዳኑ ተግባራዊ አይሆንም። በጭራሽ።

156 ምንም ብታደርጉ፡ መጽሐፍ ቅዱስን ምን ያህል—ምን ያህል ማብራራት ብትችሉም። አሁንም ያው ነው፡ ያው ነገር ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ ልትሆኑ ትችላላችሁ። ኦህ፡ ማይ! እናንተ—እናንተም፡ "እኔ አማኝ ነኝ፡ እናም ሁሉም ነገር ነኝ" ልትሉ ትችላላችሁ። ዳሩ ግን አሁንም ምልክቱ ያስፈልጋል። "እኔ ጥሩ ሰው ነበርኩ፡ ወንድም ብራንሃም፡" የምትል፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ።

157 "ማንም የሚለውን አልሰማም፡ ያንን ሰው ልታገኙት አትችሉም። በህይወቴ እንዳች ክፉ ነገር ሲያደርግ፡ አይቼው አላውቅም።" ***ያ*** ከእግዚአብሔር ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለውም። [ወንድም ብራንሃም ጣቱን አንቃጨለ—እርታዒ።] አንድ መሰፈርት አለ፡ እናም ያ ብቻ!

158 እናም ያንን ልታደርጉት አትችሉም። ደሙን በበሩ ጉበን ላይ ልትቀቡት አትችሉም፡ ማለት፡ ምልክቱ በዚያ ሊኖር የሚችለው ጠቦቱ ከሞተ ብቻ ነው። ደሙም የጠቦቱን መሞት የሚያሳይ እርግጠኛ ምልክት ነበረ። አስመሳይነት-እምነት አልነበረም፥ ጠቦቱ ሞቷል!

159 ደግሞም መንፈስ ቅዱስ ጠቦታችሁ እንደሞተና የእርሱ የሆነው ህይወት በውስጣችሁ ስላለ፡ ምልክቱን በራሳችሁ ላይ እንደተቀበላችሁ የሚያሳይ እርግጠኛ ምልክት ነው። አያችሁ? ምንም አስመሳይ-እምነት የለም። ምንም የማስመሰል-ድርጊት የለም። ምንም ማስመሰል አይቻልም። ራሱ አለ! ታውቁታላችሁ። ታውቁታላችሁ። ዓለም ያውቀዋል። ምልክቱ ራሱ አለ።

160 ሰውዬው ምንም ያህል ጥሩ ቢሆን ግድ የለኝም። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪም ሊሆን ይችላል። ምናልባት… የ—መልካም የቤተክርስቲያን አባል ሊሆን ይችላል። ጥሩ ሰው ሊሆን ይችላል። ምናልባት የሃይማኖት ተቋም አለቃ—ሊሆን ይችላል። የሮም የስልጣን ተዋረድ—ሊሆን ይችላል። ማን እንደሆነ አ—አላውቅም፡ ያ—ያ ምንም አያደርገውም።

161 የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የሆነ ሁሉ ግን፡ እስራኤል፡ በትክክልም፡ ወደ ተስፋይቱ ምድር ስትጓዝ፡ የቤተክርስቲያን ምሳሌ እንደነበረች ያውቃል። እርስዋም እየተጓዘች ያለችው ወደዚያ ነው።

162 ነገር ግን የማምሻው ዘመን ሲደርስ፡ ጉዞውም ሲቀጥል፡ አንድ ወሳኝ የሆነ መስፈርት ነበር። ምንም እንኳን ምንም ያህል አይሁዳዊ ቢሆን፡ ወይም ሰብሉን ምን ያህል በደንብ ቢንከባከብ፡ ወይም ጎረቤቶቹን ምን ያህል በደንብ ቢንከባከብ፡ ወይም ምን ያህል ቢደክም፡ ወይም ምን ያህል የቤተክርስቲያን አባል ቢሆን፡ ወይም ምን ያህል አስራት ቢሰጥ ምንም ለውጥ አያመጣም። እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካም ነበሩ። ጥሩ ነገር ነው። እሱም መልካም ሰው ነበር፡ በሕዝቡ ዘንድም፡ እንደ መልካም ሰው ተቆጥሯል። ነገር ግን፡ የደሙ ምልክት ከሌለ፡ ጠፍቷል።

163 ኦህ፡ እዚህ ላላችሁትም ሆነ፡ በቴፑ ላይ ለምትሰሙት፡ ይህንን በሚገባ እንዳሰረግጥ እግዚአብሔር ይርዳኝ!

164 ምንም ቢሆን፡ ወንጌልን ሰብካችሁ ሊሆን ይችላል፡ አጋንንትን አውጥታችሁ ሊሆን ይችላል፡ በልሳኖች ተናግራችሁ ሊሆን ይችላል፡ ጮኻችሁ ሊሆን ይችላል፡ በመንፈስ ጨፍራችሁ ሊሆን ይችላል፡ ያለ ምልክቱ ዋጋ ግን የለውም።

"ይህን ማድረግ እችላለሁን፡" ትላላችሁ?

165 ጳውሎስ ትችላላችሁ ብሏል ። "በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር፡ ድሆችን ለመመገብ ንብረቴን ሁሉ ብሰጥ፡ ሰጋዬንም እንደ መሰዋዕት ለመቃጠል አሳልፌ ብሰጥ፡ ተራሮችን እስካፈልስ ድረስ እምነት ቢኖረኝ፡ እነዚህንም ነገሮች ሁሉ ባደርግ፡ ገና ከንቱ ነኝ።" በዚህ ላይ አትደገፉ።

ዋናው ምልክቱ ነው! ምንም ያህል ስራ ብትሰሩ፡ ምንም ያህል ጥሩ ብትሆኑ፥ የእግዚአብሔር ቁጣ ሲንበለበል፡ እውቅና የሚሰጠው ለምልክቱ ብቻ ነው።

166 የሚፈለገውን ዋጋ፡ መከፈሉን የሚያሳይ ምልክት ነው። የተከፈለውም ዋጋ የኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት ነበር፡ እርሱም ሕይወቱን ሰጥቷል። ተቀባይነት ማግኘታችሁንም የሚያሳይ ምልክት ሆኖ፡ የእርሱ መንፈስ በእናንተ ላይ ተመልሶ ይመጣል። እናንተም ምልክቱን በእሁድ ቀን ብቻ ሳይሆን፡ ቀንና ሌሊት፡ ትሸከሙታላችሁ፡በማንኛውም ጊዜ። ምልክቱ እላችሁ። "እኔ... ደሙ ምልክት ይሆንላችኋል።"

167 "አሁንም አምናለሁ። እኔ አማኝ ነኝ፡" ትሉ ይሆናል። ምንም አይደለም። ሆኖም ምልክቱን የምትጥሉ ከሆነ፡ ታዲያ እንዴት አማኝ ልትሆኑ ትችላላችሁ? በእናንተ ላይ ይመሰክራል። አያችሁ፡ ድርጊታችሁ፡ ምስርነታችሁን ይቃወማል።

168 የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ፡ ጥሩ ሰው፡ የቤተክርስቲያን አባል ይሁን፡ ምንም ይሁን ምን፡ ምንም ትርጉም የለውም። አዎን፡ ወዳጄ። ምናልባት አባትሽ ሰባኪ ሊሆን ይችላል። ምናልባት እናትሽ—አባትሽ ቅድስት ነበረች። ምን... ያ—ያ ምንም አይደለም፡ እነርሱ ለራሳቸው መልስ ይሰጡ። እንዳልኩት፡ ሞክሩት...

169 ሰዎች እግዚአብሔርን እንደ አንድ ትልቅ፡ ያረጀ፡ ወፍራም፡ ሞዛዛ አያት አድርገው ሊስሉት ይሞክራሉ፡ አያችሁ፡ እንዲሁም እንደ ትናንሾቹ፡ እንደ ሪኪዎችና ኤልቪሶች ያሉ፡ የልጅ ልጆች ህዝብ እንዳሉት አድርገው፡ "ምንም ክፋት የለባቸውም" ይላሉ።

170 እግዚአብሔር እንዲህ አይደለም! የልጅ ልጆች የሉትም። እርሱ አባት ነው። ዳግመኛ መወለድ ግድ ነው! እርሱ ትልቅ ልፍስፍስ ሞዛዛ አይደለም።

171 እርሱ የፍርድ አምላክ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እርሱ እንደሆነ ይናገራል። ቁጣው አስፈሪ ነው። በእርሱ ላይ እየረገጣችሁ የእግዚአብሔር ቸርነት አንድ ቀን፡ እስከ ሀጢአታችሁ፡ ወደ ሰማይ ይወስደኛል ብላችሁ አትጠብቁ። ይህን ያደርግ ቢሆን ኖሮ፡ ይህን ሁሉ ትቶ፡ ሔዋንን በወሰዳት ነበር። ቃሉን ታምናላችሁ፡ ወይም ት... ትጠፋላችሁ። ቃሉን ስታምኑ ደግሞ፡ ምልክቱ በእናንተ ላይ ይሆናል። ኧ-ህ።

172 በዚያች ሌሊት፡ ሞት ግብፅን በማንኛውም ሰዓት ለመምታት ተዘጋጅቶ ነበር። አስፈሪ ጊዜ ነበር፥ የአምልኮ ሥርዓቶቻቸው ሁሉ፡ የበዓል ቀኖቻቸው ሁሉ፡ እንዲሁም የጾም ቀኖቻቸው ሁሉ።

173 እግዚአብሔር ጎብኝቷቸው ነበር። እግዚአብሔር በመካከላቸው ታላላቅ ምልክቶቹንና ድንቆቹን አሳይቶ ነበር። ይህ ምንድን ነው? አሁን ለአንድ ደቂቃ ቆም በሉ። እግዚአብሔር ጸጋውን አሳይቷቸው ነበር። እድል ሰጥቷቸው ነበር ።

174 ሊክዱት አልቻሉም። እንዲህ ብለዋል፡ "ኦህ፡ ምንም አይደለም። ትርጉም የለሽ ነው። እዚያ ፏፏቴ ላይ የሆነ ነገር ተፈጥሮ ነው፡ የቀይ ጭቃ ፍንዳታ ስለነበር—ነው፡ ባህሩን ቀይ ያደረገው" አሉ። ከዚያም በረዶ መጣ። ከዚያም እንቁራሪቶች መጡ። እግዚአብሔር ቦታ አዘጋጅቶ፡ ቃሉን በነቢይ አፍ ውስጥ አደረገ። እርሱ የተናገረውም ሁሉ፡ ሆነ፡ አዩትም። ሊክዱት አልቻሉም።

175 ሙሴ የጠየቀውን፡ ያንኑ፡ ከእግዚአብሔር አገኘ፡ ምክንያቱም እርሱ የተናገረው የእግዚአብሔርን ቃል ብቻ ነበር። እርሱም፡ "እኔ አምላክ

አደርግሃለሁ” አለው። ሙሴ ለእነርሱ አምላክ ነበር። አያችሁ? ሌላ ምንም የሚያውቁት አልነበረም፡ ስለዚህም፡ “አምላክ ትሆናቸዋለህ፡ አሮንም ነቢይህ ይሆናል። አየህ፡ አንተ እንደ አምላክ ትሆናለህ፡ ምክንያቱም እኔ አንተንና፡ ድምጽህን፡ ወሰጄ በአንተ እፈጥራለሁ። እኔ እናገራለሁ፡ ህዝቡም ሊክደው አይችልም፡ ምክንያቱም ልክ እዚያው ይፈጸማል። የምትለው፡ ይሆናል።” ኦህ፡ ማይ! “እነዚያን ነገሮች አሳይሃለሁ።” ማይ! ግብጽም ይህንን አየች። ልክ ከምሽቱ ጊዜ በፊት፡ ወይም ልክ በምሽቱ ጊዜ አዩት።

176 ቸርነቱን አሳያቸው። ማሰወገድ፡ መፈወስ እንደሚችል አሳይቷል።

177 አስመሳዮችም፡ ተመሳሳይ ነገር ለማድረግ ሞከሩ። ሁል ጊዜ ታገኟቸዋላችሁ። ያኔስ እና ያምብሬስ ነበሩ፡ ቆመው ነበር። ወደ እውነተኛው ነገር ሲመጣ ግን፡ ገና አላገኙትም። በትክክል። ለትንሽ ጊዜ፡ ተከተሉ። ነገር ግን፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ፡ ከንቱነታቸው ተገለጠ።

178 መጽሐፍ ቅዱስም “ኢያኔስና ኢያንበሬስ ሙሴን እንደተቃወሙ፡” በመጨረሻው ዘመን እንዲሁ ይሆናል አይልምን? ይሁን እንጂ ሰንፍናቸው ተገለጠ፡ አሁንም እንዲሁ ይሆናል። አያችሁ? ይኸውም፡ የተበላሸ አእምሮ ያላቸው ሰዎች፡ ስለ እውነትም፡ እውነትን የማይቀበሉ ሰዎች ናቸው። ጉባኤዎችና ታላላቅ ነገሮች፡ እንዲሁም ታላላቅ፡ ከፍ ያሉና፡ ትላልቅ የአበባ የተሞሉ ነገሮች ሊኖራቸው ይችላል፡ ነገር ግን ሰዓቱ በመጨረሻ ይመጣል።

179 ከምልክቱ ጋር ጽኑ! እግዚአብሔር እንድናደርግ የሚፈልገው ይህ ነው። ቃሉን አጥብቃችሁ ያዙ። አትራቁት። አብራችሁት ሁኑ። መጽሐፍ ቅዱስ ብሏልና።

180 ሞት እየመታ ነበር። እግዚአብሔር ምህረትን አሳይቶአቸው ነበር፡ ኃይላትንና ምልክቶችን አሳይቶ ነበር።

181 አሁን ለአንድ ወይም ለሁለት ደቂቃ ያህል እናቁም፡ በዚያ ሰዓት። በመጨረሻዎቹ ቀናት ምን እንደሚሆን ቃል የገባውን፡ በአእምሯችን ወደ ኋላ መለስ ብለን፡ እናስብ። እኛም፡ አላረጋገጥንም ይሆን ብዬ እገረማለሁ። አያችሁ?

182 እርሱ እነዚህን ነገሮች ሁሉ አድርጎ ነበር፡ ዳሩ ግን አሁንም ንስሃ ለመግባት፡ ወይም የዘመኑን መልእክት ለማመን አልፈለጉም። በፊታቸው ታይቶና፡ በእርግጥ ታውቆ የነበረ ቢሆንም እንኳ፡ አሁንም ለማድረግ አልፈለጉም።

183 እንደዚህ ያሉ ነገሮች ሲፈጸሙ ስታዩ፡ የመጪው ፍርድ ምልክት ነው። እነዚያን ነገሮች ፍርድ ይከተላቸዋል። ሁልጊዜም እንደዚህ ሆኖአል፡ ይህም ከዚህ የተለየ አይሆንም። አያችሁ? ፍርድ ጸጋን ይከተላል። ምህረት ሲናቅ፡ ከፍርድ በቀር ሌላ ምንም የሚቀር ነገር የለም። ስለዚህ ሁልጊዜ ይከተላል።

184 አሁን፡ ትዕይንቱ። እያንዳንዱ መንፈሳዊ ክስተት ከእግዚአብሔር የሆነ ምልክት ነው። ተጠንቀቁ። ይህንን አስተውሉ፡ አያችሁ። ተመልከቱ፡ እያንዳንዱ መንፈሳዊ ክስተት፡ የሚሆነው ነገር ሁሉ፡ ምልክት ነው። እኛ እዚህ ያለነው በአጋጣሚ አይደለም። እነዚህ ነገሮች በአጋጣሚ ብቻ የሚሆኑ አይደሉም። ምልክት ነው። በፍጥነት፡ ወደ—ደህንነት ለመድረስ፡ ምልክት ነው። ኖኅ

ለትውልዱ ምልክት ነበር፥ ኤልያስም ለትውልዱ ምልክት ነበር፥ ዮሐንስም ለትውልዱ ምልክት ነበር። አያችሁ? ሁሉም ነገር፡ የዘመኑ መልእክት፡ ምልክት ነው። አስተውሉት፡ ምን እያደረገ እንዳለ ተመልከቱ። አያችሁ? ምልክት ነው። ሁሉም ነገር ትርጉም አለው።

185 እናም እንዲህ አይነት መልእክት ከዚህ በኋላ ሊከሰት የሚችልበት ሌላ ጊዜ የለም። በሉተር ዘመን ሊመጣ አይችልም ነበር፡ በዌስሊ ዘመን ሊመጣ አይችልም ነበር፡ በጴንጤቆስጤ ዘመን ሊመጣ አይችልም ነበር። ሊያደርገው አይችልም። አያችሁ? የለም... እንደዚህ ያለ ነገር ሆኖ አያውቅም፡ ሆኖም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተስፋ ተሰጥቶን ነበር። አያችሁ? እኛ በመጨረሻው ላይ ነን። ምንም ነገር ሊሆን አይችልም፡ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ሊሆን አይችልም ነበር። ደግሞም ለምልክት እየሆነ ነው። ምልክቱ ምንድን ነው ብዬ አስባለሁ?

186 ኦህ፡ ምስኪን ሰዎች፡ ወንድሜ፡ እህቴ፡ ከዚያ ምልክት ስር፡ በፍጥነት ግቡ። አያችሁ? ምንም፡ ምንም ዓይነት ምትክ አትውሰዱ። ምንም፡ ምንም፡ ምንም፡ ያንን አታድርጉ። አያችሁ? በቃ አታስቡት። ምልክቱ መቀባቱን እስክታውቁ ድረስ እዚያው ቆዩ፡ በክርስቶስ የነበረው አሳብ (በሙላት) በእናንተ ውስጥ እስኪሆን ድረስ፡ የዓለም ከንቱነት ሁሉ እስኪጠፋ ድረስ፡ አያችሁ፡ የልባችሁ ፍላጎት ሁሉ እርሱ እስኪሆን ድረስ። አያችሁ? ስለዚህ፡ ያኔ፡ ታውቃላችሁ፡ ያኔ የሆነ ነገር እየሆነ እንደሆነ ታውቃላችሁ። ኢየሱስ፡ "ያመኑትን እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል" አለ፡ አስመሳዮችን-አማኞች ሳይሆን፡ አማኞችን ነው። አያችሁ? አሁን፡ በዚህ ላይ ምንም ዓይነት፡ ምንም ዓይነት አደጋ መውሰድ አንፈልግም፥ ማድረግ የለባችሁም።

187 የዘመኑ መልእክት ለአብያተ ክርስቲያናት ምልክት ነው። ለሕዝቡ ምልክት ነው። እናንተስ... ተ—ተረድታችሁታልን? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] በቴፑ ላይ፡ እንዲሁም በሌሎች የዓለም ክፍሎች ያሉትም፡ አያችሁ፡ ያንኑ ነገር እያደረጉ እንደሆነ፡ ተስፋ አደርጋለሁ። አያችሁ፡ የወቅቱ ምልክት እዚህ አለ። መደረግ ያለበት ምልክት አለ፡ በሌላ በየትኛውም ጊዜ ሊመጣ አይችልም ነበር።

188 ለዚያ ጊዜ የእግዚአብሔርን ዝግጅት አስተውሉ። አሁን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው እንደምናውቀው፡ "እነዚያ ነገሮች ሁሉ የተከሰቱት፡ አያችሁ፡ ለእኛ ምሳሌ እንዲሆኑ ነው።" አስተውሉ፡ እግዚአብሔር ግብጽን ለመፍረድ በተዘጋጀ ጊዜ፡ በመጀመሪያ ዝግጅት አደረገ። ለመጀመሪያ ጊዜ ምን አደረገ? አሰራሩን ፈጽሞ አይለውጥም።

189 በመጀመሪያው ጊዜ፡ እንዲህ ሲያደርግ፡ ዝግጅቱን ሲያደርግ፡ መልእክት የያዘ ነቢይ ላከ። ለህዝቡ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር መልእክት ያለው ነቢይ መላክ ነበር።

190 በመቀጠል ያደረገው ነገር፡ ነቢዩን ለማሳወቅ፡ የሚታወቅበት የእሳት ዓምድ ላከ፡ ለማሳወቅ።

191 የተላከውም ሦስተኛው ነገር ምልክት ነበር። በትክክል እውነት ነው። ምልክቱ፡ የምልክቱ ትርጉም ምን ነበር? ዋስትና!

192 በመጀመሪያ፡ መልእክቱን የያዘው ነቢዩ፥ በመካከል ራሱን አረጋገጠ... ከ—ከእሳት ዓምድ ጋር ከነቢዩ ጋር፥ ከዚያም ከዚህ ደም ስር እንድትገቡ፡

እርሱ በእናንተ ቦታ ይህን ሞት በምትክ እንደተቀበለ የሚያሳይ፡ ምልክት ላከ። ከዚያም፡ ደሙ እርሱ እንደተመለከተ፡ መልእክቱን እንደሰማችሁ፡ በእሳት ዓምድ ላይ እንዳመናችሁ፡ እንዲሁም እርሱ ያዘጋጀላችሁን ምትክ እንደተቀበላችሁ፡ እና ስለ እናንተ ከፈሰሰው የሕይወት ኬሚስትሪ ደም ስር እንደነበራችሁ የሚያሳይ ምልክት ነበር። ማይ! ምንኛ ፍጹም፡ ምንኛ ፍጹም ነገር ነው፡ አያችሁ፡ እናንተ ከደሙ ስር ናችሁ።

193 አሁን እናንተ ከመንፈስ ስር ናችሁ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ስር። አያችሁ? አያችሁ? የዘመኑን መልእክት ታምናላችሁ፡ አያችሁ፡ ኃ—ኃ—ኃ—ኃ—ኃይሉን ታምናላችሁ፡ የ—የ—የእሳት ዓምዱን። ታምናላችሁ፡ አያችሁ፡ አዎን ትማናላችሁ።

194 አሁን፡ አሁን ተመልከቱ፡ ማመን ብቻውን በቂ አይደለም። አ—ይበቃም... ባለበት ዙሪያ መመላለስ፡ በቂ አይደለም። አያችሁ፡ ያ ራሳችሁን የባሰ ማድረግ ነው፡ “መልካም ማድረግን አውቆ፡ ለማያደርገው፡ ለእርሱ ኃጢአት ነውና።” አያችሁ፡ የድንበር አማኞች፡ ኢየሱስ ስለ ተመሳሳይ ነገር ተናግሯል።

195 ዕብራውያን፡ ምዕራፍ 6 ላይ፡ “አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፡ ከመንፈስ ቅዱስ ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃል የቀመሱትን፡ ዓለምም ከሚመጣው ዓለም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን፡ በኋላም የካዱትን፡ እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፥ የእግዚአብሔርን ልጅ ለራሳቸው እንደገና ሰቅለው፥ እንዲሁም የተቀደሱበትን፡ የደም ኪዳን ያክፋፋትን... ” እዚያ ያለው ኬሚስትሪ ይቀድሳል። ምልክቱ አይደለም። ደሙ ምልክቱ አይደለም እንግዲህ። ሕይወት ነው ምልክቱ።

196 እንስሳ ስለሆነ፡ ህይወት በዚያ አይገኝበትም ነበር። ኬሚስትሪው ራሱ ምልክት ነበር፡ በበሩ ላይ ቀጥተኛ ደም መቀባት ነበረባችሁ። አሁን ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። ያንን ለማረጋገጥ፡ ከአፍታ በኋላ፡ እንመጣበታለን፡ አያችሁ። ምልክቱ የሆነው ሕይወት ራሱ ነው።

197 የእናንተ ሕይወት አልፏል፡ እናንተም ሞታችኋል፡ ሕይወታችሁም ሞቷል። በክርስቶስ በኩል፡ በእግዚአብሔር ተሰውራችኋል፡ በመንፈስ ቅዱስም ታትማችኋል። በክርስቶስ የነበረው አሳብ በእናንተ ውስጥ ነው። ክርስቶስ፡ መጽሐፍ ቅዱስና፡ ቃሉም፡ አንድ ናቸው። “በመጀመሪያ ቃል ነበረ፡ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፡ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።” ያን ጊዜ እናንተና፡ ቃል፡ እና እግዚአብሔር፡ እና ክርስቶስ፡ አንድ ናችሁ። “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ውስጥ ቢኖር፡ የፈለጋችሁትን ጠይቁ፡ ይደረግላችኋል።” አያችሁ?

198 ከቃሉ ጋር ወደዚያ ወጥቶ እንዲናገር፡ ኃይሉን በሙሴ ከንፈሮች ውስጥ አስቀመጠው፡ እንቁራሪቶችም መጡ፥ ተናገረ፡ እንቁራሪቶች ሄዱ፥ ተናገረ፡ ቅማል መጣ፥ ተናገረ፡ ሕይወት—ቅማል ሄደ። አሜን!

199 ዳሩ ግን ምልክቱ ለእስራኤል ሁሉ አስፈላጊ ነበር። ይህ ምልክት ከእስራኤል ሁሉ ይፈለግ ነበር። “እና ምልክቱን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።” ኦህ፡ ማይ፡ ማይ! እንዴት ያለ ማረጋገጫ ነው!

200 እስራኤል ከግብፅ መውጣቷ፡ ዛሬ ላለው እውነተኛው አካል፡ ምሳሌ ነበረች። ግብፅ ቤተክርስቲያን ነበረች፡ እስራኤል ደግሞ ሙሽራይቱን ትወክል ነበር። እስራኤል ከግብፅ እንደወጣች፡ ሙሽራይቱም እንዲሁ ከቤተክርስቲያን

ትወጣለች። አያችሁ? ምክንያቱም፡ የምትወጣበት አንድ ነገር እዚያ መኖር አለበት፡ ስለዚህ፡ ምሳሌ ከሆነ፡ መውጣት አለባት። ቤተክርስቲያን በ—በታች በግብፅ፡ በዓለምና በኃጢአት ውስጥ ናት፡ ስለ—ስለ—ስለ ምልክታችሁም ቅንጣት ታክል ግድ የላትም። እንደውም አያምኑበትም። እስራኤል ግን ወደደው፡ ምክንያቱም ለእነርሱ ድነት ነበርና። ኦህ! ኦህ! ሊያስደስተን ይገባል፡ ልባችንን... ኦህ!

201 ቤተክርስቲያን ሆይ፡ ተቀቢው! አሁን አይለፋችሁ። እሺ? ፀሐይ እንድትጠልቅ አ፡ አ፡ አታድርጉ። ቀንም ሆነ ማታ፡ አ፡ አ፡ አ፡ አትረፉ። ምንም እድል አትክሰሩ። አይሠራም። ልጆች ሆይ፡ አይሠራም። ምልክቱ መያዝ አለባችሁ!

202 እንዲህ ትላላችሁ፡ "እምናለሁ። አዎ፡ እሄዳለሁ። እኔ፡ አዎ፡ መልእክቱን አምናለሁ። እ... " ያ ጥሩ ነው፡ ግን፡ ያ—ያ ጥሩ ነው።

203 ሆኖም ምልክቱ ሊኖራችሁ ይገባል! ብራንሃም ታበርናክል ሆይ፡ ይሰማችኋል? ምልክቱን ልታሳዩ ይገባል! ያለ እርሱ፡ እምነታችሁ ሁሉ በከንቱ ነው። አያችሁ? መልካም ሕይወት ትኖራላችሁ፥ ቃሉ የሚለውን ትሰማላችሁ፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ፥ በትክክል ለመኖር ትሞክራላችሁ፥ ያ ጥሩ ነው፡ ግን ያ አይደለም። "ደሙን ባየሁ ጊዜ፡" ምልክቱ እሱ ነው። እና እዚህ ጋር ምልክቱ የለም...

204 ምክንያቱም፡ ምን፡ ትክክለኛውን ኬሚስትሪ ማየት—ነበረበት፡ ምክንያቱም ሕይወቱ ጠፍቷል፡ ከ... ከእርሱ ተወስዷል፡ እንስሳ ነበር።

205 እዚህ ላይ ግን በደሙ ውስጥ የነበረው የገዛ ህይወቱ ነበረ። ኬሚስትሪው የመቀደስ ምልክት ወይም አርማ ብቻ ነበር፡ ሆኖም ሕይወቱ ራሱ ምልክቱ ነው፥ ያለ መገረዝ፡ ያለ ምልክቱ፡ ኪዳኑ ውስጥ እንኳን የላችሁምና። ሙሉው ነገር አብሮ ይሰራል። ለቃሉ ለእርሱ ብቻ፡ እንደተገረዛችሁ ከተናገራችሁ፡ ቃሉን ታምናላችሁ፥ ቃሉን ካመናችሁ፡ ምልክቱ መምጣት አለበት፡ እንዲህ ብሏልና፡ "ንስሐ ግቡ፡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፡ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።" ይኸው ነው። ኦህ፡ ማይ!

206 ታዲያ ለተስፋይቱ-ምድር ህዝቡ ያደረገውን ዝግጅት አስተውሉ። ምን እንዳደረገ አስተውሉ። በመጀመሪያ፡ ምድርን ያዘጋጀላቸው ህዝብ ነበረው። ለእነርሱ ምድርን አዘጋጅቶላቸው ነበር። አሁንም ለተስፋይቱ-ምድር ህዝብ፡ ወደዚያ ዝግጅትን ልኳል። ይህ የተደረገው ለዚያች የተስፋ ምድር፡ ለሙሽራይቱ ቀን ቀድመው ለተወሰኑት ብቻ ነበር። አደራረጉም እንዲህ ነው፡ መልእክት ያለው ነቢይ ላከ፡ እርሱንም በእሳት ዓምድ አረጋገጠው፡ እናም ትክክል መሆኑን እርግጠኛ እንዲሆኑ ምልክት ሰጣቸው። ልክ ነው። ያ ማጽናኛዋ ነበር።

207 በዚያን ጊዜ እስራኤል፡ ከግብፅ መውጣቷ፡ ጥላ—ነበረች። ይህ ቤተክርስቲያን ከየሐይማኖት ተቋማት የመውጣቷ፡ የእውነተኛው አካል መገለጫ ነው። አሁን፡ ሁሉም ሐይማኖት አይደለም። ሙሽራይቱን ማለቴ ነው። አያችሁ? አንዳንድ ሰዎች አሉ፡ ከተቋማቱ ነፃ የሆኑት ልክ እንደ ሐይማኖት ተቋማቱ መጥፎ ናቸው፡ አንዳንዴም የባሱ ናቸው።

208 ስለተቀባው ምልክት ነው እያወራሁ ያለሁት። ምልክቱ ከእያንዳንዱ ቃል ጋር ይስማማል። አያችሁ? የግድ ነው፡ ቃሉ ነውና። በቃሉ ውስጥ የነበረው ሕይወት ነው። ኢየሱስ፡ "የእኔ ቃላት መንፈሳዊ ናቸው፥ ሕይወት ናቸው" ብሏል። አያችሁ?

209 ሙሴ በእስራኤል ውስጥ አገልግሎቱን በጀመረ ጊዜ፡ በታላላቅ ምልክቶች፡ አያችሁ፡ እስራኤል በፍጥነት ከመላው ግብፅ፡ ወደ ጌሤም ተሰበሰበች፡ ወደ ትውልድ ሰፍራቸው በመመለስ፡ ምክንያቱም የሆነ ነገር ሊፈጸም መሆኑን ያውቁ ነበርና። ኦህ፡ ምን ዓይነት ጥላ ነው!

> ኦህ፡ ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ፡
> ከሩቅ አገር ይመጣሉ፡ (ልክ ነው፡ መዝሙሩን ሰምታችኋል።)
> ከንጉሡ ጋር ለመብላት፡ እንደ እንግዳው ለመመገብ፥
> ተጓዦቹ ምንኛ ብጹአን ናቸው!
> የተቀደሰ ፊቱን የሚያዩ
> በመለኮታዊ ፍቅር የበሩ፥
> የጸጋው ተካፋዮች ብፁዓን ናቸው፡
> በዘውዱ ውስጥ እንደ እንቁዎች ያበራሉ።
>
> ኦህ፡ ኢየሱስ በቅርቡ ይመጣል፡
> ፈተናዎቻችን ያኔ ያበቃል።
> ኦህ፡ ጌታችን ይህ ጊዜ ቢመጣስ
> ከኃጢአት ነፃ ለሆኑት ሲመለስ?
> ኦህ፡ ደስታ ይሆንላችኋልን፡
> ወይስ ሀዘን እና ታላቅ ተስፋ መቁረጥ?
> ጌታችን በክብር ሲመጣ፡
> በአየር ላይ እንቀበለዋለን።

210 ምልክቱን ማሳየት! "በመጨረሻውም ቀን አስነሳዋለሁ።" በእርግጥ! እኛ በዚያ ዘመን ውስጥ ነን።

211 ህዝቡ ወደ ጌሤም ተሰበሰቡ። ተዘጋጅተው ነበር። የሆነ ነገር ሊፈጸም መሆኑን ያውቁ ነበር። ልክ እንደ...

212 ለምሳሌ ዳክዬዎች ብትወሰዱ፡ በመንጋ የሚጓዙበት ወቅት ሲመጣ፡ ሁሉም በአንድነት ይተማሉ። ንቦች፡ ሌላውም ነገር ሁሉ፡ ሲዘጋጁ፡ የሚሰባቸው የሆነ ተፈጥሮአዊ ስሜት አለ።

መንፈስ ቅዱስም ሕዝቡን ይሰባል!

213 ኦህ፡ የታላቁ የእግዚአብሔር ቁጣ የሚወርድበት ጊዜ ሲደርስ፡ እያንዳንዱ... ሁለት ዳክዬዎች መጡ፡ ተባዕትና እንስት። ሁለት ዝይዎች መጡ፡ ተባዕትና እንስት፥ እነሆ ሁለት ፈረሶች መጡ፡ ተባዕትና እንስት፥ እንዳች ነገር ነገር ይጎትታቸው ነበር፡ አስቀድሞ የተወሰኑትን። የተቀሩት ጠፉ። ኦህ! የተቀሩት ጠፉ! ዳሩ ግን ያ ወደ ውስጥ የመግባት ጉተታ የተሰማቸው፡ መርከቡ እንደተዘጋጀ ያውቁ ነበር። ዝናብ እየመጣ መሆኑን የሚያሳይ ምልክት ነበር። ሌሎች ሰዎች ያሳዩትና ያሰቡት የነበረው ምንም ቢሆን፡ ዝናብ እንደሚመጣ ያውቁ ነበር። ያውቁት ነበር።

214 በውስጣቸው፡ እንዲህ የሚላቸው የሆነ ነገር ነበር፡ “በፍጥነት፡ ወደዚያ ግቡ! ወደዚያ ግቡ፡ ምክንያቱም ደህንነት ያለው ብቸኛ ስፍራ ያ ነው።” ምክንያቱም፡ እግዚአብሔር ነቢይን አዘጋጀ፡ መርከብንም እንደ ምልክት ላከ፡ እንዲህም አለው፡ “ወደ ውስጥ ግባ፡” ዝናብም እየመጣ ነበር። እናም ልክ ጥንድ በጥንድ እየሆኑ፡ ወደዚያ ገቡ። እንስሳቱ ሁሉ፡ ጥንድ በጥንድ ሆነው፡ ወደ መርከቡ ገቡ፡ ከሥሩ ገብተው ነበርና። ሌሎቹ ምንም ይበሉ...

215 ከዚያ መርከብ ውጭ የነበሩት ሁሉ ጠፉ። ከምልክቱ፡ ከደሙ ውጭ የነበሩት፡ ሁሉ ጠፉ፡ እያንዳንዱ ሰው። አሁንም ከመንፈስ ቅዱስ ምልክት ውጭ፡ ያለ እያንዳንዱ ሰው፡ ይጠፋል።

216 የሐይማኖት ተቋም አባላት ምን ያህል ጥሩ፡ ምን ያህል ብዙ ቢሆኑም! በኖኅ ዘመንም ብዙ ነበሩ። በሙሴ ዘመንም ብዙ ነበሩ፥ ሆኖም፡ እንደ ምልክት አድርጎ፡ ደሙን ያልቀባ ሰው፡ ጠፍቷል። ወደ መርከብ ለመግባት ያልቻሉት፡ ጠፍተዋል። ወደ ክርስቶስ ለመምጣት ያልቻሉት፡ እርሱ መርከብ ነውና!

217 አንደኛ ቆሮንቶስ፡ 12 ላይ፡ “በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል” ይላል። ምሥጢራዊው፡ ቤተክርስቲያን አይደለም፥ ዳሩ ግን ምሥጢራዊው፡ የሐይማኖት ተቋማት አይደለም፥ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢራዊ አካል! “በአንድ መንፈስ፡” በትልቁ ፊደል S-p-i-r-i-t፡ መንፈስ፡ “ሁላችን ወደዚህ አንዱ አካል ተጠምቀናል።” ያኔ ምልክቱ በበሩ ላይ ነው፡ እናንተ በክርስቶስ ናችሁና። ፍርዱን የወሰደው፡ ያ አንዱ፡ የእናንተ መሰዋዕት እርሱ ነበር። እግዚአብሔርም ይህንን ሲመለከት፡ ምንም ነገር ሊያደርግ አይችልም። ሙሉ በሙሉ ደህንነታችሁ የተጠበቀ ነው፡ ምክንያቱም እግዚአብሔርና ክርስቶስ ያው አንድ-አካል ነውና፡ መንፈስ ሥጋ ሆነ በእኛም አደረ። እናም እግዚአብሔር ከገዛ ራሱ ጋር፡ እናንተም፡ የገዛ ልጆቹ፡ በአካሉ ውስጥ አላችሁ። ይኸውላችሁ፡ ኬሚካል ሳይሆን፡ መንፈስ ነው! “እልፋችኋለሁ።”

218 ከዚህ ምልክት ስር ይሆኑ ዘንድ፡ ከመላው ግብፅ ወጥተው፡ ወደዚህ አንድ ስፍራ ለመሰብሰብ መጡ።

219 ከምልክቱ ስር ለመግባት፡ ከሜቶዲስት፡ ከባፕቲስት፡ ከፕሬስቢቴሪያን፡ ከሉተራን፡ ከጴንጤቆስጤ፡ ከሌላውም ነገር ሁሉ መጥተዋል። ልክ በዚያን ጊዜ እንደነበረው!

220 በዚያ የተወከለው የእሳት ዓምድ ነበር። እና አንዱ ለሌላው ነገረው፡ ሌላው ለሌላው ነገረው፡ ሌላኛው ለሌላው ነገረው፡ እና፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይኸውላችሁ፡ እዚህ ሁሉም መምጣት ጀመሩ። መምጣት ጀመሩ፡ የእግዚአብሔርንም ምልክት ተመለከቱ። “ፍርድ ቀርቧል፡” አሉ።

221 ያኔ ነቢዩ፡ “ከእግዚአብሔር ዘንድ ሰምቻለሁ። ምልክት ይሆናል። ደሙንም በበሩ ላይ ታደርጋላችሁ። ጠቦቱን እረዱ፡ ደሙንም በበሩ ላይ አድርጉት፡ ያም ምልክት ይሆናል፡ ሞት ሊመታ ተዘጋጅቷልና” አለ።

222 ዛሬ እንደ ባርያው፡ ልንገራችሁ፡ በሩ ላይ ምልክት ካልተደረገ በስተቀር፡ መንፈሳዊ ሞት ሊመታ ነው። የሐይማኖት ተቋማት ሁሉ ተመልሰው ወ—ወደ ካውንስል፡ ወደ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል እያመሩ ነው። ሁሉም

ወደ ካቶሊክነት እየተመለሱ ነው። ከዚህ ውጭ የሚቀሩት፡ እውነተኛ፡ ዳግመኛ የተወለዱት ብቻ ናቸው!

223 አስታውሱ፡ የጴንጤቆስጤ ተቋማቶቻችሁ አይደሉም፡ ምክንያቱም ቀድመው ገብተዋልና። የሞቱ መሆናቸውን ያሳያል! ጠፍተዋል። መሰዋዕት አድርገዋል። ወደ ኋላ ተመልሰዋል። ከበሩ ውጭ አድርገውታል፡ እርሱ ግን ምልክቱን እየፈለገ ነው። ምክንያቱም፡ የተደገፉበት ብቸኛው ነገር በልሳን መናገር ነበርና።

224 በልሳን መናገርም ሆነ፡ በሌላ በምንም ነገር ላይ አትደገፉ። ነገር ግን ምልክቱ ራሱ፡ ማለትም የኢየሱስ ክርስቶስ አካል፡ የእርሱ የራሱ ሕይወት በእናንተ ውስጥ ይሁን። **ይህን፡ ያን** ብቻ አትገረዙ፥ ነገር ግን እናንተና ክርስቶስ አንድ እስክትሆኑ ድረስ፡ ሁለንተናችሁ ይገረዝ። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው፡ ሕይወቱም በእናንተ በኩል ይኖራል።

225 አሁን፡ አሁን፡ ከመላው ግብፅ! አሁን ተመልከቱ፡ እነሱ ምን እንዳደረጉ ካየን፡ ጊዜው እንደቀረበ ስናይ፡ ያንኑ ነገር እንድናደርግ ታዘዝናል። ታውቃላችሁ? ነቢዩ የተናገረውን ተመልከቱ።

226 ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ በዕብራውያን ምዕራፍ 10 ላይ፡ አሁን እናነባለን። ከእኔ ጋር ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ ከመቀጠላችን በፊት አንድ ወይም ሁለት ጥቅሶችን ማንበብ እፈልጋለሁ። ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ላይ፡ ዕብራውያን ምዕራፍ 10 ከ26ኛው ቁጥር እንጀምር። አይደለም፡ እ... እስኪ እንመልከተው። አዎን። አዎን፡ ወዳጄ! ዕብራውያን፡ 10 ኛው ምዕራፍ፡ ቁጥር 26 ነው፡ እያችሁ።

**ያን ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብንሰራ...**

227 ልክ ነኝ፡ እሰቲ እንየው? አዎን። ትክክል ነው። አዎን።

> **... የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በ... በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ፡ ከእንግዲህ ሰለ** ኃጢአት **መሥዋዕት አይቀርልንም።**
>
> የ**ሚያስፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ፡** ተቃዋሚዎችንም **ሊበላ ያለው፡ የእሳት ብርታት አለ።**
>
> ተመልከቱ! **የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ያለ ምሕረት ይሞታልና፥**
>
> ... **እንዴት፡ ይልቅ፡** የሚብስ **ቅጣት፡** የሚገባው **ይመስላችኋል፡ በእግሩ** ሥር የ**ረገጠው—— የእግዚአብሔር**ን **ልጅ የረገጠ፡ እናም... ያንንም የተቀደሰበትን...** የ**ኪዳኑን ደም... እንደ ርኩሰ ነገር፡ የቆጠረ፡ የጸጋውንም መንፈስ** ያ**ክፋፋ** እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመስላችኋል?

228 አገልጋይ፡ አባል፡ ጥሩ ሰው፡ የሞራል ሰው፡ ማንም ብትሆኑ፡ እግዚአብሔር ሲጋራን ከእናንተ እንደወሰደ ታውቃላችሁ። ሴቶች፡ እርሱ አጫጭር ቀሚሶችን፡ እና——እና አጫጭር ፀጉርን፡ እና ሁሉንም ነገር፡ ከ... እንደወሰደ ታውቃላችሁ ያንን እንዳደረገ ታውቃላችሁ። ዳሩ ግን ዘወር ብላችሁ ብታክፋፋት፡ እና ያንን የኪዳኑን ደም፡ እንደነበረው፡ “የርኩሰ ነገር” እንደሆነ ብትቆጥሩት፡ የቀደሳችሁን እና እስከዚህ ያመጣችሁን ብታክፋፋት!

229 ልክ እዚህ ድንበሩ ድረስ መጥተው፡ ተመልክተው፡ እንዲህ እንዳሉ፡ እንደ ሰላዮቹ፡ “እንግዲህ፡ ነገሩ እዚያ እንዳለ አውቃለሁ፡ ሆኖም መሰናክሉ በጣም ትልቅ ነው። እንደ አንበጣ እንመስላለን” አሉ። እነሱም በምድረ በዳ ጠፉ። የድንበር አማኞች!

230 **ይሄን** ያህል ርቀት መጥታችሁ፡ “መልእክቱን አምናለሁ፡” አትበሉ። መልእክተኛውን ታዘዙ። ወደ ክርስቶስ ኑ! “እሺ፡ የተባለውን ቃል ሁሉ አምናለሁ፡ ወንድም ብራንሃም፡” ትሉ ይሆናል። ያ ጥሩ ነው፡ ዳሩ ግን ያ—ያ ማንበብ መቻል ብቻ ነው።

231 መልእክቱን ውሰዱ፡ በልባችሁ ውስጥ አስገቡት፡ ምልክቱ ሊኖራችሁ እንደሚገባ፡ በክርስቶስ ውስጥ የነበረው ሕይወት ራሱ በእናንተ ውስጥ ሊሆን ይገባል። “ያንን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።”

232 ዛሬ በምድር ላይ ታላላቆቹን የመጨረሻው-ዘመን ምልክቶች ስናይ፡ ያ ትክክል መሆኑን እናውቃለን። አሁን ተመልከቱ፡ ይህን ጠብቄአለሁ፡ ለረጅም፡ ለረጅም ጊዜ፡ ይህን መልእክት ለእናንተ ለመስጠት። አያችሁ? የመጨረሻው-ዘመን ምልክቶች አይታችኋል። ሰብኬላችኋለሁ፡ አሳይቻችኋለሁም፡ ክርስቶስ በተናገረው ነገር ሁሉ። ልክ ነው? [ጉባኤው፡ “አሜን” አለ።—አርታዒ።] ያንን ታምናላችሁ? [“አሜን።”] በመጨረሻው ዘመን ላይ ነን። ምንም የቀረ ነገር እንዳች አላየሁም።

233 “ስለ አውሬው ምልክትስ፡” ትሉ ይሆናል? መንፈስ ቅዱስን የተቃወሙት አስቀድመው የአውሬው ምልክት ተደርጎባቸዋል። ቅጣቱ በኋላ ይመጣል። አያችሁ?

234 በእስራኤል ውስጥ፡ በኢዮቤልዩ ዓመት መለከት ሲነፋ፡ እያንዳንዱ ሰው… ክርስቶስ፡ ያንን ሲያነብ አስተውላችኋል? ግማሹን ብቻ ነው ያነበበው፡ ምክንያቱም ግማሹ ብቻ ለዚያ ጊዜ የተተገበረ ነበርና። አያችሁ? “የተሰበረ ልብ ያላቸውን እንድጠግን፡ ነፃነትን እንድሰብክ ላከኝ፡” እና ወዘተ፡ አያችሁ፡ እርሱ፡ ግን፡ “የተወደደችውንም የጌታን ዓመት።” የተቀረውን፡ ያንን—ያንን በጭራሽ አላነበበውም፥ ጥቅልሉን አስቀመጠው፡ ምክንያቱም ያ ለዚህ ዘመን ነውና። አያችሁ? ከፊሉን ብቻ አነበበ፡ ከፊሉ የእርሱ ዘመን ነበር።

235 አሁን ዛሬ ሊያደርገው ያለው ይህንኑ ነው። በቀባው መንፈሱ አማካኝነት፡ ለዛሬይቱ ቤተክርስቲያን፡ እየተናገረ ያለው ይህንኑ ነው፡ ሰዓቱ አሁን ነው። ጊዜው አሁን ነው። ሰዎች ሆይ፡ ተቀበሉት። ተቀበሉት!

236 ምንድን ነው? የምንመለከተው ታላላቆቹ የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች፡ በየቦታው፡ ቀይ መብራቶችን ሲያበሩ ነው። በተፈጥሮ ላይ፡ “ጊዜው ቀርቧል” እያለች፡ ተፈጥሮ መብራቷን ስታበራ እናያለን። መብራቱን ስታበራ፡ በቤተክርስቲያን ላይ እናየዋለን። ተኮንናለች። “ጊዜው ቀርቧል።” እርሷ በዓለም ውስጥ ናት። በ—በሰማያት፡ በባህር፡ በየአገሩ ላይ፡ በየቦታው እናየዋለን፥ በፀሐይ፡ በጨረቃ፡ በከዋክብት። ምልክቶች!

237 የመጨረሻው-ዘመን ምልክቶች መንፈስ ቅዱስ በህዝቡ ላይ ተመልሶ ሲመጣ አይተናል። በሎጥ ዘመን እንደነበረው፡ መንፈስ ቅዱስ በእዚያ የሰው ሥጋ ውስጥ እንዴት እንደሰራ፡ እርሱ በሥጋ የተገለጠው እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር በዚያን ጊዜ በ—በሙሽራይቱ ውስጥ ራሱን እንዴት ሰው

እንደሚያደርግ፡ ያንኑ ምልክት እንደሚያሳይ፡ ኢየሱስ በመጨረሻው ዘመን ያው ነገር እንደሚሆን ተናግሯል። አይተነዋል። ያንኑ የእሳት ዓምድ አይተናል። ሳይንስ እንኳን ፎቶውን አንስቶታል፡ እና ወዘተ። የመጨረሻው ዘመን ምልክቶች መቃረባቸውን አይተናል። እዚህ እንደሆነ እናውቃለን።

238 ታዲያ፡ ይህን እያያችሁ፡ እኔን ብታምኑኝ! እኔን ባታምኑኝ፡ ምልክቶቹን እመኑ፡ ቃሉን እመኑ፡ ምክንያቱም እነርሱ እኔ የምነግራችሁን ይናገራሉና። እኔ እውነትን እየነገርኳችሁ ካልሆነ፡ እነርሱ በፍጹም መልሰው አይናገሩም። እግዚአብሔር ለውሸት በፍጹም አይናገርም። እግዚአብሔር ለእውነት ይናገራል። እነዚህም ቃላት እኔ እውነትን እየነገርኳችሁ እንደሆነ እየመሰከሩ ነው። እነርሱ እኔ የምሰብከውን መልእክት የሚመሰክሩ ናቸው። እዚያ ወንዝ ዳር በዚያ ቀን፡ እንዲህ ያለኝ መላእክት ብቻ አይደለም፡ “መልእክትህ የክርስቶስን ሁለተኛ መምጣት ያበሰራል” ያለው ብቻ ሳይሆን፡ ስራዎቹ እራሳቸው! መልእኩ እውነቱን እንደተናገረ ማመን ካልቻላችሁ፡ ስራዎቹን እመኑ፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ነገሮች በመጨረሻው ዘመን እንደሚሆኑ ተናግሯል። የሚመሰክሩት እነርሱ ናቸው። ከእኔ ቃላት ወይም ከማንም ሰው ቃላት በላይ ከፍ ብለው የሚናገሩት እነርሱ ናቸው። የራሱ ቃል ነው። ስለ ጊዜው ይመሰክራሉ።

239 እነዚህን ታላላቅ፡ አስፈሪ የመጨረሻው ምልክቶች በህዝቡ ላይ፡ እና የጊዜውን ምልክቶች፡ በምድር ላይ፡ በየአገሩ መካከል ያለውን ጭንቀት እናያለን።

240 እስራኤልን በትውልድ ሀገሯ እናያታለን። ሰንደቋ፡ ባለ-ስድስት-ጠርዝ የዳዊት ኮከብ፡ የምታውለበልብ፡ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊው ሰንደቅ ያላት፡ በዓለም ላይ እጅግ ጥንታዊው ባንዲራ ያላት ናት። ሀገር ሆናለች፡ መንግስት ሆናለች፡ ከራሷ ህዝብ ናት፡ በተባበሩት መንግስታት ውስጥ ተካትታለች። እርሷ፡ እርሷ ሆናለች፡ እርሷ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ሆናለች። በተባበሩት መንግስታት ውስጥ ናት፡ የራሷ ገንዘብ አላት፡ ሁሉም ነገር አላት። ኢየሱስም፡ “ይህ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም” አለ። እናም፡ አስታውሱ፡ እስራኤል ሀገር የሆነችበት ሌሊት፡ የእግዚአብሔር መልአክ የተገለጠልኝ በዚያች ሌሊት ነው። ትክክል ነው። ሁላችንም በዚያ ነን።

241 ሁሉም ነገር በትክክል እውነትን ያመለክታል። አልዋሸኋችሁም። እውነትን ነግሬያችኋለሁ፡ እግዚአብሔርም እውነትን እንደነገርኳችሁ መስክሯል። አሁን፡ አስታውሱ፡ ወንድማችሁ ነኝ። ሰው ነኝ፡ አያችሁ። ልክ እንደ ሁላችሁም ሰው ነኝ፡ ዳሩ ግን አንድ ሰው ማምጣት አለበት፡ የሆነ ሰው መናገር አለበት። ያ የእኔ ምርጫ አልነበረም፥ የእርሱ ምርጫ ነበር። እውነትንም ነግሬያችኋለሁ፡ እርሱም እውነት እንደሆነ መልሶ መስክሯል።

242 ዛሬ እነዚህን ነገሮች በምድር ላይ ስናይ፡ ኦህ፡ ሰዎች ሆይ፡ ይህ የመጨረሻው ሰዓት ነው። ያንን ምልክት በተቻላችሁ ፍጥነት፡ በላያችሁ ላይ አድርጉ፥ ወይም፡ ወደ ምልክቱ ግቡ፡ ወደ ምልክቱ ግቡ። ታላቁን የመጨረሻ ምልክትና ጊዜው መድረሱን ስናይ፡ “ጊዜው ደርሷል፡” እያለ፡ ያስጠነቅቀናል።

243 ኦህ፡ ይህንን በቁም ነገር ውሰዱት! እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። ኦህ፡ ማይ! በጣም ልንዋደድ ይገባናል! እርስ በርሳችሁ መቼም ክፉ አትነጋገሩ።

አንድ ሰው ስህተት ቢሰራ፡ በፍጥነት ጸልዩለት። ከእግዚአብሔር ጋር፡ በዚህ ውስጥ አብረን ነን። እኛ ወንድሞችና እህቶች ነን። ኦህ፡ እግዚአብሔርን በመምሰል ኑሩ። ኑሩ፡ እንደ እግዚአብሔር ሴት ልጆች ኑሩ፡ እንደ እግዚአብሔር ወንዶች ልጆች ኑሩ። ጣፋጭ፡ ደግ፡ ትሁት ሆናችሁ ኑሩ።

244 ክፉ ነገር ወደ አእምሯችሁ፡ ወደ ሀሳባችሁ አይግባ። ዝም ብላችሁ፡ ዝም ብላችሁ አስወግዱት። በሩን ካንኳኳ፡ አባርሩት። ዝም ብላችሁ፡ ምልክታችሁን አሳዩ፡ ዝም ብላችሁ መንገዳችሁን ቀጥሉ፡ "ከደሙ ሥር ነኝ" በሉ!

245 አስታውሱ፡ በዚያች ሌሊት፡ ብዙዎቹ ወደ እነዚያ ሴቶች ዘንድ መጥተው፡ "ሄይ፡ ገርቲ፡ ሊሊ፡ እንዳንዶቻችሁ፡ ኑ ውጡ፡ ዛሬ ማታ ወደ ፓርቲ እንሂድ" ይሉ ነበር።

246 "ኧ-ኧ! ከደሙ ሥር ነኝ። እዚሁ ለመቆየት፡ ከምልክቱ ሥር ነኝ። ፍቅሬ ለፈጣሪዬ ነው። ዛሬ ማታ በምድሪቱ ላይ ሞት አለ።"

247 ዛሬ በምድሪቱ ላይ ሞት አለ። ፍርድ እየጠበቀ ነው፡ ተደቅኗል። አቶሚክ፡ ሃይድሮጂን፡ እንዲሁም ሁሉም ዓይነት ጥፋት፡ አሕዛብን እየጠበቀ ነው።

248 እግዚአብሔርም ቤተክርስቲያኑን እያንቀሳቀሰ ነው፡ ሁሉንም አሳይቷል። አሁን ለተወሰነ ጊዜ፡ ጠቦቱን ስንጠብቅ ቆይተናል፡ ምን እያደረገ እንዳለ እያየን፡ ተፈጥሮውንና ሁሉንም ነገር እየተከታተልን፡ ነገር ግን አሁን ምልክቱ መቀባይ አለበት። መቀባት አለበት። ብቸኛው ነገር ይህ ነው። "ሰው ከመንፈስና፡ ከውኃ ካልተወለደ በቀር፡ ከቶ ሊገባ አይችልም።" እርስ በርሳችንም ልንዋደድ ይገባናል። አማኞች ራሳቸውን ከዓለም መለየት አለባቸው። አሁን ዝም ብላችሁ አቅልላችሁ አትውሰዱት።

249 አሁን፡ ይህንን፡ በቴፕ የምትሰሙ ሰዎች፡ እናንተ ሴቶች፡ እናንተ ወንዶች፡ ለአንድ ደቂቃ አድምጡ። መቼም ቢሆን አምናችሁኝ የምታውቁ ከሆነ፡ አሁን ይህንን እመኑ።

250 እርስ በርሳችሁ መነታረክን የምታቆሙበት ጊዜ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን መልእክት እመኑ! ኢየሱስ ክርስቶስን እመኑ! እርስ በርሳችሁም ተዋደዱ፡ ክብር ስጡ፡ ተከባበሩም። ወንዶች ሚስቶቻችሁን አክብሩ። ቤቶቻችሁን አክብሩ። ቤተሰባችሁን በአንድነት ሰብስቡ፡ ምክንያቱም፡ አስታውሱ፡ ይህ ጠቦት ለቤተሰብ ነበር፡ ለአንድ ሰው ብቻ አልነበረም፥ መላው፡ ቤተሰብም፡ መቅረብ ነበረበት። ሁሉም ነገር ወደ ውስጥ መግባት ነበረበት። እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል። አማኞችም ራሳቸውን ከዓለም መለየት አለባቸው።

251 ልብ በሉ፡ ስለ መልእክቱ ለማውራት ብቻ በአንድ ላይ አልተሰበሰቡም ነበር። የተሰበሰቡት ደሙን ለመቀባት፡ ምልክቱን ለመቀባት ነበር።

252 ማድረግ ያለባችሁ ይህንኑ ነው። ፓስተር ኔቪል፡ እንዲሁም ለዚህ ጉባኤ፡ ባለአደራዎች፡ ዲያቆናት፡ ለእናንተ ወንድሞች፡ የዓለምን ሞኝነት ሁሉ ወደ ጎን የምንተውበት ጊዜ ነው፡ ሌላውንም ነገር ሁሉ ወደ ጎን የምንተውበት ጊዜ ነው። አሁን እርግጠኞች፡ አዎንታዊ እስክንሆን ድረስ፡ በቂ አይተናል። ምልክቱም መቀባት አለበት። ያለ እርሱ፡ ትጠፋላችሁ፥ መጥፋታችሁ አይቀርም፡ በቃ ይኸው ነው።

253 ኦህ፡ በአንድ ላይ ተሰብሰባችሁ፡ “እምናለሁ፡” ብቻ አትበሉ። ከሰሩ ግቡ፡ ወደ ውስጡ ግቡ! [የፐብሊክ አጭር-ሞገድ ሬዲዮ ስርጭት ጣልቃ ገብነት ተሰማ—አርታዒ።] እንዴት እናደርገዋለን? “በአንድ መንፈስ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ አካል እንጠመቃለን።” እያንዳንዱ ሰው፡ በሙሉ ልባችሁ እመኑ። አያችሁ? ከእርሱ ሥር ላልሆኑት ሁሉ እርሱ ተጠያቂ አልነበረም።

254 የተናገረው ማን ነበር? [አንድ ሰው፡ “ያ አጭር-ሞገድ ሬዲዮ ነው፡ ወንድም ብራንሃም” አለ።—አርታዒ።] ከላይ የመጣ አጭር-ሞገድ ነው? [“በድምጽ ማጉያው በኩል የመጣ ነው።”] በድምጽ ማጉያው በኩል። እዚያ ውስጥ አግኝተውታል? የሆነ ሰው ሰምቻለሁ። [“ወንድም ብራንሃም፡ ከኋላ የመጣ አጭር-ሞገድ ይመስለኛል።”] አጭር-ሞገድ፡ አዎን። ኧሃ፡ መስመር ላይ—አስገብተውት ነው። እንደሚመስለኝ... ኦህ፡ ከመኪኖቹ ነው? ይቅርታ። አንድ ሰው የሆነ ነገር እንደተናገረ አውቃለሁ። እናም ሰውየው የሆነ ነገር ሊነግረኝ የፈለገ መሰሎኝ ነበር፡ እነርሱም አልገባቸውም፡ አያችሁ፡ ያንን ያ—ያልኩበት ምክንያት ያ ነው። ዙሪያችሁን ስትመለከቱ አየኋችሁ። ድምጽ ሰማሁ። አንድ ሰው የሆነ ነገር ለመናገር የተነሳ መሰሎኝ ነበር፡ ምን እንደነበረም አላወቅሁም። አሁን፡ አሁን፡ አመሰግናለሁ።

ነገር ግን፡ እመኑ፡ ከሥሩ ግቡ!

255 እስራኤላውያን፡ እንዲህ ለማለት አንድ ላይ አልተሰበሰቡም፡ “ዛሬ ሁላችንም ወደ ጌሤም እንሂድ። ወደ ጌሤም እንሂድ። አንተ ግመልህ ላይ ውጣ፡ እኛም የበሬ ጋሪ እንይዛለን። እነ ጆንሶችን፡ ከዚህ እኛ እንወስዳቸዋለን፡ ወዘተ፡ እንዲሁም—እንዲሁም እነ ጎልድበርግ፡ ሁላችንም ወደ—ወደ ጌሤም እንውጣ። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሙሴ ዛሬ ይሰብካል።” ያ አልነበረም። አይደለም፡ ጌታዬ፡ ወንድሜ! ጉዳዩ፡ ከደሙ ሥር ግባ ነው! አዎ፡ በእርግጥ።

ስለ እርሱ ማውራት አይደለም፥ ወደ ውስጡ መግባት ነው!

256 እንዳቸው፡ “ታውቃለህ፡ ሚስተር ጎልድበርግ፡ ያ በእርግጥ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ” ይላል።

257 “አዎ፡ ወንድሜ፡ ይህ እውነት እንደሆነ እምናለሁ። ይህ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።”

“ሚስተር ላቪንስኪ፡ ስለዚሁ ምን ታስባለህ? ”

258 “ይህ ፍጹም እውነት ነው! የይሖዋ አምላክ ኃይል ሲናገር አይቻለሁ። እነዚያ እንቁራሪቶች ከምድሪቱ ሲወጡ አይቻለሁ። እርሱ እስኪናገር ድረስ እንዳልተከሰተ አውቃለሁ፡ ይህ ይሖዋ አምላክ እንደሆነ አውቃለሁ።” አሁን፡ ይህ ሁሉ ጥሩ ነው።

“ተገርዘሃል? ”

“አዎን፡ ወዳጄ!”

“አማኝ ነህ? ”

“አዎን፡ ወዳጄ!”

259 ከዚያም በዚያ ቀን፡ ፓስተር ሙሴ ሲናገር በሰማ ጊዜ፡ እንዲህ አለ፡ “ሆኖም ከዚያ ደም በታች መግባት አለባችሁ፡ ምክንያቱም እግዚአብሔር፡

‘ደሙ ምልክት ነው’ ብሏልና። እርሱ ምልክት ነው! ምንም ያህል ብታምኑ፡ ምንም ያህል ብትገረዙ፥ ያ እግዚአብሔር ለአብርሃም የሰጠው ቃል ኪዳን ነው፡ ወዘተ፡ ያ ቃል ኪዳን ነው። ነገር ግን በደም ሥር መሆን አለባችሁ፡ ምልክት ነው፡ እርሱም፡ ‘ደሙን ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ’ ብሎ ተናግሯልና። እስራኤል፡ ወይም ሌላ ነገር!”

260 የሐይማኖት ተቋም ይሁን የሐይማኖት ተቋም አይሁን፡ የትኛውም ቢሆን፡ ከደሙ ሥር መግባት አለባችሁ። ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሬስቢቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤ፡ ከሐይማኖት ተቋም ውጭ፡ የትኛውም ብትሆኑ፡ ይህ ለግለሰብ ነው። ከደሙ ሥር መግባት አለባችሁ። አሁን ስለ እርሱ ብቻ እታውሩ፥ ተቀበሉት! ስሙኝ! ስሙኝ! በጌታ ስም፡ ስሙኝ! አያችሁ? ከደሙ ሥር መግባት አለባችሁ!

261 ከደሙ ሥር ላልሆነ ለማንኛውም ሰው እርሱ ተጠያቂ አልነበረም። እግዚአብሔር ከዚያ ደም ሥር ያልሆኑት ሁሉ እንደሚጠፉ ግልጽ አድርጎ ነበር።

262 የእርሱን ቃላት ልጠቀም? ከክርስቶስ ውጭ ያሉ ሁሉ ይጠፋሉ። ወደ ክርስቶስ እንዴት ትገባላችሁ? በአንደኛ ቆሮንቶስ 12 መሰረት፡ “በአንድ መንፈስ!”

263 “በአንድ እጅ መጨባበጥ፡ በአንድ አባልነት፡ በአንድ የሐይማኖት ተቋም፡” አይደለም። ለማድረግ እየሞከሩ ያሉት ይህንን ነው። ያንን ያድርጉ።

264 “በአንድ መንፈስ ግን ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል።” “ከሰማይ የመጣ መልአክም ሌላ ነገር ቢያስተምር፡” ጳውሎስ፡ “የተረገመ ይሁን” ብሏል። መልእክቱ ይህ ነው፡ ወደ ክርስቶስ የመጣ ነው!

265 ተመልከቱ፡ ከምልክቱ ውጭ ላሉት ለማናቸውም ሰዎች፡ እግዚአብሔር ተጠያቂ አልነበረም። እግዚአብሔርም ለማንኛውም ሰው ተጠያቂ አይደለም፡ ትልቅም ይሁን ትንሽ፡ ታዋቂም ይሁን ያልታወቀ፡ ሀብታምም ይሁን ድሃ፡ ባሪያም ይሁን ነጻ፡ ወንድም ይሁን ሴት፥ ከምልክቱ ቃል ኪዳን ሥር ላልሆነ ለማንም ተጠያቂ አይደለም። እርሱ ተጠያቂ አይደለም።

266 እናንተ፡ “ነገር ግን፡ ጌታ ሆይ፡ **ይህንን** አድርጌያለሁ። አጋንንትን አውጥቻለሁ። ጌታ ሆይ፡ **ይህንን** አድርጌያለሁ። ወንጌልን ሰ—ሰብኬያለሁ” ትላላችሁ።

267 “እናንተ አመጸኞች፡ ከእኔ ራቁ። ከቶ አላውቃችሁም።” እርሱ የሚቀበለው ምልክቱን ብቻ ነው።

268 ሰምታችሁታል? “አሜን፡” በሉ። [ጉባኤው “አሜን!” አለ።—እርታዒ።] አሁን፡ ስለዚህ ጉዳዩ በእናንተ ላይ ነው። እርሱ…

269 ባለፈው ቀን እዚህ ጫካ ውስጥ ተቀምጬ፡ ልጆቹም ተገርመው፡ “ይኸው ሁለት ቀን ሆነህ፡ አንተ ምንም የለም… ” አሉ። አንድም ሽኮኮ እንኳን አልመታሁም ነበር። “ምን ሆነህ ነው፡” አሉ? አያችሁ፡ ነገሩ ያ ነበር። አያችሁ?

270 እርሱም፡ “በእነርሱ ላይ ቀባው፡ በእነርሱ ላይ ቀባው።” አክሎም፡ “ስለዚህ ጉዳይ ከእኔ ጋር—ተነጋግረሃል” አለ። አያችሁ? አሁን ኃላፊነቱ በእናንተ ጭን ላይ ወድቋል። በእናንተ እጅ ነው።

271 እርሱ ከዚያ የመንፈስ ቅዱስ ቃል ኪዳን በቀር፡ ለምንም ነገር ዕውቅና አይሰጥም። ድናችሁ፡ ተቀድሳችሁ፡ ከዚያም ወደ አካሉ ካልተጠመቃችሁ በቀር ያንን ቃል ኪዳን ልትቀበሉ አትችሉም። እርሱ አያደርገውም።

272 ማስመሰል ሊኖራችሁ ይችላል፡ ጥሩ ስሜት ሊሰማችሁ፡ **ላይ-እና-ታች** ልትዘሉ፡ በልሳን ልትናገሩ፡ በመንፈስም ልትጨፍሩ ትችላላችሁ። ይህ ከእርሱ ጋር አንዲትም ግንኙነት የለውም። በጌታ ስም፡ ይህንን ስሙ! እግዚአብሔር ለዚያ ዕውቅና አይሰጥም። ያንን አረማውያንም ያደርጉታል። ጠንቋዮችም ያደርጉታልና።

273 "ምሁር ነኝ። **ይህንን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላውን፡** አደርጋለሁ" ትሉ ይሆናል። እርሱ ምን ያህል ምሁር እንደሆናችሁ ግድ የለውም። ዲያቢሎስም፡ ምሁር ነው፡ አያችሁ።

274 እሱ እውቅና የሚሰጠው—ምልክቱን ብቻ ነው። ያም የዘመኑ መልእክት ነው! ይህ የዘመኑ መልእክት ነው! የዚህ ዘመን መልእክት ይህ ነው! በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ተቀበሉት!

275 የሆነ ዓይነት ም-... ምትክ፡ ዲያብሎስ የሚጭንባችሁ ነገር አይደለም፥ እንደ ሐሰተኛ ፍቅር፡ በሚስቱ ላይ ሌላ ሚስት እንደሚያፈቅር ሰው፡ ወይም ሌላ እንደምታፈቅር ሚስት፡ ወይም እንደነዚህ አይነቶች፡ የረከሱ ነገሮች አይደለም። እውነተኛ ፍቅር ያ አይደለም። ያ'ማ ዲያቢሎስ ነው። ሥራውም ይህ ነው። ከዚህ ይልቅ፡ እርሱ በእጃችሁ ሊሰጣችሁ የሞከረው ነገር ነው፥ ደስታ፡ ጠጥቶ በመሰከር ጥሩ ስሜት መሰማት፡ ከዚያም፡ "ድብርት ተሰምቶኛል፥ ወጥቼ መጠጥ እጠጣለሁ፡ እረሳዋለሁም።" ያ ሞት ነው።

276 እግዚአብሔር ደስታችሁ ነው። እግዚአብሔር ብርታታችሁ ነው። መልእክቱን ማወቅ፡ እውነትን ማወቅ፡ ያ አሁን መብቃታችን ነው። እርሱ ሁሉን-ቻይነቴ ነው። በርሱ ውስጥ፡ የሚያስፈልገኝ ነገር ሁሉ በርሱ ውስጥ ነው። ያ ብርታታችን ነው። "ረድኤቴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይመጣል።" እናንተ ክርስቲያኖች፡ ለደስታችሁ እርሱን ተመልከቱ፡ ለብርታታችሁ እርሱን ተመልከቱ፡ ለሀሴታችሁ እርሱን ተመልከቱ። እርሱ ሰላሜ ነው። እርሱ ደስታዬ ነው። እርሱ ፍቅሬ ነው። እርሱ ህይወቴ ነው። ያም ኪዳን ነው፡ በበሩ ላይ ያለው ምልክት!

277 ለአንድ ሰው፡ ለአንድ ሰው እንኳ ተጠያቂ አይደለም፡ ማንም ብትሆኑ፡ ከሥሩ ውጪ ከሆናችሁ፡ እርሱ ተጠያቂ አይደለም።

278 አስታውሱ፡ ቤተሰቡ በሙሉ፡ መሰብሰብ ነበረበት። ኦህ፡ ማይ! ኦህ፡ አስታውሱ!

279 እንዲህ ትላላችሁ፡ "እንዴ፡ የእኔ አባት ሰባኪ ነው። ወንድሜ! ፓስተሬ! የእኔ እከሌ... " ምናልባት፡ ያም እውነት ሊሆን ይችላል፡ ግን አንተስ?

280 አስታውሱ፡ ደህንነት የሚኖረው ምልክቱ ሲታይ ብቻ ነው! አንድ ሰው **እዚህ** ከሥር ሆኖ፡ ልጁ ደግሞ መንገድ ማዶ ቢሆን፡ ልጁ አደጋ ውስጥ ነው፡ ይጠፋልም። አባቱ ይድናል። ወይም፡ ልጁ **እዚህ** ቢሆን፡ አባቱ ደግሞ እዚያ ቢሆን፡ አባቱ ይጠፋል። ምልክቱ ብቻ ነው! "ምልክቱን ሳይ፡ አልፋችኋለሁ።" ብቸኛው ነገር ይህ ነው።

281 እናንተም፡ "እንግዲህ፡ ልጄ ሰባኪ ነው።" እናንተ እናቶች፡ "ምርጥ ወንድ ልጅ አለኝ፡" ወይም "ምርጥ ሴት ልጅ አለችኝ። እላችኋለሁ፡ እነርሱ በጣም ግሩሞች ናቸው። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተዋል፡ እንደዚህ ያለ ፍቅርም አላቸው! ታዛዦች ናቸው። እንደዚህ ያለ አይቼ አላውቅም" ትላላችሁ! እማማ፡ እርሶስ?

282 እናንተ፡ "እናቴ በጣም ግሩም ናት። ብትሞት፡ ወደ መንግስተ ሰማያት እንደምትሄድ፡ አውቃለሁ፡ ምክንያቱም በእውነት ምልክቱን አግኝታለች፡ ወንድም ብራንሀም።" ነገር ግን እህቴ፡ አንቺስ? መላው ቤተሰብ ከሥሩ መግባት አለበት።

283 ደከማችሁ'ዴ? [ጉባኤው፡ "አይ" አለ።—አርታዒ።] እ... አሰራ ሁለት ሰዓት ነው... አንድ ደቂቃ ብቻ። አቋርጬ ዛሬ ማታ እንደገና ልጀምር እችላለሁ። ["አይ።"] ነገር ግን ትንሽ—ትንሽ መቆየት ከፈለጋችሁ፡ አሁን ላፈጥን እሞክራለሁ። ["አሜን።"] ይህንን በትክክል እቋጨዋለሁ፡ ምክንያቱም አሁን በቅባቱ ስር ሳላችሁ፡ ይህንኑ አሁኑኑ ብታገኙት የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

284 ምልክቱ ሲታይ ብቻ ነው! ስለዚህ፡ መላው ቤተሰብ በዚያ ምልክት፡ በደሙ ሥር መሆን አለበት። አባባና እማማ፡ ምን እንደሚሰማችሁ አውቃለሁ። እኔም፡ ልጆች አሉኝ፡ ሲድኑ ማየት እፈልጋለሁ። ዛሬ ለራሴም እየተናገርኩ ነው። አያችሁ? ወንድሞች አሉኝ። እህት አለችኝ። የምወዳቸው ሰዎች አሉኝ። እ— እነሱም፡ ሲድኑ ማየት እፈልጋለሁ። ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ ምልክቱ ካልታየ፡ ይጠፋሉ። ለእነርሱ ትንሳኤ የለም። ልክ ነው። ጠፍተዋል። ምልክቱ ሲታይ ብቻ ነው!

285 ተመልከቱ፡ ኢያሱን፡ ለማንበብ ጊዜ ቢኖረን ጥሩ ነበር። ጻፉት፡ ኢያሱ ምዕራፍ 2 ላይ፥ ያመነችው አህዛብ ጋለሞታይቱ፡ ረዓብ።

286 ኦህ፡ ሰዓቱ ገና ዘጠኝ ሰዓት በሆነ ብዬ እመኛለሁ። ያንን ወሰጄ—ወሰጄ እንዴት በዚያ እንደነበረ ላሳያችሁ እፈልግ ነበር፡ አያችሁ።

287 ይህቺ ጋለሞታ፡ አህዛብ ነበረች፡ ተመልከቱ፡ ቤተሰቧን በሙሉ። አማኝ ነበረች። ቤተሰቧ በሙሉ በዚያች ቀይ ገመድ፡ በዚያ ምልክት ሥር መግባት ተገባው። ከሥሩ መግባት ነበረባቸው፡ አለበለዚያ ይጠፉ ነበር። ስለ እግዚአብሔር ቁጣ ሰምተው ነበር። በህዝቡ መካከል ስለታዩት የእግዚአብሔር ምልክቶችና ተአምራት ሰምተው ነበር፡ ሊቀበሉትም ግድ ነበር። እርሷ ልትቀበለው ግድ ነበር። አጥፊው መልአክ፡ እግዚአብሔር፡ እየመጣ ነበር። አውቀውት ነበር። ያ መልአክም ኢያሱ ነበር። ደጃፍ ላይ ነበሩ።

288 በዓለም ላይ ያለ እያንዳንዱ አገርም እንዲሁ፡ በእግዚአብሔር ፍርድ ደጃፍ!

289 ይህቺ ትንሽ፡ ጋለሞታ፡ ሰምታ ነበር። እምነት ከመስማት ይመጣል! "አገሩ ሁሉ በእናንተ ምክንያት ታውኳል፡" አለች። ልክ ነው።

290 አሁን፡ ሁኔታዎችን ለማመቻቸትና፡ ለመሳሰሉት ወደዚያ የተላኩትን ሰላዮች፡ እነዚያን ሰዎች አከበረቻቸው። እናም፡ እሷ፡ ለመዳንም ፈለገች። እንዲህ አለች፡ "አምላካችሁ አምላክ እንደሆነ አውቃለሁ፡ ያደረጋቸውን ታላላቅ ነገሮችም ሰምቻለሁ። በዐግ ላይ ያደረገውን አውቃለሁ፡ በተለያዩ ወገኖች ላይ ያደረገውን አውቃለሁ። እርሱን የሚቀበሉ እንደሚድኑ፡ እርሱን የማይቀበሉ

ደግሞ እንደሚጠፉ አይቻለሁ። በህይወት መኖር እፈልጋለሁ፡” አለች። ኦህ፡ ማይ! ይኸውላችሁ። “በህይወት መኖር እፈልጋለሁ።” ምክንያቱም እነርሱ...

291 ልብ በሉ፡ እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ኢያሪኮ ሰምታ ነበር፡ ነገር ግን ማስጠንቀቂያውን መቀበል አልፈለገችም።

292 በዚህ አገር ዙሪያም፡ እግዚአብሔር እያደረገ ያለውን ያልሰማ የሐይማኖት ተቋም፡ የለም። ማስጠንቀቂያውን መቀበል ግን አይፈልጉም።

293 ታላቅ ኃይሉና ምልክቶቹ ታይተዋል። ምን አደረገ፡ በደረቅ መሬት ላይ እንደሚራመድ፡ ቀይ ባሕርን ተሻግሯል። ነገሮችንም ፈጠረ፡ እንቁራሪቶች፡ ቅማሎች፡ እንዲሁም ቁንጫዎች፡ በአየር ላይ እንዲመጡ አደረገ፥ በነቢዩ በኩል፡ በቃሉ ፈጠራቸው። ይህም ሚስጥር አልነበረም። ያውቁት ነበር።

294 ረዓብም እንዲህ አለች፡ “ያንን ሰምቻለሁ። ከእነዚህ የማያምኑ ጋር መጥፋት አልፈልግም። ኧረ፡ በፍጹም!” እነርሱ የፍርድ ኢላማ ውስጥ ስለነበሩ፡ ፍርድ እንደሚከተል ታውቅ ነበር። አውቃዋለች። ስለዚህም፡ የምታመልጥበትን መንገድ አዘጋጁላት።

295 ትልቋ የሐይማኖት ተቋማቸው የሆነችው ኢያሪኮ የእግዚአብሔርን ቁጣ መቋቋም እንደምትችል አምነው መሆን አለበት፡ አያችሁ፡ ትልቋ የሐይማኖት ተቋማቸው።

296 ዛሬ ብዙዎቹ የሚያስቡት ያ ነው። “ኦህ፡ በእርግጥም እግዚአብሔር ያንን አያደርግም።” ሰይጣን ለሔዋን የነገራት ይህንኑ ነው። “ኦህ፡ በእርግጥ እግዚአብሔር አያደርግም።” ያደርጋል፡ አደርገዋለሁ ብሏል፡ አያችሁ፡ ያ ቃሉ ነው። አዎን፡ ወዳጄ።

297 “ሰው ካልተወለደ በቀር!” “የተወለዱትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሏቸዋል!” አያችሁ? “ደቀ መዛሙርቴ እንደሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ” ወዘተ፡ አያችሁ። እሺ፡ ማድረግ ፈልጌ ነበር። ኦህ!

298 ምን ተፈጠረ? አሁን በሮቻቸውን ዘጋግተዋል። “እዚህ ምንም ዓይነት ሪቫይቫል አይደረግም። የሐይማኖት ተቋማችን እንደዚህ ዓይነቱን ነገር አይደግፍም። በመካከላችን እንዲህ ዓይነት ከንቱ ነገር አይኖርም። ማናችሁም ወደዚያ ሰብሰባ እንዳትሄዱ እከለክላለሁ።” ሃ! ኢያሪኮ፡ ልክ በጥፋት ኢላማ ውስጥ!

299 ሆኖም አስቀድሞ ለተወሰነው ዘር፡ ቴፕ የሚያጫውቱ ወንዶች የሆነ ቦታ ሾልከው ገብተው ነበር። ወደ ቤቷ ሾልከው በመግባት አንዳንድ ቴፖችን አጫወቱላት። እርሷም መልእክቱን ለመቀበል፡ ቤቷን—ቤተክርስቲያን አደረገች።

300 አሁንም ደርሷቸዋል፡ ታውቃላችሁ። መልእክቱ፡ አስቀድሞ ለተወሰነው ዘር እንደምንም ሆኖ ደርሷል። እንዴት እዚያ እንደደረሰ አናውቅም፡ ነገር ግን ጻድቃን ከኃጢአተኞች ጋር እንዳይጠፉ፡ እዚያ ደርሷል። እግዚአብሔር፡ ዛሬም ይህንን እያየው ነው። አዎ፡ በሆነ መንገድ ሾልኮ ይገባል። እንዴት እንደሆነ አናውቅም። እነዚያ ምንም እንኳን ባይደግፉትም፡ አስቀድሞ የተወሰነው የሆነ ዘር ግን እዚያ አለ።

301 ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያውቅ ማንኛውም ሰው፡ ጋለሞታዋ አስቀድማ የተወሰነች እንደነበረች ያውቃል። በእርግጥም ነበረች! እርሷ ግን... መጽሐፍ ቅዱስ፡ “እርሷ ከማያምኑት ጋር አልጠፋችም” ይላል። ልክ ነው። እሷ ግን የዘመኑን መልእክት አመነች።

302 እግዚአብሔርም በመልእክተኞቹ በኩል፡ ምልክት ሰጣት። እንዲህ አለ፡ “ቀይ፡ የደም ግምጃ ወሰደሽ እሰሪ... ” አለ፡ “አስታውሺ፡ ያንን ግምጃ እዚያ ካላሰርሽው፡ ወይም እኛ ያመለጠንበትን፡ ያንን ነገር እዚያ ካልተውሽው፡ ለመሓላችን ተጠያቂ አይደለንም።” በተጨማሪም፡ “ከሥሩ ከወጣሽ፡ ተጠያቂ አይደለንም።” ኦህ፡ ማይ! “ረዓብ ሆይ፡ በአካባቢው ያለውን አስቀድሞ የተወሰነውን ዘር በሙሉ፡ ውጪና ፈልጊያቸው። አባትሽን፡ እናትሽን ሁሉ አምጪ! ምክንያቱም፡ እኛ በዚያ ሰርየት ሰር ሆነን፡ ከግብፅ፡ ወጥተናል፡ በዚያም ምልክት ሥር ያልነበረው ሁሉ ጠፍቷል። ረዓብ፡ ምልክት እየሰጠሁሽ ነው። ምልክት ነው። እነሆም፡ በጌታ ስም፡ እላለሁ፡ ያንን ብታደርጊ! ያንን ከመልእክተኛው ጋር፡ አውቀዋለሁ። የቁጣውን መልአክ ኢያሱን፡ አውቀዋለሁ። እርሱ የእግዚአብሔር አጥፊ መልእክተኛ ነው። እርሱን አውቀዋለሁ፡ የዓላማ ምልክት መኖር እንዳለበትም ያውቃል። ያንን እዚያ እንጠልጥዪው፡ አረጋግጥልሻለሁም። እምላለሁ።” እግዚአብሔርም፡ ደግሞ፡ ከእርሱ ውጭ ያለው ሁሉ እንደሚጠፋ፡ በእርሱ ሰር የነበረው ሁሉ ደግሞ በህይወት እንደሚኖር መሐላ አድርጓል።

303 አሁን፡ ዛሬም ያው መሐላ ነው፡ ያው ነገር፡ አያችሁ፡ “መልእክቱን ከማያምኑ ጋር አብራችሁ እንድትጠፉ አልፈቅድም።” እነርሱም...

304 ሰራዎቹ እንደተሰሩ ሰምታ ነበር፡ አመነችውም። ነገር ግን፡ ስለ፡ እርሷ... በመላው ከተማ ውስጥ ያመኑት፡ እርሷ፡ አባቷ፡ ጥቂት ወንድሞቿ፡ ወይም የመሳሰሉት ብቻ ነበሩ።

305 ምን ያህል ጥቂት እንደሆነ አያችሁ? **እዚህና እዚያ፡** አንድ ብቻ ከአንድ ክፍለ ሀገር አንዲት ትንሽ ቤተሰብ ትወጣለች። ልክ ነው? እውነት ነው፡ አሁን የምንናገረው እውነታ ነው። እኛ... ፍጻሜው ምን እንደሆነ ማየት ከፈለጋችሁ፡ መጀመሪያ ጥላው ምን እንደነበረ ማየት አለባችሁ። ጥላው ምን እንደሆነ ማየት አለባችሁ፡ ከዚያ እውነተኛው ነገር ምን እንደሚመስል ታውቃላችሁ። አያችሁ?

306 ኃይሉ ታይቷል። ፍርድ ደጃፍ ላይ ነው። ለመዳን፡ ማመን አለባቸው። አዎ፡ ጌታዬ። እነዚህም ትናንሽ...

307 እነዚህ ሰዎች ወደዚያ ገቡ፡ እነዚህ መልእክተኞች፡ ያመነውንም—ያንን አስቀድሞ የተወሰነውን ዘር ወሰዱ። እነዚህን መልእክተኞች ለመቀበል፡ ቤቷን እንደ ቤተክርስቲያን ተጠቀመች። በእነዚያ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ እያስገባቻቸውም ነበር። የለም፡ ጌታዬ። አያችሁ? ስለዚህ እርሷ...

308 እናንተንም፡ እያስገባችሁም። ስለ እርሱ ምንም ብትናገሩ ያባርሯችኋል። አዎ። አያችሁ?

በከተማዋ፡ ያመኑትን ሁሉ፡ ከምልክቱ ሥር አደረጓቸው።

309 ዛሬ ብናደርግ የሚሻለው ልክ ያንን ነው። የምትወዱት ሰው እንዲድን ከፈለጋችሁ፡ አሁኑኑ ወደ ውስጥ ብታስገቧቸው ይሻላል። አያችሁ?

310 የእግዚአብሔር ቁጣ ያችን ትልቅ ከተማ ሲያጠፋ፡ የሰንደቁ ምልክት ቤቷን በደህና ጠበቀው። አሜን። ለምን? ሰንደቁ ምልክቷ ላይ ነበር... ወይም፡ የተቀረው ከተማ ፈርሶ መሬት ሲደባለቅ፡ ምልክቱ በቤቷ ላይ ነበር። ምን ነበር? ምን ነበር? የጌታ መልእክተኛ፡ ኢያሱ! እግዚአብሔር ራሱ የመልእክተኛውን መልእክት ተቀበለው። አሜን! አረጋገጠው። አረጋገጠው። እነርሱ መልእክቱን ተቀበሉ። እርሱ የመልእክተኛውን መልእክት ተቀበለው። የተቀረው ከተማ ሁሉ ሲፈርስ፡ የረዓብ ቀይ ምልክት በበሩ ላይ ቆሞ ነበር፡ የተቀሩትም ሁሉ ጠፍተው ነበር።

311 ከዚያም፡ አጥፊ መላእክት ቀጥ ብለው ወጡና በከተማዋ ያለውን ሁሉ አጠፉ፡ አንድም የዕቃ ቁራጭ አልቀረም። አንዱ አንድ ዕቃ አወጣ፡ ከዚያ የሐይማኖት ተቋም በሰተውጭ፡ ከያዘአው ጋር መጥፋት ነበረበት። ሁሉንም ነገር ወስዶ አጠፋው! “እርሷን ለመገንባት የሚሞክር ሰው የተረገመ ይሁን። ሲጀምር የበኩር ልጁ ይሞታል፡” የመሳሰሉትም። እግዚአብሔር እንዲህ ረገማት፡ የናቁት ያንን ትልቅ ነገር-... የጸጋና የምሕረት መልእክትን ንቀው፡ ደህንነታቸው የተጠበቁ ይመስላቸው ነበር።

312 ዛሬ፡ ብዙ ሰዎች፡ “የቤተ ክርስቲያን አባል መሆኔ፡ ደህንነቴ የተጠበቀ ነው” ብለው ያስባሉ። እንደዚህ ያለ ከንቱ ነገር አትመኑ።

313 እንግዲህ፡ “ደሙ ምልክት ይሆንላችኋል።” አሁን ምልክታችሁ መንፈሱ ነው፡ ይህም በደሙ ውስጥ የነበረው ሕይወት ነው።

314 ያው፡ በግብፅ የተጠቀሙበትን ያንን ምልክት፡ እናስብ፡ በግብፅ የነበረው፡ ያው የሕይወት ምልክት፡ እግዚአብሔር ያንኑ ምሳሌ እዚያ ተጠቅሟል። የኢየሱስ ፍጹም ጥላ የሆነው፡ ኢያሱ፡ መልእክተኞቹ ለሰበኩት የምልክት ማረጋገጫ ታማኝ ነበር። ኢያሱ፡ ያንን ሲናገር፡ እንዲህ አለ፡ “ያንን ቤት ወይም በውስጡ ያለውን ማንኛውንም ነገር እንዳትነኩ። እርሱ ለጌታ የተጠበቀ ነው።” አሜን!

315 ከአሕዛብ የሆነች፡ ጋለሞታ፡ የመንገድ ላይ አዳሪ፡ ነገር ግን ሰምታ አመነች፡ ምልክቱንም ተግባራዊ አደረገች።

316 ምንም እንኳን በኃጢአት ብትወድቁም፡ ያደረጋችሁት ምንም ቢሆን፡ ከእርሱ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። ምልክቱን ተቀበሉ። ለእናንተ ነው። በልባችሁ ውስጥ የሆነ ነገር እንደሆነ ከተሰማችሁ፡ እርሱ ለእናንተ ነው። ምልክቱን ተቀበሉ። ታላቁም ኢያ-...

317 **ኢያሱ** የሚለው ቃል “ይሖዋ-አዳኝ” ማለት ነው። **ኢየሱስም** እንዲሁ፡ “አዳኝ” ማለት ነው። ኢያሱም፡ መልእክተኞቹን፡ ሲያውቅ...

318 መልእክተኞቹም፡ ተመልሰው፡ “ትእዛዝህን ፈጽሜአለሁ። ቴፖቹን ስናጫውት ያገኘናት፡ አንዲት ሴት ነበረች፡ ታውቃለህ። ያመነች አንዲት ሴት አገኘን። እኛም፡ በዚያ ቀይ ምልክት ሰር የሚመጣ ሁሉ፡ ምልክቱ፡ ትርጉም እንደሚኖረው ነገርናት። አሁን ያንን ሰብኬአለሁ። ታከብረዋለህ ወይ፡ ኢያሱ? ”

“ያንን እንድታደርጉ ልኬአችኋለሁ።” አሜን።

319 ከዚያም፡ እግዚአብሔር፡ ያንን ሲያከብረው፡ ቤቱ በፍጹም አልፈረሰም። ኢያሱም እዚያ ቆሞ ሁሉንም ነገር ለማጥፋት ምልክት ሲሰጥ፡ ቀጥ ብሎ ወጣ፡

ረዓብና ቤተሰቦቿ ሁሉ በትክክል ተቀመጡ፡ ንብረታቸውም ሁሉ፡ አሜን፡ አሜን፡ ንብረታቸው ሁሉ በቤቱ ውስጥ፡ በሰላም ነበሩ። እዚያ ዝም ብለው ቆሙ፡ ከመስኮትም መመልከት አላስፈለጋቸውም። ጦርነቱ እየተካሄደ እያለ ቅዱሳት መጻሕፍትን ማንበብ ይችሉ ነበር።

320 እርሷም ወዲያው ተመልሳ፡ ጄኔራሉን በሠራዊቱ ውስጥ አግባባች፡ ተነሳችም፡ ወደ ቤተልሔም መጣች፡ ድርሻዋም በዚያ ተሰጣት። እርሷም… ታዋቂ የሆነ ወንድ ልጅ ወለደች፡ ያም ታዋቂ ልጅ ሌላ ታዋቂ ልጅ ወለደ፡ ያም ልጅ ሌላ ታዋቂ ልጅ ወለደ፡ ታላቁ ታዋቂው ልጅ፡ እስኪመጣ ድረስ። ቀጥታ ወደ ታች፡ በኢዮቤድ በኩል፡ በእሴይ በኩል፡ እንዲሁም ወደ ዳዊት። ልክ ነው፡ ጋለሞታይቱ ረዓብ፡ የመልእክተኛውን መልእክት ሰላመነች። ምልክቱን ተግባራዊ አደረገች፡ ቤቷም ዳነ፡ አለበለዚያ ግን በነበረችበት ታች ትጠፋ ነበር።

321 አሁን በደንብ አዳምጡ። ኦህ፡ እስኪ፡ አውቃችሁታልን? በግብጽ ከሥሩ የነበሩት ሁሉ ዳኑ። በኢያሪኮ ከሥሩ የነበሩት ሁሉ ዳኑ። ዛሬም ከሥሩ የሚሆኑት ሁሉ ይድናሉ። በደም-የጸና፡ የደሙ ጠቦት፡ የኢየሱስ ክርስቶስ ጥላ ነው።

322 በዕብራውያን 13፡10 እና 20 ላይ። ለማንበብ ጊዜ የለኝም። ዝቅ ብዬ። አነበዋለሁ። "ኤቨርላስቲንግ ቃል ኪዳን" ይባላል። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም "የዘላለም ቃል ኪዳን" ይባላል። አዎን፡ ወዳጄ! "ኤቨርላስቲንግ ቃል ኪዳን።"

323 "ዘለአለማዊ ቃል ኪዳን" ለምን አልተባለም? ምክንያቱም ዘላለማዊ አይሆንም። ከተቤዠን በኋላ፡ ያኔ ሁሉም ነገር ያበቃልና። **ኤቨርላስቲንግ** ነው፡ ትርጉሙም፡ "የተወሰነ ዘመን፡" ጊዜው እስኪያበቃ ድረስ ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ሌላ አይኖርም። ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፡ ቃል ኪዳን እያስፈልገንም። ጊዜው እስኪደርስ ግን፡ ቃል ኪዳኑን ያስፈልገናል።

324 አስታውሱ፡ ዕብራውያን 13፡10-20፡ "ኤቨርላስቲንግ ቃል ኪዳን፡" ይላል። የእግዚአብሔር በደም-ባጸናው ቃል ኪዳን ከሐጢአት ነጻ ያደርገናል። አሜን! በእርሱ ውስጥ ኃጢአት የለም፥ ኃጢአት፡ ራሱ፡ ሰጋ።

325 አምልኩት ተሰፋ የተሰጠበትንም ኃይሉን ግለጡ! በደም-የጸኑ፡ በምልክት-የጸኑ፡ የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ህዝቦች የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ አላቸው፡ ይህም፡ "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡" ቃል ኪዳኑን እያሳየ ነው። አያችሁ?

326 አዲስ ኪዳን! **ኪዳን** ማለት "ስምምነት" ማለት ነው። ልክ ነው፡ አይደለም እንዴ፡ ዶክተር ቨይል? **ኪዳን** ማለት "ስምምነት" ማለት ነው። **አዲሱ ኪዳን** ማለት "አዲሱ ስምምነት" ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን፡ በጠቦቱ ሥር ያረጀ ስለነበረ፡ ሕይወቱ በአማኙ ላይ ሊመለስ አይችልም ነበር። አዲሱ ኪዳን የእግዚአብሔር በግ ነበር፡ የእርሱም ሕይወት ወደ እኛ ይመለሳል። የደሙ ሕይወት! አያችሁ? በአዲስ ኪዳን ውስጥ ደም ሕይወት ነው፡ አያችሁ፡ ሕይወት ከበጉ ደም ነው፡ ይህም አዲስ ኪዳን፡ አዲስ ስምምነት ማለት ነው።

327 ያም፡ እግዚአብሔር፡ "ከእነዚያ ቀናት በኋላ ሕጌን በልባቸው ጽላት ላይ እጽፋለሁ" አለ። አያችሁ? አያችሁ? "በድንጋይ ጽላት ላይ አይደለም፡ እንዲሁም፡ 'አዎ፡ ደሙን **እዚህ**—አለ፡ አሁን ምን ላድርግ ይላል፡' ማለት በሚገባችሁ በበግ ደም ላይ አይደለም? ነገር ግን በልባችሁ ጽላት ላይ፡ አያችሁ፡ ከመንፈስ ጋር ስምምነት ከሰዎቹ ጋር አደርጋለሁ።"

328 እርሱም ኃይሉን ያሳያል። ዮሐንስ 14፡12፡ እንዲህ ይላል፡ "በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ስራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል።"

329 **አዲስ ኪዳን** "አዲስ ሰምምነት፡" አዲስ ሕይወት ማለት ነው፡ ከእንግዲህ ወዲህ ኩነኔ በሌለበት፡ በደሙ ስር ሆነን፡ እውነተኛ፡ የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች እንድንሆን፡ እግዚአብሔር የጠየቀውን ሁሉ፡ ኢየሱስ እንዳሟላልን ያሳያል።

330 ሮሜ 8፡1 ላይ፡ "እንግዲህ በዚያ ሥር ላሉት ምንም ኩነኔ የለባቸውም፡" **እያመኑ** ላሉት አይደለም፡ "ከእንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት፡ እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ፡ እንደ ሥጋ ፈቃድ ለማይመላለሱ።" "ቃሌም መንፈስና ሕይወት ነው።" አያችሁ? ኦህ፡ ከዚህ ላይ ጥቅስ ወስጄ ለተጨማሪ ጥቂት ሰዓታት መቆየት አልችልም እንዴ። እኛ ግን በፍጥነት እናልፈዋለን፡ አያችሁ።

331 ከእንግዲህ ወዲህ ኩነኔ የለም፥ ከኃጢአት ነፃ፡ ከዓለም ጭንቀት ነፃ፡ ኩነኔ የለም። ለምን? "በአንድ መንፈስ፡ ወደ አንድ አካል፡ ለተጠመቁት።" እዚያ ላይ የጠቦቱ ደም ተቀብቷል። የሰማይ አምላክ ተቀብሏችኋል፡ የእናንተ... ሕይወቱ በእናንተ ውስጥ ነው፡ እናንተም የእግዚአብሔር ወንዶችና ሴቶች ልጆች ናችሁ።

332 የእናንተ ባሕርይ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው። ምንድነው፡ ትንሽ የሚገፋ ነገር ነውን? አይደለም፡ ወዳጄ! እግዚአብሔር የፍርድ አምላክ ነው። እርሱ የእርምት አምላክ ነው። በመንገዱ ላይ መሆን አለበት። ሌላው ነገር አይሰራም። እናንተም ያ ዓይነት ባሕርይ ያላችሁ ናችሁ፡ ምክንያቱም የአባታችሁ ባሕርይ ናችሁ። አያችሁ?

333 ምን? ሕይወት፡ (እርሱ) ያ ሕይወት፡ ለደም ሲወሰድ ተመልከቱ። አያችሁ? ሕይወት ራሱ ተወሰደ። አያችሁ? ሕይወቱ፡ በደሙ፡ ተወሰደ። አያችሁ? ደሙ ተቀባ፡ እና ሕይወቱ በእንስሳ ሕይወት ምክንያት፡ በአማኙ ላይ ሊመጣ አልቻለም። ሕይወቱ አይደለም...

334 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ ከሰው ልጅ ይልቅ፡ የላቀ፡ የላቀ፡ የላቀ ሰብዓዊ ፍጡር ነበር። አያችሁ? ያም የሰውን ልጅ አሁን ሰብዓዊ ፍጡር ብቻ ሳይሆን፡ የእግዚአብሔር ወንድና ሴት ልጅ ያደርጋችኋል፡ በእርሱ ውስጥ የነበረው የላቀ፡ የላቀ፡ የላቀ፡ የላቀ፡ የላቀ ሕይወት፡ በእናንተ ላይ ይመለሳልና፡ ኃጢአተኛ ከመሆንም ይለውጣችኋል፡ ከዓለምም ነገሮች፡ የቤተክርስቲያን አባል፡ እና የሐይማኖት ተቋም ተከታይ ከመሆን፡ ዳግም-የተወለደ ክርስቲያን፡ በመንፈስ የተሞላ ያደርጋችኋል፥ የእግዚአብሔርም ሕይወት፡ ልክ ከቀጥቃጭ ብረት ላይ እንደሚወጣ ብልጭታ፡ ሰትራመዱ፡ በበጎነት፡ በፍቅር፡ በየዋህነት፡ እና መንፈስ ቅዱስ ሲንቀሳቀስ፡ ሲናገር ከእናንተ ይፈልቃል። ኦህ፡ ማይ! ይኸው። እናም (በምኑ? ) መልእክቱን በመስማት፡ የእሳቱን ዓምድ በመመልከት፡ እና፡ "ከሞት ወደ ሕይወት ተሻግሬአለሁ" በሚለው የተባረከ ማረጋገጫ። ልብ በሉ፡ ስለዚህ፡ ምንም ዓይነት ኩነኔ የለም።

335 "ልባችን ባይፈርድብን፡ ያን ጊዜ ልመናችን እንቀበላለን፡" አያችሁ፡ "እናውቃለን።" ኃጢአት በልባችን ውስጥ ካለ ግን፡ ይፈርድብናል፡ እ— እንደውም ባንጀምረው ይሻላል። አያችሁ? ከኃጢአት ነፃ መውጣት አለባችሁ። ከኃጢአት ነፃ መውጣት የምትችሉበት ብቸኛው መንገድም በእርሱ ውስጥ መግባት ነው። የኃጢአት ብቸኛው መሸፈኛ ያ ነው፡ ክርስቶስ ነው።

336 አስታውሱ፡ የኪዳኑ ደም፡ የኪዳኑ ደም ያለ ምልክቱ እውቅና አያገኝም። ሊሆን አይችልም። አትችሉም። “እሺ፡ እ—እኔ ከነገሮች ተቀድሻለሁ፡” ትሉ ይሆናል። ያ ምልክቱ አይደለም። መንፈሱ ነው፡ ምልክቱ፡ የክርስቶስ መንፈስ በእናንተ ላይ። እመኑት!

337 አሁን፡ ተመልከቱ፡ ቃሉ የተሰፋውን ቃል ያረጋግጥልናል። ይህ ሁሉ እኔ እዚህ የጻፍኳቸው ማስታወሻዎች ናቸው። አያችሁ፡ ይመስለኛል፡ በዚህ ጉዳይ ላይ፡ ዝም ብዬ ቀኑን ሙሉ መሰበክ እችላለሁ። አያችሁ? ቃሉ የተሰፋውን ቃል ያረጋግጥልናል፡ ምክንያቱም የተሰፋው ቃል ነው። ቃሉም ተሰፋው ነው፡ ቃሉም እግዚአብሔር ነው፡ ቃሉም የእኛ—ነው። እኛ ቃል እንሆናለን፡ ቃሉም እኛ ይሆናል። “በእኔ ብትኖሩ፡ ቃሌም በእናንተ ቢኖር፡” ከዚያ፡ አያችሁ፡ አንድ ትልቅ ቤተሰብ ይሆናል። አያችሁ? ያረጋግጥልናል። ለምን? እንግዲህ፡ የእኛ አካል ነው። አያችሁ? አያችሁ? አያችሁ፡ የእኛ አካል ይሆናል። እንዴት ያለ ጽሑፍ ነው! እሺ። ያረጋግጥልናል፡ የተሰፋ ቃሉ።

338 ምልክቱ ክፍያው እንደተፈጸመና ተቀባይነት እንዳገኘ የሚያሳይ አርማ ነው። አሁን፡ ዋጋውን ሳትከፍሉ ከባቡር ትኬት ምልክቱን ማግኘት አትችሉም፥ ዋጋውን የምትከፍሉበት ብቸኛው መንገድም መክፈል ነው። ልክ ነው። ምን? እመኑት። ተቀበሉት። ለእግዚአብሔር ቃል ሁሉ ሙሉ ታዛዥነት ምልክቱን እንድታገኙ መብት ይሰጣችኋል። ሙሉ ታዛዥነት! የሐይማኖት ተቋማችሁ እንደሚሄደው የእርሱን ክፊል ሳይሆን፡ ሙሉውን። ቃሉን ሙሉ በሙሉ በመታዘዝ፡ እርሱም ክርስቶስ ነው፡ ወደ ክርስቶስ ያደርሳችኋል።

339 አሁን ወደ ውስጥ ገብታችሁ፡ እግራችሁ ግን ወደ ውጭ ቢንጠለጠልስ? ወደ ውስጥ ገብታችሁ፡ እጆቻችሁ ወደ ውጭ ቢንጠለጠሉስ? አብዛኛው ነገራችን ገብሮ፡ ልባችን ግን ወደ ውጭ ቢንጠለጠልስ? አያችሁ? አያችሁ? ልብ ገና በዓለም ውስጥ ነው? አያችሁ? እኛ ግን ያንን አናደርግም።

340 ሙሉ፡ የተሟላ መታዘዝ እናንተንና ቃሉን አንድ ያደርጋችኋል። በሙላት፡ ሁሉንም ታምኑታላችሁ። በሙላት በውስጣችሁ ነው፡ በእናንተም በኩል ሲሰራ ትመለከቱታላችሁ።

341 በብዙ ከንቱ ድርጊቶች ውስጥ አትመላለሱም። አያችሁ? ክርስቲያን ናችሁ። ማንም ምንም ቢል፡ በፍጹም አይነኳችሁም። በክርስቶስ ውስጥ ናችሁ። ሙሉ በሙሉ በአስተማማኝ ሁኔታ ውስጥ ናችሁ።

342 ሞት በራፍ ላይ ሲያንኳኳ፡ ምንም መያዣ የለውም፡ አያችሁ፡ በፍጹም። ለምን? **ከዚህ** ወጥቶ ወደዚያ መግባት ብቻ ነው።

343 ዕድሜ ምንም ትርጉም የለውም። ከዕድሜ አልፋችኋል። በዘላለም ውስጥ ናችሁ፡ ምክንያቱም በእርሱ ውስጥ ናችሁ። እርሱ ዘላለማዊ ነው። ወጣት፡ ያረጀ፡ የመካከለኛ ዕድሜ፡ ወይም ማንኛውም ብትሆኑ፡ ምንም ትርጉም የለውም። ቆንጆ፡ አስቀያሚ፡ አጭር፡ ወፍራም፡ ምን፡ ምንም ለውጥ አያመጣም። አያመጣም።

344 ወዲያና ወዲህ አትዞሩም፡ እንዲሁም እነዚህን ሌሎች ነገሮች ሁሉ አታደርጉም። እናንተ፡ ከዚያ ነገር አልፋችኋል። ሞታችኋል። ሕይወታችሁ በክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ውስጥ ተሰውሯል። እዚያ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል፡ በክርስቶስም ትመላለሳላችሁ። የምታዩት ብቸኛ ዓላማ

ክርስቶስ ነው። ያ ብቻ ነው። እርሱ ብቻ ነው፡ የምትመላለሱት በእርሱ ነው። ኦህ፡ ማይ! ያቺ መዝሙር ደጋግመን መዘመራችን አያስገርምም፦

መንገዴን ሁሌ በፍቅር ሙላው፡
ከሰማያዊት እርግብ ጋር ሰጓዝ፥
በፈገግታ በዝምሬ፡ ልሂድ፡
መንገዴን…

345 ወንድም ልሁን። ክርስቶስ ሰው ሊሆን ይገባል ያለውን ምሳሌ ልኑር። ለወንድም ወንድም፡ ለእህትም ወንድም ልሁን። ለ—ለአገልጋዮች አገልጋይ ልሁን። ለምሳሌዎች ምሳሌ ልሁን። ይህ ቃል ክርስቶስ መሆኑን ለዓለም ላሳይ። ይህንን ማድረግ የምችልበት ብቸኛው መንገድ ወደ እርሱ መግባት ነው። ምክንያቱም፡ እኔ ራሴ ላደርገው አልችልም፡ እናንተም ልታደርጉት አትችሉም። ነገር ግን ቃሉና እናንተ አንድ ሁኑ፡ ያን ጊዜ እርሱ ራሱን ይኖራል። እርሱ ሙሉ በሙሉ ሲቆጣጠራችሁ-… በእናንተ ላይ ሙሉ ቁጥጥር ሲኖረው፡ ቃልን ሁሉ ለማድረግ፡ እናንተ የኢየሱስ ክርስቶስ ህያው ደብዳቤ ናችሁ።

346 እርሱ **በዚህ** መንገድ ሲመጣ፡ “ይህንን ማድረግ እፈልጋለሁ” ቢል፡ እናንተም፡ “የለም፡ የለም፡ ያንን አላምንም” ብትሉ፡ አያችሁ፡ ገና በቃሉ ውስጥ አይደላችሁም። አያችሁ?

347 ሙሉ፡ አሁን ተመልከቱ፡ ሙሉ በሙሉ፡ አሁን፡ ለመላው የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ መታዘዝ ምልክቱን እንድናገኝ መብት ይሰጠናል። ከዚያም ሰን፡ ሰንጸልይ፡ ከጸሎታችን ጋር የምናቀርበው ምልክት ሊኖረን ይገባል።

348 እናንተ፡ “ጌታ ሆይ፡ እጸልያለሁ፡ ግን በእርግጥ የለኝም… ” ብትሉ እሺ፡ የላችሁም። ማቆማችሁ ሳይሻል አይቀርም፡ አያችሁ፡ ወደ… መጀመሪያ፡ ሂዱና፡ ምልክቱን ተቀበሉ፡ አያችሁ፡ ምክንያቱም እርሱ እውቅና የሚሰጠው ያንን ምልክት ነው። አያችሁ? አዎ፡ ጌታዬ!

349 ሰንጸልይ፡ ያን ጊዜ ምልክቱን ይዘን መቅረብ አለብን፡ “ጌታ ሆይ፡ ሙሉ በሙሉ፡ ታዝዤሃለሁ። ለኃጢአቶቼም ንስሐ ገብቻለሁ። ይቅር እንዳልከኝ ይሰማኛል። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠምቄአለሁ። መንፈስ ቅዱስ በእኔ ላይ ነው። አሁን ለክብርህ የተወሰነ ነገር አስፈልጎኛል። ጌታ ሆይ፡ ሰጠኝ። አሁን የእኔ ነው።” ያን ጊዜ **እዚህ** ጀርባ ላይ የሚያርፍ መልህቅ አለ፡ “ፊው-ፊው፡” የእናንተ ነው። አብቅቷል። ከዚያም ሁሉም አልቋል። ሁሉም አብቅቷል። እልባት አግኝቷል። “**ይህን**ን እጠይቃለሁ። እጠይቀዋለሁ። ላገኘው ይገባል።” አያችሁ? አያችሁ? “እኔ—ለክብርህ እፈልገዋለሁ።” አያችሁ? እሺ፡ ያው ነው፡ ከዚያም ዝም ብሎ ይሰጣችኋል። ያን ጊዜ የእናንተ እንደሆነ ታውቃላችሁ። ልጆቻችንም፡ የመሳሰሉትም፡ እንደዚያው ነው፡ ደሙን እንቀባለን፡ እናምነዋለን። አለቀ። እሺ።

350 ታዲያ እርሱ ምን ያደርጋል? ያላችሁን ምልክት ከጸሎታችሁ ጋር ማቅረብ፡ ስትችሉ፡ ለመላው የእግዚአብሔር ቃል ሙሉ በሙሉ ወደ መታዘዝ እንደመጣችሁ ያሳያል። ምልክቱን ስታገኙ፡ ቃልን ሁሉ እንደታዘዛችሁ ያሳያል። ያን ጊዜ፡ እናንተና ቃሉ አንድ ናችሁ፡ የምትጠይቁት እናንተ ራሳችሁ የሆናችሁትን ነገር ብቻ ነው። አያችሁ? አያችሁ? ያን ጊዜ፡ ለምን፡ ታውቃላችሁ።

351 እኔ **ለዚህ**፡ “እጅ ሆይ፡ ታዘዘኝ፡ ያንን መሀረብ ዘርጋና ያዝ!” ብለው ያደርገዋል። አያችሁ፡ እጅ ታዘዘኝ። ለምን? የእኔ አካል ነው። አያችሁ?

352 ያን ጊዜ እናንተና ቃሉ አንድ ስትሆኑ፡ የተሰፋ ቃል ሁሉ፡ ክብር ለእግዚአብሔር፡ የተሰፋ ቃል ሁሉ የእናንተ ነው። ይታዘዛችኋል። ያን ጊዜ ምን ማድረግ እንደምትፈልጉ ትጠነቀቃላችሁ። ዝም ብላችሁ፡ “ሳደርገው እዩኝ” ለማለት ብላችሁ፡ እጃችሁን በእሳት ውስጥ አታስገቡም። ኦህ፡ ኖ፡ አይሆንም! አያችሁ? ነገር ግን በዚያ እሳት ውስጥ፡ ልደርስበት የሚገባኝ ነገር ካለ፡ ይታዘዘኛል። አያችሁ? አያችሁ? በትክክል። አያችሁ፡ እያደረጋችሁት ያለውን ነገር መመልከት አለባችሁ።

353 ለዚህ ነው መንፈስ ቅዱስ በጥንቃቄ የሚሰጠው፡ እና ነገሮች፡ ምን ማለቴ እንደሆነ ታውቃላችሁ፡ ምክንያቱም አንዳንድ... እናንተ አትፈልጉም... እውነተኛ የእግዚአብሔር አገልጋይ በእርሱ አይታበይም፡ አያችሁ። ያ ነው። ያ ራስን ማሳየት ነው።

354 ስንጸልይ፡ ምልክቱን እናቀርባለን። ሙሉ በሙሉ እንደታዘዝን ያሳያል።

355 ጳውሎስ፡ “ደሙ ይናገራል፡” ይለናል። ያ፡ ደሙ፡ በእርግጥ፡ ራሱ መናገር እንደማይችል፡ ማንም ያውቃል። ኬሚስትሪ ነው። ልክ ነው? ያንን ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ነገር ግን ደሙ እንደሚናገር ስንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? ያንን መጸፍ ከፈለጋችሁ፡ ዘፍጥረት 4፡10። እግዚአብሔርም አለ፡ “ወንድምህስ? ” እንዲህ አለ፡ “የወንድምህ ደም ድምፅ፡ ከምድር በአንተ ላይ ይጮኻል።” ልክ ነው? ደሙ እየተናገረ ነው። ሃሌሉያ! እግዚአብሔር አለ፡ “የት አለ? ”

እርሱም፡ “የወንድሜ ጠባቂው እኔ ነኝን? ”

356 አለ፡ “ደሙም እየጮኸ ነው። ደሙ እየጮኸ ነው።” ምልክት ነው። መገደሉን የሚያሳይ፡ ምልክት ነው። ደሙ በእርሱ ላይ እየጮኸ ነበር።

357 አሁን፡ ያንን በዘፍጥረት 4፡10 ላይ ካያችሁ፡ በዕብራውያን 12፡24 ላይ፡ ማንበብ ጀምሩ። በዕብራውያን 10፡ 12፡24 ላይ። “የኢየሱስ ደም ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻል ይናገራል፡” ይላል።

358 አያችሁ፡ አቤል፡ ጻድቅ ሰው ነበር። ሞተ። የሞተውም፡ ንጹሕ ሆኖ ነው፡ ምክንያቱም በመንገዱ ላይ ነበር። እርሱ በመንገዱ ላይ ቆሞ የነበረው፡ ለነበረው እውነተኛ መገለጥ ነበር። ተናገረ። ጮኸ! የፍትሕ የሆነው የአቤል ደም በቃየን ላይ ጮኸ።

359 የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ግን፡ መጮህ ብቻ ሳይሆን፡ ተቤዠን። አሜን! “የሚሻልን ይናገራል።” ወንዶችና ሴቶች ልጆች ያደርጋችኋል። ከእግዚአብሔር ቁጣ ይሰውራችኋል። አያችሁ? የአቤል ደም ቃየንን ሊሰውረው አልቻለም፡ አያችሁ፡ ነገር ግን የኢየሱስ ደም ይችላል። አሜን!

360 ስለዚህ፡ ቃየን ሆይ፡ በቃሉ ላይ አሳዳጅ ከሆንክ፡ እና፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል። ይህ ነገር ሁሉ ከንቱ ነው፡” እና የመሳሰሉትን የምትል ከሆንክ፡ ዛሬ ውጣ።

361 እርሱ እየጮኸ ነው፡ አያችሁ። የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይጮኻል፡ ነገር ግን ከተቀበላችሁት በእርሱ ውስጥ ይቅርታ አለው። በዚህ ላይ በጥቂቱ መቆየት በቻልን ብዬ እመኛለሁ፡ አያችሁ፡ “ደም የሚሻልን ይናገራል።”

362 እመኑ፡ ለደህንነት። ከዚያም ቀቡት፡ አያችሁ። ለ... እመኑ ለማመን የሚገባችሁ ይህ ነው። አያችሁ፡ የራሳችሁን ደህንነት ፈልጉ። ለደህንነታችሁ እመኑ፡ ከዚያም ምልክቱን ለመላው ቤተሰብ ቀቡት። አያችሁ? እናንተም፡ “ያንን እንዴት ላደርገው እችላለሁ” ትሉ ይሆናል? ዋጁት! በእናንተ ላይ ከሰራ፡ ያን ጊዜ እናንተና ቃሉ አንድ ትሆናላችሁ። አሜን! አሜን! አያችሁ? አያችሁ፡ ለሁለታችሁም ይሰራል። እናንተና ቃሉ አንድ ናችሁ፡ ከዚያም በልጆቻችሁ ላይ ቀቡት፡ በምትወዷቸው ሰዎች ላይ ቀቡት።

363 ረዓብ እንዳደረገችው፡ ምልክቱን በአባቷ ላይ ተገበረችው፡ በእናቷ ላይ ተገበረችው፡ በወንድሞቿና በእህቶቿ ላይ ተገበረችው፡ እና ሁሉንም አስገባች።

364 እናንተም ተግብሩት፡ ከዚያም፡ “ጌታ ሆይ፡ ልጄን ፍለጋ ልሄድ ነው። ሴት ልጄን ፍለጋ ልሄድ ነው። ለራሴ ዋጀኋት!” “ሰይጣን፡ ልቀቃት! ወደ እርሷ ልመጣ ነው። ምልክቴን፡ መንፈስ ቅዱስን ቀባኋት።” “በእኔ ውስጥ የምትኖረው፡ መንፈስ ቅዱስ ሆይ፡ እዚያ ያለችውን ልጄን ያዛት። ቅባትህ በእኔ ላይ ሆኖ፡ አሁን ወደ እርሷ ልሄድ ነው።” እርሱ ያደርገዋል። አሜን።

365 በግብጽ ያደረጉትም ይህንኑ ነው። በኢያሪኮ ውስጥ ያደረጉት ይህንኑ ነው።

366 ሌላ ማንበብ ትፈልጋላችሁ፡ የሐዋርያት ሥራ 16፡ 31። ጳውሎስ ለመቶ አለቃው እንዲህ አለው፡ “በዘመኑ መልእክት እመን። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፡ አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ።” ልክ ነው? ለቤትህ እመን፡ ሁሉንም በእርሱ ስር አምጣቸው። “አሁን የሰማይ አምላክ ተአምር ሲሰራ አይተሃል። ከፍርድ በፊት ነው። ታምነዋለህ? ”

“አዎን! ምን ላድርግ? ”

367 እርሱም፡ “ተነሰና ተጠመቅ” አለው። ጳውሎስ ወደ ውጭ አውጥቶ አጠመቀውና፡ “አሁን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፡ አንተና ቤተሰቦችህ ትድናላችሁ፡” አለው።

368 ምን ማመን? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን፡ ለቤትህ፡ ምልክቱን በቤትህ ላይ አድርገው።

369 ታዲያ በቤታችሁ ላይ ስትቀቡት ምን ታደርጋላችሁ? ቆሻሻውን ሁሉ አውጡ። አጫጭር ቀሚሶችን፡ እና ቁምጣዎችን፡ እና ካርዶችን፡ እና ሲጋራዎችን፡ እና ቴሌቪዥኖችን፡ እና ሌሎችንም ሁሉ አውጡና፡ ምልክቱን ለመተግበር ስትሄዱ፡ በበሩ ወደ ውጭ አባርሯቸው፥ ችላ አትበሏቸው። አዎ፡ ጌታዬ። ሁሉንም አውጡት። ዳንሶች ሁሉ፡ ፓርቲዎች ሁሉ፡ የሮክ-እና-ሮል፡ የብልግና ጋዜጣዎችን፡ እና የዓለም ነገሮችን፡ ከበሩ ወደ ውጭ አሰወግዷቸው፡ “ይህንን ሰፍራ እያጸዳነው ነው፡” በሉ።

370 ያዕቆብ እንዳደረገው፡ እርሱም፡ ለሚስቱና ለሁሉም፡ እንዲህ አላቸው፡ “ልብሶቻችሁንና ሁሉንም ነገር አጥቡ። አማልክትን አሰወግዱ።” አሜን። አ-...

371 ከመሻገራቸው በፊት ኢያሱ ምን እንዳለ ታውቃላችሁ? እንዲህ አላቸው፡ “ልብሳችሁን አጠቡ፥ ወደ ሚስቶቻችሁ አትቅረቡ፡ እና ወዘተ፡ እና ተዘጋጁ፡ በሦስት ቀናት ውስጥ ዮርዳኖስን እንሻገራለንና።” አሜን። እየተዘጋጀ ነበር፡ ምልክቱን እየተቀባ ነበር። አሜን። ያ ነው።

372 ተዘጋጁ። ቀቡት። እመኑት። ንጹሃን ሁኑ። ልጆቻችሁ፡ ቤተሰቦቻችሁ፡ የምትወዷቸው ሰዎች፡ በእናንተ ውስጥ ይዩት። ልክ ነው። ውጤት ያመጣል። አዎ፡ ጌታዬ!

373 ከዚያም ምልክቱን በጸሎት ሆናችሁ ቀቡት፡ ከ—ከ—ከመረዳት ጋር፡ በማመን። በጣም በፍቅር፡ ወዘተ ቀቡት፡ እንደሚይዝ፡ እንደሚፈጸም እስከታውቁ ድረስ። በቃ። እንደሚረዳ በማመን፡ በልበ ሙሉነት ቀቡት። ያንን ልጅ ስታነጋግሩ፡ ባላችሁን ስታነጋግሩ፡ ሚስታችሁን ስታነጋግሩ፡ ይህንን የምትወዱትን ሰው ስታነጋግሩ፡ እንደሚረዳው እመኑ። እዚያው ጸንታችሁ፡ “ጌታ ሆይ፡ የእኔ እንደሆኑ አውጃለሁ። የእኔ ናቸው። ጌታ ሆይ፡ ለአንተ ላመጣቸው ነው፡” በሉ።

374 ቀቡት፡ እና በዙሪያችሁ ያንን ድባብ ፍጠሩ፡ ልክ ወደ እርሱ ዘልለው እንዲገቡ። አያችሁ? ኦህ፡ እናንተ፡ እናንተ፡ ምልክቱ ካላችሁ፡ በእናንተ ዙሪያ መንፈስን፡ ኃይልን ትፈጥራላችሁ፡ ስትራመዱ፡ ሰዎች እናንተ ክርስቲያን እንደሆናችሁ ያውቃሉ። ለእነርሱ የሆነ ነገር እንድትነግሯቸው ይወዳሉ። ቃላችሁን ያምናሉ። የምትናገሩትን፡ አጥብቀው ይይዙታል። አያችሁ? ያ ነው።

375 ምልክቱን ቀቡት፡ ከዚያም በእርሱ ተመላለሱ። ቤተሰባችሁን የራሳችሁ እንደሆኑ ዋጁ። አሁን ማድረግ አለባችሁ። ይህ የማምሻው ዘመን ነው። አሁን፡ ለረጅም ጊዜ አዳምጣችኋል፡ ይህ የማምሻው ዘመን ነው። የመቀባት ዘመን ነው። ከእነዚህ ቀናት በአንዱ፡ ቁጣው ይመታል፡ ያን ጊዜ በጣም ሊረፍድ ይችላል። አያችሁ? ምልክቱን፡ በልበ ሙሉነት ቀቡት።

376 ያንን ማንበብ ከፈለጋችሁ፡ እዚህ የሆነ ነገር አንብቡ፡ ለዚህ የጻፍኩት ጥቅሴ፡ ኤፌሶን 2፥12ን አንብቡ፡ እና መጻፍ ከፈለጋችሁ። ልብ በሉ፡ በኤፌሶን 2፥12 ላይ፡ ስታነቡት፡ እንዲህ ይላል፡ ይህም፡ የሞተ ስራን አናገለግልም፡ ነገር ግን ህያው አምላክን፡ በህያው ስራዎች እናገለግላለን። አሜን! ኦህ፡ ማይ! በህያው ስራዎች፡ በህያው ምልክቶች። በህያው ምልክቶች ታምናላችሁ? እንዲሁም ይህን ጻፉት፡ ዕብራውያን 9፥11-14፡ ያንን መጻፍ ከፈለጋችሁ። ህያው ምልክቶች፡ ህያው ስራዎች፡ ያንን ቀቡት!

377 የሞቱ የሐይማኖት መግለጫዎች አይሁን፡ “ልጄን ወደ ቤተክርስቲያን ወስጄ ቤተክርስቲያን አባል አደርጋለሁ።”

378 አንዳንድ ጥሩ ክርስቲያን ሰው፡ ጥሩ ጓደኛ፡ የድሮ ጓደኛዬ፡ እውነተኛ ሰው፡ እርሱ—እርሱ ወደዚህ መጣና፡ ተጠመቀ። እናቱም፡ “መጠመቅ—መጠመቅ ከፈለግክ፡ ወደ ትልቅ ቤተክርስቲያን ብትሄድ ኖሮ እመኝ ነበር” አለችው። አያችሁ? አያችሁ፡ ያረጁ የሞቱ የሐይማኖት መግለጫዎችንና የመሳሰሉትን አልፈለገም ነበር። አያችሁ?

379 የሞቱ የሐይማኖት መግለጫዎችንና የሞቱ አማልክትን አናገለግልም። እኛ የምናገለግለው ከዚህ በፊት ደሙ የፈሰሰውን ህያው አምላክ ነው፡ እኛም ደግሞ በህይወት እንድንኖር፡ ምልክቱ ተቀብቶልናል። አሜን። አዎ፡ ጌታዬ!

380 ሄዳችሁ እነዚያን የሞቱ የሐይማኖት መግለጫዎች አታገልግሉ። እነርሱ እንደ ምልክት ያሉትን ነገሮች እንኳን ይክዳሉ። እንዲህ ይላሉ፡ “የተአምራት ዘመን አልፏል። የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ብሎ ነገር የለም።” ታዲያ ለምን እንደዚያ ያለውን ነገር ትቀላቀላላችሁ? አያችሁ? ያንን አታድርጉ።

381 ምልክቱን ቀቡት፡ ከዚያም፥ “ህያው አምላክን አገልግሉ፡” ለህያው ሰራዎች፡ ህያው ምልክቶች፥ ህሙማንን የሚፈውሱ፡ ሙታንን የሚያስነሱ፡ ነገሮችን አስቀድመው የሚናገሩ፡ በልሳን የሚናገሩ፡ የሚተረጉሙ፡ ሁልጊዜም በትክክል፡ የሚተነብዩ እና **ይህና ይህ** ይሆናል የሚሉ፡ በላይ በሰማይ፡ በምድርም ላይ ምልክቶችን የሚያሳዩ፡ ምልክቶችና ድንቆች፡ አሜን፡ መጽሐፍ ቅዱስ ይሆናል ያለውን በትክክል የሚናገሩ። “ህያው አምላክን አገልግሉ፡” ምልክቱን ቀቡት!

382 ወደ እነዚያ አብያተ ክርስቲያናት አትሂዱና ያንን የሞተ ሰራና የመሳሰሉትን አትቀላቀሉ፡ ምክንያቱም እነርሱ ምልክትን በሚመስሉ ነገሮች እንኳን አያምኑም። ነገር ግን እኛ የምናምን፡ አሜን፡ እናውቃለን... እነርሱ እንዲህ ይላሉ፡ “ምልክት የሚባል ነገር የለም። ያ፡ ኦህ፡ ኦህ፡ ያ ከንቱነት ነው። እዚያ ላይ የሚያወሩት፡ እብደት ነው። ለምን፡ እንደዚያ ያለ ነገር የለም። ለምን፡ እናንተ ሴቶች እዚያ፡ ኦህ፡ እናንተ—እናንተ፡ እንዴ፡ ይህ አይደረግም... አለባበሳችሁ ምንድነው... ? ” ይደረጋል። መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላል። “ፀጉራችሁ ምን ልዩነት ያመጣል... ? ” መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚያ ይላል።

383 ያ፡ ያ ዝም ብሎ ልዩነቱ ነው፡ አያችሁ። “አትንኩት፡ አትያዙት፡ አትቅመሱት።” እርሱ እግዚአብሔር ነው። አያችሁ? ስለዚህ፡ የሆነ ትርጉም አለው።

384 ስለዚህ፡ እነርሱ እብደት እንደሆነ ያስባሉ። ነገር ግን ለእኛ ለምናምንና እውነትን ለምናውቅ፡ ይህ ህያው ሕልውናው እንደሆነ እናውቃለን፡ ምክንያቱም በምድር ላይ በነበረ ጊዜ ያደረጋቸውን ተመሳሳይ ነገሮች ያደርጋልና። አሜን።

385 “ኦህ፡” ይላሉ፡ “በምናባቸው የእሳት ዓምድ አይተናል ይላሉ።” ኦህ፡ ኖ! ኦህ፡ ኖ! የእኛ ምንም ነገር በምናብ አይደለም።

386 ጳውሎስም፡ በምናቡ ያየው መሰሏቸው ነበር። ግብፅም የእስራኤል ነገር በምናብ የተሳለባቸው መሰሏት ነበር፡ ሆኖም ወደ ተሰፋይቱ ምድር ወሰዷቸዋል። አዎ፡ ጌታዬ! እኛ እ...

387 ዕብራውያን 13፡ 8 ላይ፡ ታውቃላችሁ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትም፡ ዛሬም፡ እስከ ለዘላለምም ያው ነው፡” ያንን፡ እየጻፋችሁ ከሆነ፡ አያችሁ፡ ያ፡ “እርሱ ያው ነው።” ይህ—ይህ—ይህ አይደለም ያው... የሆነ ምናብ አይደለም።

388 እነዚህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እዚህ ሰጽፍ፡ መጽሐፍ ቅዱስ የት እንዳሉ አውቃለሁ፡ ወደ እነርሱም የምሄደው በዚህ መንገድ ነው። አያችሁ?

389 እርሱ በዚህ መንፈስ ያንኑ ያደርጋልና፡ ህያው መገኘቱ እንደሆነ እወቁ። አሁን፡ ወደሆነ የሐይማኖት መግለጫ ወይም የሐይማኖት ተቋም ገብቶ ቢሆን ኖሮ፡ ክርስቶስ እንዳልነበረ በፍጥነት እናውቃለን። ልክ ነው? ወደሆነ የሐይማኖት መግለጫ ወይም ሌላ ነገር፡ ብመራችሁ ኖሮ፡ ከተወሰነ የሐይማኖት ተቋም የተላክሁ እሆን ነበር። ነገር ግን የሐይማኖት መግለጫዎችን አላመጣላችሁም፡ የሐይማኖት ተቋማትንም አላስተምራችሁም። ለራሴ ብቻ ሳይሆን፡ ለሚፈልግ ሁሉ የተገለጠውን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ ኃይል የሆነውን፡ የእግዚአብሔርን ቃል፡ እያስተማርኳችሁ ነው። አያችሁ? ይህም እናንተ...

390 ወንድሞቼ ናችሁ። እኔ ታላቅ ሰው፡ እናንተ ትንሽ ሰው አይደላችሁም። በእግዚአብሔር ፊት ሁላችንም ትናንሽ ሰዎች ነን። አያችሁ? የእርሱ ትናንሽ ልጆች ነን። ልናውቀው የሚገባንን ያህል፡ ምንም አናውቅም። እንደ ፈቃዱ እንድናውቅ ያደርገናል፡ ሰለ በረከቶቹም ሰለምናውቀው ነገር ሰለእርሱ ምስጋናችን ብዙ ነው። ይህንንም ለብቻዬ አልካፈልም፥ ከእናንተ ጋር ልካፈለው እፈልጋለሁ። አያችሁ? ወደዚህ እንድትገቡ እፈልጋለሁ፡ ይህንንም ምልክት እንድትቀበሉ እፈልጋለሁ። ይህንንም ካላደረጋችሁ... ከእናንተ ብዙዎች፡ አብዛኞቻችሁ፡ ቀድማችሁ አድርጋችሁታል። ነገር ግን አንዳንዶቻችሁ ይህንን ካላደረጋችሁ...

391 አያችሁ፡ በቴፕም ላይ፡ እየተናገርኩ ነው፡ እንደምትረዱት። ከዚህም ብዙዎቹ... እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ አልልም፥ ሁላችንም ወጥተናል፡ ብለን እናስብ። ነገር ግን በሺዎች የሚቆጠሩ ሺዎች ቴፑን ይሰማሉ፡ አያችሁ። ይህ፡ ደግሞ፡ አገልግሎት ነው። ወደ ኢያሪኮ፡ በቴፕ ስተት ብሎ የሚገባ ሰው ይኖራል፡ ታውቃላችሁ፡ ስለዚህ እኛም—ወደዚያ ሲገባ ያንን አስቀድሞ የተወሰነውን ዘር ለመያዝ እንፈልጋለን፡ አያችሁ፡ ቁጣው እየመጣ ነውና።

392 የሕያው እግዚአብሔር መገኘት መሆኑን እወቁ፡ በተሰፋ ቃሉ መሠረት እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሳው ያረጋግጣል። “ጥቂት ጊዜ አለ ዓለምም ከእንግዲህ ወዲህ አያየኝም። ኢያሪኮ፡ ግብፅ፡ ከእንግዲህ ወዲህ አያዩኝም። እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ ምክንያቱም እኔ... ” “እኔ፡” የግል ተውላጠ ስም፡ ሁልጊዜ የሚጠቁመው፡ አያችሁ። “እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። እኔ ምልክት ነኝ። ትንሣኤዬም ምልክት ነው። የማደርገው ሥራ መታወቂያችሁ ነው፡ እኔንም በውስጣችሁ እንድታወቅ ያደርጋል።”

393 “የምሽቱ መልእክት ሲወጣ፡ በሎጥ ዘመን—እንደነበረ፡ በሰው ልጅ መምጣትም እንዲሁ ይሆናል።”

394 “ሲመሽ ብርሃን ይሆናልና። በማምሻው ዘመን ላይ፡ ብርሃን ይመጣል።” ኦ፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! በሠራዊት መካከል እንድሮጥ በቅጥርም ላይ እንድዘል ያደረገኛል። አያችሁ? አያችሁ? “ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።” ትክክል ነው። ነቢዩ ተናግሯልና።

395 “ከእናንተ ጋር እሆናለሁ። በሉተር ዘመን ውስጥ እሆናለሁ፥ በዌስሊ ዘመን እገኛለሁ፥ በጴንጤቆስጤ ዘመን ላይ እሆናለሁ፥ በማምሻው ዘመን ግን፡ ብርሃን ይመጣል።” የሐይማኖት ተቋማት ያልፋሉ፡ ምልክቱም ይቀባል። በዚያም ዘመን ውስጥ ያለፉ፡ ቅን ልብ ያላቸው ሁሉ፡ ያለ—ያለ እናንተ ፍጹማን አ—አይሆኑም። ነገር ግን በእናንተ ውስጥ...

396 ልክ እግርን ለመውሰድ፡ ራስ መሄድ እንዳለበት ነው። እጅን ለመውሰድ፡ ራስ መሄድ አለበት። ልብን ለመውሰድ፡ ራስ መሄድ አለበት። አፍን ለመውሰድ፡ ራስ መሄድ አለበት። አያችሁ፡ ራስ መሄድ አለበት።

397 አሁንም ምልክቱ በበሩ ጉበን ላይ፡ አያችሁ፡ በበሩም መቃኖች ላይ በሚቀባበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። “ከዚያም ደሙን ምልክት ሆኖ፡ በማይበት ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።”

398 አሁን በተቻለኝ ፍጥነት፡ እፈጥናለሁ። አምስት ደቂቃዎች፡ ወይም በአስር ደቂቃዎች ውስጥ፡ እንጨርሳለን።

399 እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሣው ያረጋግጣል። ታምናላችሁ? ዛሬ በመካከላችን አለ። እናም ይህ "እኔ" ክርስቶስ ነው። እና ያ "እኔ" እስከ ፍጻሜ ድረስ ከእኛ ጋር ነው፡ ይህም... እስከ **ፍጻሜው**፡" ማለት፡ "የዓለም መጨረሻ ነው።" ቃል እንደገባው እንደ ቃሉ መሰረት፡ "እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ እሆናለሁ" ብሏል። ቃል ገብቷል። "እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ።" ለእኛ ትርጉም የሌለው አይደለም። ምልክቱ ነው። ምልክቱ ነው።

400 ይህን የተቀደሰ የደም መሥዋዕት እንቀበላለን። መስዋዕት የሆነውን ደሙን እንቀበላለን፡ ከዚያም እ... ሕይወትን፡ ምልክቱን፡ የተስፋ ቃሉን ማኅተም የሚሰጠን እርሱ ነው። ኤፌሶን 4፥30 ላይ፡ "ደሙን አታሳዝኑ"፡ ይላልን? አይ። "የመንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ፡ በእርሱም ምን የሆናችሁበት... " [ጉባኤው፡ "የታተማችሁበትን" አለ።—አርታዒ።] "ቃል ኪዳን የተገባላችሁ፡ የተለያችሁ።" ቃል ኪዳን ተጋብታችኋል። አዎ። ምልክቱ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ማኅተም ይሆናል። ማንኛውም ነገር በማኅተም ውስጥ ሲታተም፡ ባትከፍቱት ይሻላል። ልትከፍቱት አትችሉም፡ እናንተ፡ የእግዚአብሔርን ማኅተም በጭራሽ። አይ። አያችሁ? ምክንያቱም እ... "ለቤዛችሁ ቀን የታተማችሁበትን፡ የእግዚአብሔርን መንፈስ ቅዱስ አታሳዝኑ፡" ይህም አካሉ የሚነሳበት ነውና።

401 ዘር ነው፡ ዘሩ የዘላለም ሕይወት እንዳለው የሚያሳይ ምልክት፡ "**ዞዊ**፡ 'የራሴ ሕይወት፡' በመጨረሻውም ቀን ደግሞ አስነሳዋለሁ።" ስትራመዱም፡ የክርስቶስ ሕይወት በእናንተ ውስጥ እንዳለ፡ እናንተም በእርሱ ውስጥ እንዳላችሁ መተማመን አላችሁ። "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡ በእርሱም በመንፈስ ቅዱስ ታትመናል፡" እንደዚህ ባሉ አማኞች መካከል፡ "ኢየሱስ እስከሚያስነሳን ቀን ድረስ።" ኡህ፡ ማይ! ምልክቱን ቀቡ። ለእኛ ትርጉሙ ይሄው ነው። ይህ መስዋዕት ሕይወትን እንደሚሰጠን እንጠብቃለን፡ እርሱም ይሰጠናል። ከዚያም ምልክቱን ይሰጠናል፡ እኛም ምልክቱን እንቀባዋለን፡ ይህም ማሕተም የሆነው እስከ... ከ—ከዚህ ተካፋዮች መሆን፡ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር ነው፡ ተካፋዮች መሆን፡ በዚህ በአንድ መንፈስ ተጠምቀን፡ ወደዚያ ወደ አንድ ምስጢ-... ተረታዊ አካል መግባት።

402 ያንን ቃል በትክክል አልኩት፡ **ተረታዊ**? መንፈሳዊ፡ መንፈሳዊ አካል፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል። አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ "ያንን በስህተት እየተናገርክ ነው" አለኝ። እኔ መሃይም ብሆንም፡ ዳሩ ግን እርሱ፡ "ያንን በስህተት እየተናገርክ ነው" አለኝ፡ "**ተረታዊ**፡" አልኩት፡ እርሱ ግን የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል ነው፡ አያችሁ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈሳዊ አካል። ትምህርት... ትምህርት አያስፈልገንም፥ መንፈስ ቅዱስ ያስፈልገናል። ዋናው እሱ ነው። አያችሁ? ዋናው እርሱ ነው። አዎ፡ አያችሁ፡ ያ... አንድን ሰው የትም ቦታ አደናቅፎ ሊሆን ይችላል፡ የሆነን የተማረ ሰው፡ አሁን በትክክል እንደሚረዳው ተስፋ አደርጋለሁ። መንፈሳዊ አካል! ለሆነ ነገር ይሆናል፡ ምክንያቱም እርሱ ያንን ባላለ ነበርና። አያችሁ? እርሱ አሁን ልክ እዚህ አለ። እሱ እዚህ ፑልቢት ላይ ይገኛል። እዚያ አለ። እሱ ነው። አያችሁ? ፊው!

403 በእርሱም ውስጥ ሞት የለም። በእርሱ ውስጥ ሀዘን የለም። በእርሱ ውስጥ ድካም የለም። በእርሱ ውስጥ ኃጢአት የለም። በእርሱ ውስጥ በሽታ የለም። በእርሱ ውስጥ ሞት የለም። እኛ በእርሱ ውስጥ ነን! ሰይጣን የሆነ

ነገር ሊያስታቅፋችሁ ቢሞክር፡ እንደ በሽታ፡ ዝም ብላችሁ ምልክታችሁን ወስዳችሁ ተቀቡት። ኦህ፡ ማይ! እናንተ በዋጋ የተገዛችሁ የኢየሱስ ክርስቶስ ንብረቶች እንደሆናችሁ፡ ምልክታችሁን ወስዳችሁ ተቀቡት። ምልክቱ የጉዞ ዋጋችሁ እንደተከፈለ ይቆማል።

እርሱ፡ “ስትሞት፡ ጠፍተሃል” ቢላችሁ።

404 እንዲህ በሉት፡ “ተሳስተሃል። በዋጋ የተገዛው ንብረት ነኝ። በዋጋ ተገዝቻለሁ። ምልክቱ አለኝ።”

“ምልክቱ ምንድን ነው? ”

405 እርሱ ምን እንደሆነ ያውቃል። ከእሱ ጋር፡ ከእሱ ጋር አትቃለዱበት። እርሱ ምን እንደሆነ ያውቃል። አሁን፡ ከእነዚህ አንዳንዶቹ ሰባኪያን ጋር ልትነጋገሩ ትችላላችሁ፡ እነርሱም ይከራከሯችኋል። ሰይጣን ግን አይከራከርም፥ ጠንቅቆ ያውቃል። አያችሁ? ኦህ፡ አዎን። በእርሱ ላይ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ፡ መጣበት፡ ታውቃላችሁ፡ ሊፈትነው ሲል፡ ስህተት ሰርቷል። የምትናገሩትን ሰይጣን ያውቃል። ዝም ብላችሁ ያንን ምልክት አሳዩት፡ ይበርራል። አዎን።

406 ምክንያቱም፡ ምንድን ነው? የታተመ ንብረት ነው። እርሱ ያንን ሰብሮ ከፍቶ፡ ልክ ያልሆነን ነገር በዚያ ውስጥ ሊያስገባ አይችልም። እንዲህ በሉት፡ “እጅህን አንሳ! ታትሜያለሁ።” ኦህ፡ ማይ! የታተመ ንብረት! አዎ፡ ጌታዬ! በዋጋ የተገዛችሁ ናችሁ። ምልክቱን በማይናወጠው በተሰፋ ቃሉ ላይ ባላችሁ እምነት ላይ ያዙ፡ ሲሰሽ ታያላችሁ። “የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች!” አያችሁ? አያችሁ? ምልክት ውሰዱ። እርሱ ለዚህ ነው። ሰይጣን ሊፈትናችሁ ነው።

በግብፅም ውስጥ ነበረ፡ ሊፈትን።

407 ለምን፡ ታውቃላችሁ፡ ረዓብ ያቺ ጋለሞታ ያንን... ጋለሞታይቱ ያንን ገመድ ወደ ታች ባደረገችበት፡ በዚያ ቀን፡ ከወታደሮቹ አንዳንዶቹ እንደሳቁባት እና እንዳፌዙባት አስባለሁ፡ እንዲህም አሉ፡ “ያቺ እብድ አሮጊት እዚያ ላይ! አእምሮዋን ስታለች። ተመልከቱ፡ እዚያ ላይ አንጠለጠለች። ሃ፡ ሃ፡ ሃ! እንዴ፡ እንደዚህ አይነት ነገር ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እንዴ፡ ዶክተር ጆንስ ተናግሯል፡ እርሱ፡ ‘ተራ ነገር ነው ምን የለውም’ ብሏል።” ዳሩ ግን አለው፡ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የሆነ መልእክተኛ መልእክቱን አምጥቶ ነግሯቸዋልና።

408 ግብጻውያኑ ይህንን ሲሉ ልታስቡ ትችላላችሁ፡ “ኧረ ተመልከት... እንዴ፡ እነዚያ የሆሊ ሮለሮች እዩዋቸው፡ ደም ሲቀቡ! ሃ፡ ሃ! አሁን ያንን ለማጠብ፡ ምንኛ አይቸገሩም! ኦህ፡ ማይ! እነዚያ ትልልቅ ያማሩ ቤቶች ሁሉ በደም አበላሿቸው! ኦህ፡ እንዴት ያለ ግማት ነው! በጥቂት ቀናት ውስጥ አስፈሪ እንደሚሆን እወራረዳለሁ። ምንም ትርጉም አይኖረውም። ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? **እገሌ-እና-እገሌ** የተባሉት ቅዱስ አባት እንዲሁ ብለዋል።” ዳሩ ግን ነበረው። ነበረው። የሆነ ትርጉም ነበረው።

409 ለምናምን ለእኛ የሆነ ትርጉም አለው። አያችሁ? በዚህ ቃል ላይ ያላችሁን የማትናወጥ እምነት ዝም ብላችሁ አስታውሱ! አሁን፡ ከእንግዲህ ሔዋን አደላችሁም። አያችሁ? ከእነዚህ ተጠራጣሪዎች አንዱ አደላችሁም፡ እና፡ ደህና፡

ከሰይጣን ጋር አታመቻምቹም። እያንዳንዱን የእግዚአብሔር ቃል ትይዛላችሁ። እያችሁ?

ሔዋን እንዲህ አለች፡ “እሺ፡ ጌታ እንዳለው!”

410 ሰይጣን እንዲህ አለ፡ “ግን፡ ታውቂያለሽ፡ ጌታ በእርግጥ እንደ አንቺ ላለች ቆንጆ ሰው እንዲህ ያለን ነገር አያደርግም። ኦህ፡ አንቺ በጣም ውብ ነሽ። አያደርገውም።” ኧረ፡ አዎ፡ ያደርገዋል፡ ደግሞም። እንደሚያደርገው ተናግሯል።

411 “እንግዲህ፡ አባቴ አገልጋይ ነበር። እኔ አገልጋይ ነበርኩ።” እኔ—እኔ ልረዳህ አልችልም። ያለ ምልክት፡ ጠፍታችኋል። ቊጣው በእናንተ ላይ ነው፡ አያችሁ፡ ያ ነው በቃ፡ ያለ ምልክት። አያችሁ? አዎ። እርሱ እንደሚያደርገው ተናግሯል፡ እርሱም ያደርገዋል። ያ፡ ያ በቀላሉ ይደመድመዋል። እርሱ እንደሚያደርገው ተናግሯል።

“ኦህ፡ እኔ እንደማምነው ከሆነ የተአምራት ዘመን… ”

412 አዎ፡ ነገር ግን እርሱ እንዳላለፈ ተናግሯል። “ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነኝ፡” አያችሁ፡ እርሱ መሆኑን የሚያረጋግጠውም ልክ ያንኑ ነው።

413 አሁን፡ ለእኛ፡ እናውቀዋለን። ለእነሱ፡ አያምኑትም። እኛ ግን ያንን እናምናለን። እውነት እንደሆነ እናውቃለን። አያችሁ?

414 ስለዚህም፡ በዚያ ውስጥ በመሆናችን፡ የቃሉ አካል ነን። ከዚያ በኋላ፡ በተሰፋው ቃል ላይ፡ “የምፈውስህ ጌታ እኔ ነኝ፡” የሚለውን ምልክትን ውሰዱ።

415 ስለዚህ ዛሬ ማታ ለፈውስ አገልግሎት ተዘጋጁ። አያችሁ? ምልክቱን ውሰድ፡ በቃሉ ላይ አንጠልጥለው፡ በዚያ ቃል ላይ ባለህ የማይናወጥ እምነት፡ ትወጣለህ። እንግዲህ፡ እርሱን የሚያሰወጣ ያ—ያ ነው፡ ምክንያቱም በእርሱ ዘንድ እንዲህ ያለ ነገር የለም።

416 ባለፉት ጥቂት ሳምንታት ውስጥ ሲከናወኑ ካየኋቸው ጥቂት ነገሮች ጋር፡ አሁን መመስከር ብችል እመኛለሁ። አያችሁ? አያችሁ? ኦህ፡ የቱን መሰክሬ እችለዋለሁ!

417 ታውቃላችሁ፡ ሉቃስ እንዲህ አለ፡ “ኢየሱስ ያደረጋቸው ሁሉ በመጻሕፍት ውስጥ ቢጻፍ፡ በ… በዓለም ላይ ያንን ለመጻፍ የሚያስችል በቂ መጻሕፍት አይገኙም ነበር።”

418 እኔ በራሴ አገልግሎት ውስጥ ብቻ ያየሁትን፡ እርሱ ሲያደርግ ያየሁትን፡ በዚህ መድረክ ላይ ያሉትን ጥራዞች እዚህ ላይ መደርደር አትችሉም። በራሴ አገልግሎት ውስጥ ብቻ ሲያደርግ ያየሁትን በዝርዝር ብጽፍ፡ ሲያደርገው አይቼዋለሁ። አያችሁ? በራሱ አገልግሎት ላይ ካደረገው ይልቅ በእኔ አገልግሎት ያደረገው ራሱ ይበልጣል። በትክክል። ይህ እየተቀዳ ነው። ስለዚህ፡ ልብ በሉ፡ በአሁኑ እጅግ ድል አስመዝግቧል፥ እኔ አይደለሁም፡ እርሱ። ክብር ይሁን! ሃሌሉያ!

419 በናዝሬት ካደረገው ይልቅ በጀፈርሰንቪል ያደረገው ብዙ ውጤት አስመዝግቧል። በዚያች ክፉ ከተማና በዚህች ክፉ ከተማ አደረገ። አሜን! ክብር! ምክንያቱም፡ “እዚያ ምንም ተአምር ማድረግ አልቻለም፡” እዚህ ግን አደረገ። በመጨረሻም እዚህ፡ ሰብሮ ገብቷል። እዚህ አድርጎታል። ሰዎችን

ከሌላ ሰፍራ ማግኘት ፈልጎ ሊሆን ይችላል፡ ዳሩ ግን እርሱ—እርሱ ምንም ይሁን ምን፡ አድርጎታል። ስለዚህ፡ እዚህ ጋር—በቅፍርናሆም ወይም—በናዝሬት ላይ፡ ከዚህ በበለጠ ስኬታማ ነበረ። በምድር ላይ በነበረው አገልግሎቱ ሁሉ ካደረገው ይልቅ ልክ እዚህ በዚህ ተበርናክል ውስጥ ብዙ ተአምራትን አድርጓል። ልክ ነው፡ እርሱ አድርጎታል። አሁንስ ስለ ቀሪው ዓለም? ኦህ፡ ማይ! አሁን እርሱ ያደረገው ያንን ነው።

420 አሁን አስታውሱ፡ "እርሱ" አደረገ። እናም፡ አደረገው ከቶ አላለኝም፡ አያችሁ፡ አይ፡ ምክንያቱም አላደረግሁትምና። በቃ አላደረግሁትም። ወደድሁት ራሴንም ለእርሱ አስገዛሁ፡ እርሱ ያለውንም ተናገርሁ፡ መንፈስ ቅዱስም ወደ ሌሎች ሰዎች ሄደ እነርሱም እርሱ ያለውን አመኑ፡ ከዚያም እርሱ ሥራውን አደረገ። በቃ ያ ነው።

421 ሁላችንም ያንን እንድናምን ሊያደርገን ከቻለ! ሁላችንም ልክ አሁን እንድናምነው ማድረግ ቢችል ኖሮ ልክ አሁን ምን ያደርግ ነበር፡ ልክ ነው? በከተማው ዙሪያ አንድም ደካማ ሰው አይኖርም ነበር። በትክክል። ሁሉም እንዲያምኑ ማድረግ ቢችል፡ ያበቃለታል። አያችሁ?

422 ምልክታችሁን በማይናወጠው በተሰፋ ቃሉ ላይ ባላችሁ እምነት ላይ ያዙት፡ ሰይጣንም ይሄዳል።

አሁን እዘጋለሁ።

423 እግዚአብሔር በአንድ ወቅት ለዓለም ሌላ ምልክት ሰጥቶ ነበር፥ እርሱም ቀስተ ደመና ነበረ። ያንን ታስታውሳላችሁ? እርሱ ለዚያ ምልክት ዘወትር፡ ዘወትር ታማኝ ሆኖ ኖሯል፡ ምክንያቱም ለምልክት ሰጥቶታልና። በእነዚህ በሺዎች በሚቆጠሩ ዓመታት ሁሉ፡ ያንን ምልክት ከማሳየት ወደ ኋላ ብሎ አያውቅም። ልክ ነው? ለምን? ያከብረዋል። የሰጠው ራሱ ነውና። ከእንግዲህ ወዲህ ዓለምን በጥፋት ውኃ እንዳያጠፋ ለዓለም ምልክትን ሰጥቷል። ከዚያም ቀን ጀምሮ፡ እርሱ ዘወትር፡ ዘወትር፡ አሳይቷል።

424 ያንን ቀስተ ደመና የሚፈጥሩ አንዳንድ ንጥረ ነገሮች፡ በአየር ውስጥ አሉ። ዝናብ ሲዘንብ፡ ፀሐይም ስትወጣ፡ ያ ያሳየዋል። ፀሐይዋ ዝናቡን ታደርቀዋለች፡ ስለዚህም ምድርን። ዳግመኛ ሊያጠፋ የሚችል በቂ ውኃ በምድር ላይ ከቶ እንደማይወርድ ለማረጋገጥ እርሱ ቀስተ ደመናውን በዚያ አኖረ። ያ ቃል ኪዳኑ ነው። ምልክት ነው። "እነሆ ምልክት እሰጣችኋለሁ፡" ብሏልና።

425 እርሱ ምልክቱን አክብሯል። በኖኅ ዘመን ምልክቱን አክብሯል። አሁንም ያሳየዋል። በግብፅም ውስጥ ምልክቱን አክብሯል። በኢያሪኮም አክብሮታል። ዛሬም ያከብረዋል። ምልክቱ በሚታይበት ጊዜ እርሱ ዘወትር ምልክቱን ያከብራል።

426 በእነዚህ ሁሉ ሺህ ዓመታት ውስጥ፡ ያንን ምልክት ማሳየት ወደደ። ፈጽሞ አይረሳውም። ምልክቱን አይረሳውም ። አሁን፡ ዓለም ምንም ያህል ቢለወጥም፡ ቀስተ ደመናው አሁንም አለ። አያችሁ፡ ምልክቱን ያከብረዋል።

427 አሁንም እንዲሁ ያደርጋል፡ እርሱ ምልክቱን ያከብራል። ቤተክርስቲያን ምንም ያህል ብትለወጥ፡ ምንም ያህል **ይህን** ብታደርግ፥ እግዚአብሔር አሁንም፡ ያንን ምልክቱን ብቻ ያከብራል። የሚያደርገውንና የሚናገረውን

ከማክበር ከቶ ወደ ኋላ እንደማይል ያሳየናል። ያንን እንቀበላለን፡ እኛ—እኛ ያንን እናከብራለን። አከብረዋለሁ።

428 በእምነታችን ላይ የእርሱን ምልክት ለሰይጣን፡ ለማያምኑት ኑፋቄዎቹና የሐይማኖት ተቋማቱ ሁሉ እንድናሳይ ይጠብቅብናል፡ የተሰፋ ቃሉ እውነት እንደሆነ እንደምናምን፡ እርሱም ሊያደርግ ቃል የገባውን ነገር ሁሉ እንደሚያደርግ እንድናሳይ ይጠብቅብናል። ቤተክርስቲያን ማለት ይቺው ናት።

429 እዚያ ውጭ እኛ እንደምንለው፡ ወደ መጀመሪያው ደረጃ እንኳን መድረስ አለመቻላቸው አይገርምም፥ አገላለጼን ይቅርታ አድርጉልኝ። የትም አለመድረሳቸው አይገርምም ዳሩ ግን ወደ የሐይማኖት ተቋም ተመልሰው የተሸሞነሞነ-መንጋ፡ ተሸሞንሙኖ-የለበሰና ህዝብ፡ ምሁራዊና፡ የተማረ ህዝብ ይፈጥራሉ። የትም አይደርሱም፡ ምክንያቱም የሚያሳዩት ያንኑ ነው፡ "ሜቶዲስት ነኝ። ፕሬስባይቴሪያን ነኝ።" በቃ ያ ብቻ ናቸው።

430 አማኞች ግን ምልክቱን ይወስዳሉ! ኢየሱስ በገሊላ ማድረግ የጀመረውን፡ አሁንም በቤተክርስቲያን ላይ፡ የመንፈስ ቅዱስን ምልክት በማሳየቱ ማድረጉን ቀጥሏል። ምክንያቱም፡ የሐዋርያት ሥራ አልነበረም፡ ዳሩ ግን በሐዋርያት ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነበረ፡ ያም ምልክት ነበረ።

431 ያልተማሩ ሰዎች መሆናቸውን ሰላዩ፡ ጴጥሮስና ያዕቆብ… ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ መልካም በሚባለው በር ሲያልፉ፡ ሊናገሩ ግድ እንደሆነባቸው ተናገሩ። እነርሱ እንዲህ ብለው ሊሆን ይችላል፡ "ይሄ፡ ያኛው፡ ተሸከም፡ ቆይ፡ አምጣ፡ ውሰድ። **ሰለዚህ** ነገር እነግራችኋለሁ።" እያችሁ? ሊረዱት የማይችሉት አይነት የሰዋሰው አጠቃቀም ሁሉ ሊኖራቸው ይችል ይሆናል። ሰለ ልዩነቱ ላያውቁ ይችላሉ፡ ሰለ መጽሐፍ ቅዱስ… ሰለ መጽሐፍ ቅዱስ ሰሌቶች ሁሉ—ላያውቁ ይችላሉ። ከኢየሱስ ጋር እንደነበሩ ግን አስተዋሉ። ያንን ምልክት ሊያሳዩ ችለዋል፡ ምክንያቱም ከመስቀሉ በፊት፡ በእርሱ ላይ የነበረው ያው መንፈስ፡ ከትንሳኤ በኋላ በእነርሱ ላይ ነበረና። አሜን!

432 ታዲያ እርሱ ያ ዕብራውያን 13፥8 እንዲሆን ያደርገዋል፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘላለምም ያው ነው።" እሱ ህያው መሆኑ የምናውቀው በዚህ መንገድ ነው። ለምን? እኛ እንደምንኖር እንዴት እናውቃለን? ምክንያቱም እሱ ህያው ነውና። በሕይወት መኖራችንን የምናውቀውም፡ እኛ እርሱን ሰለምንመስልና፡ በእርሱም ውስጥ ሰላለን ነው። እርሱም፡ "እኔ ህያው ሰለሆንሁ፡ እናንተም ደግሞ ህያዋን ትሆናላችሁ፡" ብሏል። በራእይ መጽሐፍ፡ "ሞቼ የነበርሁ፡ እነሆም ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ህያው ነኝ" አለ። እናም ለራሳችን—ለራሳችን ከሞትንና በእርሱ ውስጥ ህያዋን ከሆንን፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ህያዋን ነን። ከዚያም በእኛ ውስጥ ያለው የእርሱ ሕይወት ልክ እንደማንኛውም ሌላ ነገር ሕይወት ነው፡ እርሱ ምን እንደነበረ ያሳያል። ይህም እርሱ ትናንትናና፡ ዛሬ፡ እስከ ዘለአለም ድረስ ያው እንደሆነ ያደርገዋል።

433 አሁን እነርሱ ያንን ሲክዱ፡ እናንተ እንዴት ትችላላችሁ? "የሞተ ሥራን፡" አታዩምን? ህያው እግዚአብሔርን አምልኩ፡ በዘላለም… ማለቴ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ውስጥ በነበረው የሕይወት ኤቨርላስቲንግ ቃል ኪዳን። አሁን

በመቀጠል፡ ለማጠናቀቅ፡ እ... እንግዲህ፡ ልክ እዚሁ፡ የምናቆም ይመስለኛል። የጸጋውን፡ የፍቅሩን ምልክት፡ አያችሁ! አሁን፡ ይህ ምልክት ሳይተገበር...

434 አሁን፡ ይህ ምልክት ነው። ምልክት ምንድን ነው? ምልክቱ የተከፈለበት ስለመሆኑ ማሳያ ነው። ዋጋ የተከፈለ ነው። የመዳናችን ዋጋ ሞት ነበር፡ አያችሁ፡ ከክርስቶስ በቀር ማንም ሊከፍለው አይችልም። የ—የሃይማኖት ተቋም መንፈስ፡ የጳጳስ መንፈስ አይደለም፡ የአንድ ሰው ወይም ቅዱስ ሰው አይደለም፥ ነገር ግን የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ፡ በቤተክርስቲያን ላይ፡ ዕዳው እንደተከፈለ የሚያሳይ ምልክት ነው እግዚአብሔር የጠየቀውን ሁሉንም መስፈርቶች አሟልቷል፡ እኛ እና እርሱ አንድ ነን። "እኔ በአብ እንዳለሁ፡ አብም በእኔ እንዳለ፡ እኔ በእናንተ፡ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ፥ በዚያ ቀን ታውቃላችሁ።"

435 ምልክቱን ቀቡት! የትንሳኤውን ምልክት ቀቡት። ይህም፡ ምክንያቱም እኛን ለማጽደቅ እርሱ ስለተነሳ፡ እኛንም ደግሞ ከእርሱ ጋር አስነስቶናል። አሁን ደግሞ በምልክቱ ኅብረት ሥር፡ በክርስቶስ ኢየሱስ፡ በሰማያዊ ስፍራ ተቀምጠናል።

436 እስራኤል እዚያ ተቀምጣ ሳለች፡ ውጭም በጎዳና ላይ፡ ለቅሶ እየተሰማ በነበረበት ጊዜ፡ የሚጨነቁበት አንዲትም ነገር አልነበራቸውም። ብቸኛው ነገር፡ ደሙ፡ ምልክቱ፡ እየታየ መሆኑን እርግጠኞች መሆን ብቻ ነበረ።

437 ልክ አሁን እኛም ልንጨነቅበት የሚገባን ብቸኛው ነገር ያ ነው። በመንገድ ላይ—እየተፈጠረ ያለ መከራ አለ፡ ወዳጆች ሆይ። ብዙም አይቆይም፡ መከራው ይወርዳል። ያንን ታውቃላችሁ። ምልክቱ እየታየ መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ። ምልክቱም መንፈስ ቅዱስ ነው። "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናል፡ የክብሩም ተካፋዮች ሆነናልና፡" አሁን ወደ አገራችን፡ ወደ ቤታችን፡ ወደ ተሰፋይቱ ምድር በሚደረገው ጉዞአችን ነን።

438 ትወዱታላችሁ ወይ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—አርታዒ።] ምልክቱን ታምናላችሁ? ["አሜን።"] "ኦህ፡ ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ በዚህ ምልክት ስር እንድወድቅ፡ ጸልይልኝ፡" ለማለት የሚፈልግ ስንት ሰው አለ? ["አሜን።"]

ራሶቻችንን ዝቅ እናድርግ።

439 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እጅግ ጸጋ የሞላብህ! ዓለም በኃጢአት ውስጥ በነበረችበት ጊዜ፡ ማንም ሊረዳ በማይችልበትም ጊዜ፡ እግዚአብሔር፡ በምሕረቱ፡ ኃጢአትን ሊያስወግድ የሚችል ምልክት እንደሚመጣ፡ በጥላ፡ አስቀድሞ አሳየ፥ ዝም ብሎ የሚሸፍን ብቻ ሳይሆን፡ ነገር ግን ሊያስወግድ የሚችል። ኢየሱስም በትክክለኛው ጊዜ መጣ፡ እርሱም ደሙን፡ የራሱን ሕይወት አፈሰሰ፡ ወሰደ... ስለ ኃጢአታችን ማስተሰሪያ አድርጎልን፡ ከዚያም እርሱ እስኪመጣ ድረስ፡ ለቤተክርስቲያን የሚጠበቅ ምልክት የሆነውን መንፈስ ቅዱስን አድርጎ እርሱን መልሶ አቀረበ። ሐዋርያው ጴጥሮስም፡ "የተሰፋው ቃል ለእናንተና፡ ለልጆቻችሁ፡ ጌታ አምላካችን ለሚጠራቸው፡ በሩቅ ላሉት ሁሉ ነውና" ብሏልና።

440 ጌታ ሆይ፡ በጸጋህ፡ በእርዳታህ፡ ይህንን መልእክት የሚሰማውን ሁሉ ለእግዚአብሔር እንዲሆኑ ዋጀሁ። ለእግዚአብሔር ዋጇኋቸው፡ ጌታ ሆይ፡ እዚህ ዛሬ ጠዋት ያሉትንም ሆነ በቴፕ ስለሚሰሙትን ሁሉ፡ እጸልያለሁ።

እናም በማንኛውም ሰፍራ፡ አስቀድሞ የተወሰነ ዘር ቢኖር፡ ጌታ ሆይ፡ የዚህን የመጨረሻ ቀን ቃል ለመስማት፡ አሁን በገርነትና፡ በትህትና ይምጡ፡ የድል አክሊላቸውንም በመስቀሉ ስር ያስቀምጡ፡ ወይም የጠራቸውን፡ የእግዚአብሔር ጸጋ የድል አክሊል በማድረግ ራሳቸውን ያስገዙ። በመንፈስ ቅዱስም ይሞሉ በዚህም ምድር ላይ እስካሉ ድረስ በትንሳኤው የነበረውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሕይወት ምልክት ያሳዩ። ይሁንልን፡ ጌታ ሆይ።

441 እነዚህን ቃላት፡ ጌታ ሆይ፡ በትክክል አልተናገርኳቸው ይሆናል። ካልተናገርኳቸውም፡ ህዝቡ ያለ ምንም ክፋት እንዲረዳና እንዲያውቅ፡ መንፈስ ቅዱስ እነዚያን ቃላት ወሰዶ፡ መቅረብ በሚገባቸው መንገድ እንዲያቀርባቸው እጸልያለሁ። ፍቅር የሚያርም መሆኑንም እንዲያውቁ አድርግ። ይህ የሆነውም አሁን እየኖርንበት ባለው ሰዓትና፡ የጌታ መምጣት በመቅረቡ የተነሳ መሆኑን፡ እንዲሁም ጊዜው መድረሱን፡ የሚያሳዩት ታላላቆቹ ቀይ መብራቶች፡ በዓለም ሁሉ ላይ ብልጭ ሲሉ ስለምናይ መሆኑን እንዲያውቁ አድርግ።

442 ህዝቡ ዛሬ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ! በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጸልያለሁ፡ በፊትህም አቀርባቸዋለሁ። ቃል እንደገባኸውም፡ በሕይወት እስካለን ድረስ ምልክት ይሁንልን። አንተ ቃል ስለገባህና፡ እንደሚሆንም ስለማውቅ፡ ይህን መጠየቅ ቀላል ነው። በኢየሱስ ስም እንጸልያለን። አሜን።

አሁን፡ ራሳችንን እንዳጎነበስን፡ ለአንድ አፍታ እንቆይ።

443 በእምነት፡ እያመንኩ፡ በማውቀው መጠን ሁሉ፡ ስለ እናንተ ጸልያለሁ። በቅንነት፡ ስለዚህ ነገር መጸለይ በማውቀው መጠን ሁሉ ጸ—ጸልያለሁ።

444 ተመልከቱ፡ ይህን እረዳለሁ። ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የምተዳደረው በእናንተ አሥራትና መባ ነው። እዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ፡ ለእነርሱ የምሰብክላቸው ሰዎች እንዲኖሩኝ ያደረገው፡ የእናንተ ድጋፍ ነው። ፍቅራችሁ፡ "አሜንታችሁ፡" እና ህብረታችሁ ነው። በዓለም ውስጥ በመላው ሀገሪቱ፡ ወደ ተለያዩ ግዛቶች ስትሄዱ የምትናገሯቸው ደግ ቃላቶቻችሁ፡ መልእክቱ እንዲደርስ የሚረዳው የእናንተ ቃላት ነው። እናንተው ናችሁ። በዚህ ውስጥ፡ ከክርስቶስ ጋር አንድ አካል ነን። ወንድማማቾችና እህቶች ነን፡ እርሱም ንጉሳችን ነው። እወዳችኋለሁም። እ—እ—እ—እኔ፡ ባለሁበት፡ እናንተም እንድትሆኑ እፈልጋለሁ። ለእናንተ ጥቂት ጊዜ ለመናገር፡ ሀገሪቱን አቋርጬ በመኪና እጓዛለሁ። እሁድ ጠዋት ከእናንተ ጋር ለመገናኘት እናፍቃለሁ። እወዳችኋለሁ። ሁሌም እወዳችኋለሁ። አንዳንድ ጊዜ በጣም ጠንከር ብዬ መናገር ይኖርብኛል፡ ነገር ግን ለማረም ያህል ብቻ ነው። እያችሁ፡ ይህ ስለምወዳችሁ ነው፡ እያችሁ፡ እንድታጡትም አልፈልግም። እናንተ፡ ይህን ማድረግ የለባችሁም።

445 አሁን፡ በጣፋጭነትና በትህትና፡ በልባችሁ ውስጥ ባለው ሁሉ፡ በጥልቅ፡ ብቻ ተቀበሉት። እንዲህ በሉ፥ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ አሁን በውስጤ ያለውን፡ አንተን የማይመስለውን ሁሉ ውሰድ፡ ትዕቢቴን ሁሉ፡ በውስጤ ያለውን ሁሉ አውጥቼ እንድጥል፡ ፍቀድልኝ። በውስጤ ያለው ቆሻሻ ሁሉ፡ አለማመን ሁሉ፡ እ—አሁን እጥለዋለሁ፡ ጌታ ሆይ። አሸቀንጥሬ እጥለዋለሁ። ጣፋጭ የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም፡ እንደ ርግብ፡ ወደ ውስጤ ይውረድ። ለ—ለዘላለም መኖር እፈልጋለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ በ—በዚህ ጊዜም እንድትረዳኝ እፈልጋለሁ። አሁን ይሁንልን።"

446 እናንተ እየጸለያችሁ ሳለ፡ ይህን መዝሙር እናንጎራጉራለን፡ ወይም ድምጻችንን ዝቅ አድርገን፡ በአንድነት እንዘምራለን፡ **እወደዋለሁ**። ደግሞም፡ አስታውሱ፡ እርሱ የሚመጣው በፍቅር ነው፡ እርሱ ፍቅር ነውና። ሰዎቹ ሳይመሽ በፊት ሊወስዷቸው ስለሚችሉ፡ እጆቼን በእነዚህ መሀረቦች ላይ እያደረግሁ ነው።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ፡

አሁን ሕይወታችሁን ለእርሱ አሳልፋችሁ ስጡ።

መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ…

447 ውደዱት፡ ውደዱት፡ ውደዱት። ምን እንዳደረገላችሁ እዩ። በፍቅር ነው። ፍቅር መታዘዝን ያመጣል። ፍቅር መተጫጨትን ያመጣል። ፍቅር ጋብቻን ያመጣል። እኛም እያመራን ያለነው ወደዚያ ነው፥ ወደ በጉ የሰርግ እራት። አዳኜንም ሲጠራኝ እሰማለሁ፡ እርሱም፡ ይወደኛል።

… እኔም፡ እ።

እ…

448 በሙሉ ልባችሁ፡ የሆነ ነገር በጣም በጣፋጭነት ወደ ውስጣችሁ ሲገባ ይሰማችሁ። ያ መንፈስ ቅዱስ ነው።

ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

449 ከ… ከህዝቡ ጋር፡ ከሙዚቃው ጋር፡ እጆቼን አነሳለሁ። ኃጢአት ሰርቼ ከሆነ፡ አንዳች ስህተት አድርጌ ከሆነ…

አሁን ስለ እናንተ፡ እንዲሁም ስለራሴ እየጸለይሁ ነው።

450 አንዳች ስህተት አድርጌ ከሆነ፡ እጄን ወዳንተ ማንሳቴ፡ ጌታ ሆይ፡ ይቅርታ ማለቴ ነው። እጄን ወዳንተ ማንሳቴ፡ ጌታ ሆይ፡ ማ—ማድረግ አልፈለግሁም ማለቴ ነው። እየሞትኩ መሆኔንም አውቃለሁ፡ ጌታ ሆይ። ይህን ዓለም፡ በአካላዊ ማንነት መተው ይኖርብኛል። ከአንተ ጋር መገናኘት እፈልጋለሁ። እጄን ማንሳቴ፡ ውሰደው ጌታ ሆይ፡ ማለቴ ነው። በመንፈስ ሙላኝ። በእኔ ላይ ያለውን የፍቅርህን ምልክት፡ መንፈስ ቅዱስን ስጠኝ፡ ያም በጣፋጭነት፡ በገርነት እንድኖር የሚያደርገኝን፡ በክርስቶስ ውስጥ የነበረውን ሕይወት እንድኖር የሚያደርገኝን፥ ልቤ ለሌሎች እንዲቃጠል፡ ማግኘት የምችለውን ሰው ሁሉ እስካገኝ ድረስ፡ ቀንም ሆነ ማታ፡ እረፍት እንዳላገኝ የሚያደርገኝን። በኢያሪኮ እንደነበሩት መልእክተኞች እሆናለሁ፥ ወደምችለው ሰው ሁሉ እሄዳለሁ፡ ምልክቱን እንዲቀበሉ ከደም ኪዳን ስር፡ ከበጉ ደም ስር፡ እንዲመጡ ማድረግ እችል እንደሆነም እያለሁ።

451 እያችሁ፡ ደሙ ያነጻል። ደሙ ስለመቀባቱ የመንፈስ ምልክት ነው። እያችሁ? ደሙ ስለመቀባቱ መንፈሱ ምልክቱ ነው። ደሙ እስኪቀባ ድረስ፡ መ—መንፈስ ሊመጣ አይችልም። ደሙ ሲቀባ ግን፡ መንፈስ ምልክት ነው፡ ያኔ በደሙ ላይ ያላችሁ እምነት ተቀባይነት እንዳገኘና፡ ዋጋችሁ እንደተከፈለላችሁ፡ ወደ እናንተ መልሶ በመላክ ምልክት ይሆናል። ዋጋችሁ ተከፍሏል። ሁሉም አልቋል። ክሱ ተዘግቷል። እናንተ ክርስቲያን ናችሁ። አማኝ ናችሁ። ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ነው፡ እናንተም በክርስቶስ ናችሁ።

… ቀድሞ ወደደኝ
መዳኔንም ገዛው
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

452 አሁን በእግዚአብሔር ፊት ልባችሁ እንደተደፋ፥ እረኛችሁ፡ ወንድም ኔቭል፡ በመዝጊያ ቃላቱና ሊናገረው ባለው ነገር ይቀጥላል።

453 የዛሬ ማታውን አገልግሎቶች፡ የፈውስ አገልግሎቱን አስታውሱ። በጊዜ ኑ። በሰባት ሰዓት እንጀምር፥ በሰባት-ተኩል መድረክ ላይ ልውጣ። ይህ መልካም ነው፡ ወንድም ነቪል? [ወንድም ኔቪል፡ "በጣም ጥሩ ነው" አለ።—አርታዒ።] እያችሁ፡ ዛሬ ማታ፡ የጌታ እራት ይኖረናል። ኑ!

454 ዛሬ ከሰዓት በኋላ፡ እጥብቃችሁ ያዙ። ይህ መልእክት እንዲሄድ አትፍቀዱለት። አስታውሱ፡ ይህ መልእክት እንዲሄድ በፍጹም አትፍቀዱ!

455 ሕይወት ለመስጠቱ ደሙ ምልክት ይሆናል። እያችሁ? "ደሙንም ባየሁ ጊዜ፡ አልፋችኋለሁ።" ደሙ በልባችሁ ላይ ለመቀባቱ መንፈስ ቅዱስ ምልክት ነው፡ ደሙም ለመቀባቱ ምልክት ነው። ከቶውኑ ካልተቀባ፡ ምልክቱ አይመጣም። ገባችሁ? "አሜን፡" በሉ። [ጉባኤው፡ "አሜን" አለ።—አርታዒ።] ደሙ መቀባት አለበት፡ ከዚያም ምልክቱ ይመጣል። የቤዛነት ደም ለመቀባቱና ዋጋችሁ ለመከፈሉ ምልክት ነው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ወንድም ኔቭል።

63-0901M ምልክት
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2026 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

Voice Of God Recordings

P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.

www.branham.org